# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 81ኛ ዓመት ቁጥር 346 ነሐሴ 16 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም

- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# ‹‹ወጣቶች ከተደመሩና ከተጋገዙ በአጭር ጊዜ የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ ይቻላል››

- ዶክተር ዐቢይ አሕመድ
የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር



ጌትነት ምህረቴ

አዲስ አበባ፡- ወጣቶች ለመለወጥ ከወሰኑና ከመገፋፋት ይልቅ ከተደመሩ፣ ከመጠላለፍ ይልቅ ከተጋገዙ፤ ውድ ጊዜያቸውን፣ ዕውቀታቸውንና የስራ ወዳድነት ባህላቸውን በአግባቡ መጠቀም ከቻሉ የኢትዮጵያን ብልጽግና በአጭር ጊዜ ማረጋገጥ ይችላሉ ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ትናንት በአዲሱ ንግድ ባንክ አዳራሽ ከመላው ሀገሪቱ ከተውጣጡ ወጣቶች ጋር “የወጣቶች ሚና” በሚል በተዘጋጀ ሀገር አቀፍ የወጣቶች የውይይት መድረክ ላይ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሰላምን፣ አንድነትንና ፍቅርን ማጎልበት ከቻሉና ጠንክረው ከሰሩ አገርን ማሳደግ ቀላል ነው፡፡

‹‹መላ የኢትዮጵያ ወጣቶች መተጋገዝ፣ መተባበርና መደመር ከቻላችሁ ለኢትዮጵያ ብልጽግና ብቻ ሳይሆን ለሌላውም ዓለም ትተርፋላችሁ›› ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ወጣቶች ራሳቸውንም ሆነ አገራቸውን ለመጥቀም ሁሌም ጊዜያቸውን በአግባቡ የሚጠቀሙና ለልማት ስራዎች ትጉህ መሆን እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል፡፡

ብልጽግናን የሚመኙ፣ በሀሳብ ልዕልና የሚያምኑ፣ በሰፈር አጀንዳ የማይጠመዱና ሌብነትን የሚጠየፉ ወጣቶች አገር እንደሚለውጡም አመልክተዋል፡፡

መንግሥት በትልልቅ ፕሮጀክቶችና የግሉን ዘርፍ በመደገፍ በርካታ ወጣቶች የስራ ዕድል ተጠቃሚ ማድረጉን አውስተው፤ ወጣቶች አካባቢያቸውን በመቃኘት ስራ ፈጥረው መስማራት እንደሚጠበቅባቸውም ጠቁመዋል፡፡

ለአብነትም መንግሥት በገበታ ለሸገር፣ በገበታ ለአገርና በግዙፍ

ወጣቶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# "በግድቡ ሳቢያ የሚመጣውን ተጽእኖ ለመግታት የውስጥ አንድነት ማጠናከር ያስፈልጋል"

-አምባሳደር ዲና ሙፍቲ
በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር ጄኔራል

ዋቅሹም ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- ከታላቁ ህዳሴ ግድብ ጋር ተያይዞ መልኩን በመቀያየር የሚመጣውን የውጭ ተጽእኖ ለመግታት የውስጥ አንድነትን ማጠናከር ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ዲና ሙፍቲ አመለከቱ።

በግድቡ ሳቢያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን በመንጌ ወረዳ የወርቅ ማምረቻ ማሽን መርቀው ከፈቱ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሀሰን የቤኒሻንጉል የማዕድን ዘርፍ ልማት ማሕበር በመንጌ ወረዳ ከሻፍ ቀበሌ ያስገነባውን ወርቅን በዘመናዊ መንገድ ማምረት የሚችል ማሽን መርቀው ከፈቱ፡፡

ማሕበሩ ትናንት ሥራ ያስጀመረው የወርቅ ማሽን ከሁለት ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት ሲሆን፣ ሙሉ በሙሉ ከኬሚካል ተጽዕኖ ነጻ መሆኑም ተመልክቷል፡፡

አቶ አሻድሊ ሀሰን የወርቅ ማምረቻ ማሽኑን መርቀው ሥራ ባስጀመሩበት ወቅት፤ ማሽኑ የወርቅ ማዕድንን በዘመናዊ መንገድ በማምረት የተሻለ የወርቅ ምርት ወደብሔራዊ ባንክ ለማስገባት እየተደረገ ላለው ጥረት ፋይዳው የጎላ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ወርቅ በማምረት ላይ የተሠማሩ ማሕበራት ከኬሚካል ነጻ የሆኑ ማሽኖችን ከመጠቀም በተጨማሪ የወርቅ ምርቱን ሙሉ በሙሉ ወደ

ርዕሰ መስተዳድር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# “የተቀላጠፈ አገልግሎት ባለማግኘታችን ለእንግልት ተዳርገናል”

- ተገልጋዮች

# “የቆዩ ውዝፍ ስራዎች ለአገልግሎቱ መጓተት ምክንያት ናቸው”

-የኢሚግሬሽን ዜግነትና ቪዛ አገልግሎት

በኃይሉ አበራ

አዲስ አበባ፡- የኢሚግሬሽን ዜግነትና ቪዛ አገልግሎት አሰጣጥ የተቀላጠፈ ባለመሆኑ ለእንግልት መዳረጋቸውን የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ገለጹ። በኮቪድ፣ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳይ እና ከስደተኞች ብዛት ጋር ተያይዞ የቆዩ ውዝፍ ስራዎች በመኖራቸው የአገልግሎት ፈላጊዎችን በሚፈለገው ፍጥነት ልክ ማስተናገድ አልተቻለም ሲል የኢሚግሬሽን ዜግነትና ቪዛ አገልግሎት ምላሽ ሰጥቷል፡፡

ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ቅሬታቸውን የገለጹት የኖርዌይ አገር ዜግነት ያላቸው ወይዘሮ ሂዳያ ዓለሙ የኢሚግሬሽን ዜግነትና ቪዛ አገልግሎት ለአገልግሎቱ ፈላጊዎች የተናበበና ትክክለኛ መረጃ አይሰጥም፡፡ አገልግሎት አሰጣጡም የተንዛዛ ነው ብለዋል ።

የቪዛ አገልግሎቱ በቴክኖሎጂ የተደገፈና ቀልጣፋ መሆን እንዳለበት የጠቆሙት ወይዘሮዋ፤ ተቋሙ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ፈጣን አገልግሎት ቢሰጥ ኖሮ ተገልጋዩ አይጉላላም ሲሉ ገልጸዋል።

ከአሜሪካ ላስቬጋስ፣ የመጡት ሌላኛዋ አገልግሎት ፈላጊ ወይዘሮ ጽጌረዳ አበባው በበኩላቸው፣ ለሶስት ወር ቆይታ 75 የአሜሪካን ዶላር ከፍለው ቪዛ እንዲመታላቸው የጠየቁ ቢሆንም የተመታላቸው ቪዛ ግን የአንድ ወር ቆይታ ያለው መሆኑን ገልጸዋል። ስህተቱ እንዲስተካከልላቸውና ብሩን ለማስመለስም ልጅ ይዘው ሶስት ቀን ሙሉ ከቢሮ ቢሮ ቢመላለሱም ስህተቱ እስካሁን ድረስ አልታረመላቸውም፤ ለሚጠየቁት ጥያቄም መልስ የሚሰጥ አካል የለም ሲሉ አማረዋል።።

የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ የተንዛዛ በመሆኑንም አገልግሎት ፈላጊው እንደሚጉላላና ጊዜውን ያላግባብ እንደሚያባክን ወይዘሮ ጽጌረዳ ገልጸው፤ አገልግሎቱ ይህን ኋላ ቀር አሰራሩን ማስተካከልና ፈጣን አገልግሎት መስጠት እንደሚጠበቅበት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ትውልደ ኤርትራዊው አቶ ሳሚ ኃይለሚካኤል በበኩላቸው ከሶስት ወር በላይ ጊዜ ያለፈበት ቪዛቸውን ለማሳደስ ቢፈልጉም አሁን አገልግሎቱ ለጊዜው የተቋረጠ በመሆኑና በቴሌቪዥን ማስታወቂያ እስኪነገር ድረስ እየተከታተሉ እንዲጠብቁ ስለተነገራቸው ከቤተሰብ ጋር ለመገናኘት መቸገራቸውን ገልጸዋል።



ወይዘሮ ሂዳያ ዓለሙ



አቶ ከድር ሰዒድ

ከሶስት ወር በላይ ቪዛውን ሳያሳድስ ጊዜው ላለፈበት ሰው በቀን ሶስት ዶላር ቅጣት እንደሚከፍል ጠቁመው፤ ይህ መረጃ ቀድሞ ስላልተነገረን በሚመለከተው አካል እንደገና እንዲታይላቸውም ጠይቀዋል።

ወይዘሮ ሰላም ኪዳነ የተባሉ ተገልጋይ በበኩላቸው የትዳር አገራቸውን ይዘው ወደ አሜሪካን ሀገር ለመሄድ ፕሮሰስ መጀመራቸውን ገልጸው፤ በጋብቻ መረጃው በወቅቱ ባለመታደሱ የጉዞ ቪዛው እየተጓተተባቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በኢሚግሬሽን ዜግነትና ቪዛ አገልግሎት የሰነዶች ምዝገባና አሰጣጥ ዳይሬክተር አቶ ከድር ሰዒድ በበኩላቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ምላሽ፣ በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ወረፋ መብዛቱ አንዱ ምክንያት በኮቪድ፣ በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዩ ጋር ተያይዞ እና ከስደተኞች መብዛት ጋር ተያይዞ የቆዩ ውዝፍ ስራዎች እንደነበሩ ጠቁመዋል።

ተገልጋዩም በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ሳይሆን በአንድ ጊዜ ግር ብሎ የሚመጣ መሆኑ ወረፋውን እያበዛው መሆኑን ጠቅሰው፤ አስቸኳይ ጉዳይ ያላቸው ተገልጋዮች ቀድመው ቢስተናገዱ እና አጣዳፊ ጉዳይ የሌላቸው ዘግይተው ቢስተናገዱ ጫናውን ይቀንሰዋል ብለዋል።

ውዝፉን ስራዎችን ለመቀነስና ሕጋዊና ሕጋዊ ያለሆኑትን የማጥራት ስራም ባለው የሰው ኃይል ከመንግሥት የስራ ሰዓት በተጨማሪ የበዓል ቀናት እና ቅዳሜና እሁድን ጭምሮ አገልግሎት እየተሰጠ እንደሚገኝም አመልክተዋል።

የኢሚግሬሽን ዜግነትና ቪዛ አገልግሎት ለጉዞ የሚያገለግሉ የጉዞ ቪዛ እና አስቸኳይ የጉዞ ሰነድ ብቻ አዘጋጅቶ ይሰጣል ያሉት አቶ ከድር፤ የጋብቻ ሰርተፊኬት፣ እና ሌሎች የወሳኝ ኩነት መረጃ አገልግሎቶችን በተመለከተ የውጭ ዜጎችም ሆነ ኢትዮጵያውያን በአዲስ አበባ እና በክልል መስተዳድሮች ወሳኝ ኩነት ኤጀንሲ በኩል የሚሰጥ መሆኑን ጠቁመዋል።

ለቱሪስት አገልግሎት፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለመንግሥታዊና ለግል ሥራ፣ የሚመጡ የውጭ ዜጎችና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ እንዲሁም በኢንዱትሪ ፓርኮች የመኖሪያ ፈቃድ አገልግሎት እየተሰጠ መቆየቱንም ገልጸዋል።

ይሁንና አገር ውስጥ እንዲገቡ ከተፈቀደላቸው በኋላ ከአንድ ወር በላይ ቪዛቸውን ሳያሳድሱ የቆዩ ሰዎች ያሉበት ሁኔታ እስኪታወቅ ለጊዜው አገልግሎቱን አቁመናል ብለዋል።

ይህም ሆኖ ቪዛቸውን ሳያሳድሱ የቆዩትን እስከ አንድ ወር ጊዜ በመታገስ አገልግሎቱን እየሰጠን ነው። ከአንድ ወር በላይ የቆዩትንም የምዝገባ ጣቢያዎችን በማቋቋም ምዝገባ እንዲያካሄዱ እየተደረገ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በከተማዋ በርካታ ስደተኞች መኖራቸውንም ጠቁመው፤ ከስደተኞች ተቋም ጋር በመሆን የመውጫ ቪዛ እና የመጓጓዣ የጉዞ ሰነድ እየተሰጠ መሆኑንም ገልጸዋል።

የውጭ አገር ዜጎች ቀርበው ምዝገባ እንዲደርጉ እና የት መመዝገብ እንዳለባቸው እና ምን ማሟላት እንደሚገባቸው ከአንድ ወር በላይ በብዙሃን መገናኛዎች መገለጹንም አስታውሰዋል።

የተገልጋዩን እንግልት ለመቀነስም የኢሚግሬሽን ቅርንጫፎች በየክልሎቹ የማስፋፋት ስራ ይሰራል ብለዋል፡፡

ለውጭ ዜጎች የተለያዩ የመኖሪያ ፈቃዶች አገልግሎት እየተሰጡ ቢሆንም ሁሉም የአገልግሎት አሰጣጦች ወደ ኦንላይን አልተቀየረም። ይህም ለአገልግሎት መጓተቱ ምክንያት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በቅርቡ ለውጭ ዜጎች ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃድ በከፊል በኦንላይን የሙከራ አገልግሎት መስጠት መጀመሩን ጠቁመው፤ አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋ የሚያደርግ በመሆኑም በቅርቡ ሙሉ በሙሉ በኦንላይን አገልግሎት የሚሰጥ መሆኑን አመልክተዋል።

ከ2011 ዓ.ም ወዲህ የፓስፖርት አገልግሎትም በኦንላይን መሰጠት መጀመሩን አስታውሰው፤ የትውልደ ኢትዮጵያውያን ጊዜያዊ ቪዛም በኦንላይን ለማድረግ በሙከራ ሂደት ላይ መሆኑንም ጠቁመዋል።

በኢሚግሬሽን ዜግነት እና ቪዛ አገልግሎት የአራት ኪሎ የውጭ ዜጎች ቡድን መሪ ወይዘሮ አልማዝ ሸዋዬ በበኩላቸው፣ አገልግሎቱን ያጓተተው ምክንያት አንደኛው በሕገ ወጥ መንገድ ወደ አገር ውስጥ የሚገባው ስደተኛ መብዛቱ እንደሆነና ሌላኛው ደግሞ ጊዜያዊ የመኖሪያ ፈቃዳቸውን በወቅቱ ሳያሳድሱ የቆዩ የውጭ አገር ዜጎች እንዲመዘገቡ ማስታወቂያ በመነገሩ በአንድ ጊዜ መምጣታቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# በከተማዋ የውሃ ብክነት ለመቀነስ የ696 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የሚስተዋለውን ከፍተኛ የውሃ ብክነት ለመቀነስ የሚያስችልና በዓለም ባንክ የሚደገፍ የ696 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት ትግበራ መጀመሩን ባለሥልጣኑ አስታወቀ:: የከተማዋ ውሃ ብክነት ከ37 እስከ 41 ከመቶ ይደርሳል ተብሏል::

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ውጤትን መሠረት ያደረገ የውሃ ብክነትና ቁጥጥር ፕሮጀክት አስተባባሪ አቶ አልታሰብ አዘዘው በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በመደበኛው የባለሥልጣኑ ሥራ የውሃ ብክነት ለመቀነስ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ሲሆን በዓለም ባንክ የሚደገፍ አዲስ ፕሮጀክት ትግበራ መጀመሩን አስገንዝበዋል::

የከተማዋ አጠቃላይ የውሃ ብክነት ከ37 እስከ 41 ከመቶ እንደሚደርስ ጥናቶች የሚያመለክቱ መሆኑን ያወሱት አቶ አልታሰብ፤ ይህን ብክነት በመቀነስ በመደበኛ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ እየሰራ ነው::

የውሃ ብክነት በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከሰቱ ሲሆን የመጀመሪያው ፊዚካል ብክነት የሚሰኘው፤ የተለያዩ መሠረተ ልማቶች ግንባታዎች ሲከናወኑ በሚሰበር መስመርና እንዲሁም ሌሎች የውሃ መሰረተ ልማቶችና ቧንቧዎችና መስመሮች እያረጁ ውሃ ሲያፈሱ ውሃ ይባክናል:: በተጨማሪም ከተማውም ሰፊ በመሆኑም የውሃ መስመር ሲስተም ማስተካከያ አለመደረጉም ውሃ ይባክናል ብለዋል::



የለገዳዲ ውሃ ፕሮጀክት

ሌላኛው ኮሞርሻል ብክነት የሚሰኘው ደግሞ ውሃው ጥቅም ላይ እየዋለ ገቢ ባለመሰብሰብ የሚከሰት ብክነት መሆኑን የጠቀሱት አስተባባሪው፤ ይህም ሕገ-ወጥ የውሃ መስመር ቅጥያ፣ ዘመናዊ የውሃ ቆጣሪዎችን ሥራ ላይ አለማዋል፤ ተቋማት በወቅቱ የውሃ ቆጣሪ አለመክፈል፣ በውሃ ቆጣሪ ባለሙያ ንባብ እና ዳታ ኢንኮዲንግ አለመናበብ፣ ሕብረተሰቡ የውሃ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ አለመጠቀምን ያካትታል ብለዋል::

በዚህ የተነሳ ከፍተኛ የውሃ ብክነት እየተስተዋለ በመሆኑ ተቋሙ አዲስ ፕሮጀክት ለመተግበር መገደዱን አቶ አልታሰብ አስረድተዋል::

እንደ አስተባባሪው ገለፃ፤ ይህ ፕሮጀክት በለሚ ኩራ እና ጉርድ ሾላ ቅርንጫፎች ለናሙና የሚተገበር ሲሆን 100ሺ ደንበኞችን ተጠቃሚ ያደርጋል:: በዚህ ፕሮጀክትም በቀን 18ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃን ከብክነት ማዳን ይቻላል:: ይህን ፕሮጀክት በሂደት በሌሎች የከተማዋ ክፍሎች ተግባራዊ ይደረጋል::

የፕሮጀክቱ ትግበራ በአሁኑ ወቅት የተጀመረ ሲሆን አራት ዓመት ከሁለት ወር ውስጥ የሚጠናቀቅ ሲሆን፤ ለዚህም 696 ሚሊዮን ብር የወጪ ይደረጋል:: የፕሮጀክቱ ዋነኛ ዓላማው ከ37 እስከ 41 ከመቶ የሚባክነውን ውሃ መቀነስ ነው:: ይህ ለማድረግ ደግሞ አዳዲስ መስመሮችንና ቆጣሪዎችን መቀየር፣ ሲስተም ማስተካከል፣ የውሃ ግፊት ማመጣጠንና ተያያዥ ሥራዎች ይከናወናሉ:: ይህም እንደሞዴል ተወስዶ የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ በሌሎችም ቅርንጫፎች የሚተገበር ይሆናል::

ፕሮጀክቱን የዓለም ባንክ በገንዘብ የሚደግፈው ሲሆን፤ በአፍሪካ እና ሌሎች የዓለማችን ሀገራት ረጅም ልምድ ያዳበረው ‹‹ሚያ›› የተባለው የአውሮፓ ኮንትራክተር ሥራውን የሚያከናውን ይሆናል:: ባለሥልጣኑ ደግሞ ፕሮጀክቱን በዋናነት የሚያስተዳድር ሲሆን፤ አስፈላጊ መረጃዎችንም በወቅቱ ይሰጣል::

ከአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን የተገኘው አሃዛዊ መረጃ እንደሚያመለክተው፤ ባለሥጣኑ በአሁኑ ወቅት በቀን 700ሺ ሜትር ኪዩብ ውሃ እያመረተ ለደንበኞች የሚያቀርብ ሲሆን፤ ዕለታዊ የከተማዋ ፍጆታ ግን 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ውሃ ነው:: ይህ በእንዲህ እንዳለ የከተማዋ ውሃ ብክነት ከ37 እስከ 41 ከመቶ ደርሷል:: በተጨማሪም ከሚመረተው ውሃ 25 ከመቶ የሚሆነው በመብራት መቆራረጥ የተነሳ ይባክናል::



# በ600 ሚሊዮን ብር ወጪ የተገነባው የቪታ ውሃ ፋብሪካ ተመረቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከ600 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ በጀት በሶማሌ ክልል ሺኒሌ ወረዳ መርማርሳ ቀበሌ የተገነባውን የቪታ ውሃ ማምረቻ ፋብሪካን ርዕሰ መስተዳድሩ አቶ ሙስጠፌ ሙሀመድ መርቀው ሥራ አስጀምረዋል።

ትናንት የተመረቀው ፋብሪካ የቪታ ውሃ የማስፋፊያ ፕሮጀክት ሲሆን፤ ከድሬዳዋ ወጣ ብሎ በሲቲ ዞን በሺኒሌ ወረዳ መርማርሳ በሚባለው ሰፈር የተገነባ ነው:: የፋብሪካው የማምረት አቅሙ ከመጀመሪያው ፋብሪካ በአምስት እጥፍ የሚበልጥ ነው ተብሏል።

የፋብሪካው ባለቤት አቶ አብዲ አራብ ፋብሪካው ከ500 በላይ ለሚሆኑ ሰራተኞች የስራ ዕድል እንደፈጠረ ጠቁመዋል:: በቀን 50 ሺህ ደርዘን ውሃ የማምረት አቅም እንዳለው እና ከምርቱ 40 በመቶውን ወደ ጎረቤት ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት መታቀዱንም በምርቃት ሥነሥርዓቱ ላይ ተናግረዋል።




# ለ100 ሺህ ዜጎች ነጻ የጤና ምርመራ እና የህክምና አገልግሎት ዘመቻ ሊካሄድ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የጤና ሚኒስቴር እየሰጠ ባለው የክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ችግኞችን ከመትከል እና የአቅመ ደካማ ቤቶችን ከማደስ ባለፈ "በጎነት ለጤናችን" በሚል መሪ ቃል መቶ ሺ ለሚሆኑ ዜጎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ነጻ የጤና ምርመራ እና የህክምና አገልግሎ ዘመቻ ከዛሬ ጀምሮ ሊያካሂድ መሆኑ ተገለጸ፡፡

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ በሰጡት መግለጫ እንዳመለከቱት፤ ዘመቻው በጎ ፍቃደኛ ባለሙያዎችን፣ የግል እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት እና የመንግሥት ጤና ተቋማትን በማስተባበር ከዛሬ ጀምሮ ለአንድ ሳምንት እንደሚሰጥ አስታውቋል፡፡

ለዚህም በየደረጃው የዝግጅት ስራ እየተሰራ ይገኛል ያሉት ዶክተር ሊያ በዚህ ዘመቻ ተደራሽ የሚሆኑት የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይም የመክፈል አቅም የሌላቸው አቅመ ደካማ ዜጎች፣ የጎዳና ተዳዳሪዎችና ሌሎች ተጋላጭ ሕብረተሰባችን ክፍሎች መሆናቸውን ተናግረዋል።

በዚህ ዘመቻ በተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች የተጠናከረ የጤና አጠባበቅ ትምህርትና ምክር አገልግሎት፣ የኮሌራና ሌሎች ውሃ ወለድ ተቅማጥ በሽታዎች፣ ወባ፣ ኤች አይ ቪ ፣ ቲቪ ፣ ኮቪድ-19፣ የካንሰር ህመምና ሌሎች ትኩረት በሚሹ የጤና ጉዳዮች ማለትም የደም ግፊት ፣ የደም የስኳር መጠን፣ ከአንገት በላይ፣ የአይን፣ የቆዳ፣ የሥነ ምግብ፣ አእምሮ ጤና ሌሎችም የጤና አገልግሎቶች እንደሚሰጡም ሚኒስትሯ ተናግረዋል፡፡

በምርመራው ወቅት ከፍተኛ ህክምናና ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች ወደሚመለከታቸው የጤና ተቋማት እንደሚላኩና ተጨማሪ አገልግሎት እንዲያገኙ እንደሚደረግ የገለጹት ሚኒስትሯ፤ ይህ ዘመቻ የጤና አገልግሎትን ከመስጠት ባለፈ የሕዝባችንን የጤና ንቃት ለማሳደግና የመረዳዳት ባህላችንን የበለጠ ለማሳደግ የራሱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ያላቸውን እምነት ገልጸዋል፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት በጤና ሚኒስቴር፣ ተጠሪ ተቋማትና በክልሎች እስከ ወረዳና ቀበሌዎች ድረስ ሕብረተሰቡን በማስተባበር የተለያዩ የክረምት በጎ ፍቃድ ስራዎች በስፋት እየተከናወኑ ይገኛሉ ያሉት ዶክተር ሊያ፤ በዚሁ መሰረት የጤና ሚኒስቴር የተለያዩ የበጎ ፍቃድ ስራዎችን በተለይም የችግኝ ተከላ፣ የከተማ ግብርና የአቅመ ደካማ ቤቶችን ማደስ እና ለአቅመ ደካማ ቤተሰብ ተማሪዎች የትምህርት ቁሳቀሶችን የማሰባሰብና የመሳሰሉት ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙም ከጤና ሚኒስቴር ድረገጽ የተገኘው መረጃ አመላክቷል፡፡



# የክልሉ ግብርና ዘርፍ ላይ የደረሰውን ጉዳት ስማካካስ ርብርብ እየተደረገ መሆኑ ተገለጸ

**- ሕወሓት በፈጸመው ወረራ ከ341 ቢሊዮን ብር ጉዳት መድረሱ ተገልጿል**

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት በወረራ ይዟቸው በነበሩ የአማራ ክልል አካባቢዎች የደረሰውን ከፍተኛ ጉዳት ለማካካስ ከፍተኛ ርብርብ እየተደረገ መሆኑን የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ አስታወቀ:: በወረራው ምክንያት በግብርናው ዘርፍ ብቻ ከ 341 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት ጉዳት መድረሱን ቢው ጠቁሟል::

የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ ዶክተር አልማዝ ጊዜው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአማራ ክልል አሸባሪው የሕወሓት ቡድን ወረራ ይዟቸው በነበሩ አካባቢዎች ቢሮው ባደረገው የዳሰሳ ጥናትም በግብርናው ዘርፍ ላይ ከ341 ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት የሰብዓዊ፣ ቁሳዊና የተቋማት ጉዳት ደርሷል:: ከፍተኛ ጉዳት ከደረሰባቸው ተቋማት መካከልም ከፍተኛ ወጪ የተደረገባቸው የምርምር ተቋማት ቤተ ሙከራዎች፣ አነስተኛ መስኖ መሰረተ ልማቶችና የአደጋ ጊዜ የእህል ማከማቻ መጋዘኖች ይገኙበታል ::

ከወረራው ከተቀለበሰ በኋላ ቢሮው ለመልሶ ማቋቋም እንዲረዳው የደረሱ ጉዳቶች ምን ያህል ናቸው፣ በምን መልኩ ልንገነባቸው እንችላለን የሚል የዳሰሳ ጥናት ተሰርቷል ያሉት ዶክተር አልማዝ፤ በመልሶ ግንባታ ላይም ከዩኒቨርሲቲዎች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት፣ ከባለሀብቶችና ማሕበረሰቡ ጋር ተከታታይ ውይይቶች ተደርገዋል ብለዋል::

ግብርና ቢሮውና ተጠሪ ተቋማቱ ለዘመናት የተገነቡ እንደመሆናቸው የደረሰውን ጉዳት በአንድ ጊዜ መመለስ ስለማይቻል የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ስትራቴጂክ እቅዶች መዘጋጀታቸውንም ያስታወሱት ምክትል ቢሮ ኃላፊዋ፤ በዚህም ቢሮዎችን መልሶ የማደራጀት፣ ለአርሶ አደሮች አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ ወደ መደበኛ ሥራ እንዲገቡ የማገዝ ሥራ ተሠርቷል ብለዋል::

ለአርሶ አደሮችም ዘርና የእርሻ መሳሪያዎችን ከማቅረብ በተጨማሪ የሚያርሱበት በሬ ለሌላቸውም በሬና ትራክተር በኪራይ እንዲያገኙ መደረጉን ጠቁመው፤ ሁሉም የሚታረሱ መሬቶችን በዘር ለመሸፍን ርብርብ በመደረጉ ክልሉ ላይ የተሰጋው የረሃብ አደጋ እንዳይከሰት ማድረግ ተችሏል ብለዋል::

ከፌዴራል መንግሥቱ ጋር በተደረጉ ውይይቶች ጉዳት የደረሰባቸውን ቢሮዎችና ተቋማት መልሶ ለማደራጀት የሚያስችሉ ቁሳቁሶችና 54 መኪናዎች እገዛ መገኘቱን አስታውሰው፤ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ባለሀብቶችና ማሕበረሰቡ ለቀረበው ጥሪ ምላሽ በመስጠት ከፍተኛ እገዛ ማድረጋቸውን ተናግረዋል::

ቢሮው ለግብረ ሰናይ ድርጅቶች የደረሰውን ጉዳት ለማስረዳትና ድጋፍ እንዲያደርጉ ሰፊ ሥራ መሥራቱን የጠቆሙት ዶክተር አልማዝ፤ የተወሰኑ ድጋፎች ቢኖሩም ከሚጠበቀው አንጻር አነስተኛ መሆኑን ጠቁመዋል::

እስካሁን ድረስ ዘርፉን ለመገንባት የነበረው እንቅስቃሴ ከሌሎች ዘርፎች አንጻር አነስተኛ እንደነበር አመልክተው፤ ለመልሶ ግንባታ ከሚያስፈልገው ሀብት ውስጥም 30 በመቶው ብቻ ተገኝቷል ሲሉም ጠቁመዋል:: የክልሉ ነባራዊ ሁኔታ እየተሻሻለ በመምጣቱ አሁን ላይ ለመልሶ ግንባታው የተለያዩ ተቋማት ለመሳተፍ ፍላጎት እያሳዩ መሆኑንም ገልጸዋል::

ለመልሶ ግንባታው ድጋፍ ላደረጉ ባለድርሻ አካላት ምስጋናቸውን አቅርበው፤ የግብርናው ዘርፍ መነቃቃት ለክልሉ ብሎም ለአገሪቱ አጠቃላይ እድገት ያለው ሚና ከፍተኛ በመሆኑ የደረሰውን ጉዳት ለማካካስ የሚደረገው ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ዶክተር አልማዝ ጥሪ አቅርበዋል::

ዜና

# ከግድቡ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን ተጨማሪ የዝግጅት ሥራዎችን ማከናወን እንደሚገባ ተጠቆመ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ከታላቁ የህዳሴ ግድብ ይበልጥ ተጠቃሚ ለመሆን ከወዲሁ በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ የዝግጅት ሥራዎችን ማከናወን ያስፈልጋል ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በረኸተስፋ ገለጹ።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ከዓባይ ግድብ የበለጠ ተጠቃሚ እንድትሆን ከወዲሁ በቱሪዝም ዘርፍ ብቁ የሰው ኃይል ማሰማራት፣ የግድብን ኤሌክትሪክና የአካባቢውን ግብዓት የሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋትና የሰላምና ደሕንነት ሥራዎችን ማጠናከር ያስፈልጋል።

ዓለም በአካባቢ ብክለት በሚታመስበት እንዲሁም በኤሌክትሪክና በጋዝ ኃይል እጥረት በሚቸገርበት ወቅት እኛ ከታላቁ ህዳሴ ግድብ አካባቢን የማይበክል የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘታቸው ትልቅ ውጤት ነው። ውጤቱን ለማሳደግ ደግሞ የአካባቢውን ሰላምና ደሕንነት የበለጠ እያስጠበቁ ለኢንዱስትሪዎችም ሆነ ለቱሪዝም ልማቱ ዕድገት የሚረዱ ዝግጅቶችን በተቀናጀ መልኩ ከወዲሁ ማከናወን ይገባል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ገለጻ፤ ለአብነት በቱሪዝም ዘርፉ ማየት ቢቻል ግድቡ ሲጠናቀቅ ለውሃ ላይ መዝናኛና



ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ

ለሆቴል ኢንዱስትሪዎች ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። በመሆኑም በቱሪዝሙ ዘርፍ የውጭውንም ሆነ የአገር ውስጡን ጎብኚ መሳብ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን በመንደፍና አስፈላጊው የሰው ኃይል በመመደብ ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚህ ባለፈ የቱሪዝም፣ የግብርና፣ አሳ ሀብት፣ የኢንዱስትሪ እንዲሁም ሌሎች የሕዝብን ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊና መስተጋብሮች የሚያሳድጉ ክንውኖችን ከሰላምና ደሕንነት ስራው ጋር ማስተሳሰር የሚችሉ ብቁ የሕዝብና የልማት አስተዳደር ባለሙያዎችን ማሰማራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ባለሙያዎቹም አገራዊ ግብና ራዕይን ይዘው እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ የአካባቢውን ዕምቅ ሀብት ለተገቢው ጥቅም የሚውልበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል ብለዋል።

ከሰው ኃይል ዝግጅት ባለፈ ደግም የግድቡን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ለማሳደግ በአካባቢው ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት ያስፈልጋል ያሉት ባለሙያው፤ በተለይም ኢትዮጵያ ወደኢንዱስትሪ ለምታደርገው ሽግግር አስፈላጊ የሆኑና ከአግሮ ኢንዱስትሪው ጋር የተያያዙ ፓርኮችን በአካባቢው በመገንባት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

በተለይ የአሳ ሀብትና ግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎችን በመገንባት ኤሌክትሪኩንም ሆነ የፋብሪካ ግብዓቶቹን በአቅራቢያው እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪ የአካባቢው የቀርከሃ ሀብትና የማዕድን ሀብቶች የተሻለ ገቢ እንዲያመጡ በቦታው ያለውን ምቹ የኃይል አቅርቦት በማሳወቅ ኢንቨስተሮች ወደሥራ እንዲገቡ የሚያስችል ጥረት ከወዲሁ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

በሌላ በኩል ደግም የግድቡን ኃይል ዘላቂነት ባለው መልኩ ለሚፈለገው ጥቅም ለማዋል የአካባቢው ሰላምና ደሕንነት ማጠናከር ያስፈልጋል። ግድቡ በድንበር አካባቢ እንደመሆኑ ከሕብና የጸጥታ ተቋማት ጋር በትብብር የሚከናወኑ ስራዎች ዘመኑን በዋጅ መልኩ እየጎለበቱ መሄድ አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንዳስታወቁት፤ የተጠናከረ የሰላምና ደሕንነት ስራው በኋላም በአካባቢው ሊገነቡ የሚችል ፋብሪካዎች በተመቻቸ ሁኔታ እንዲያመርቱ የሚያግዝ በመሆኑ፤ እንደእስካሁኑ ሁሉ የሰላምና ደሕንነት ስራው ሕዝብን ባሳተፈ መልኩ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባል።

በተለያዩ ተጽዕኖዎች ውስጥ ሆነንም ቢሆን ግድቡን መገንባት መቻቻችን በእራሱ የሚሰጠን የመንፈስ ጥንካሬም አለ ያሉት ባለሙያው፤ ያንን ጥንካሬ ተጠቅመን በቀጣይም የአገራችንን ሰላም መጠበቅ አለብን። ይህም ከግድቡ የሚገኘውን ኃይልና የአካባቢውን ዕምቅ ሀብት በመጠቀም የአገርን የኢኮኖሚ እንድናሳድግ ይረዳናል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ከሆነ፤ በአጠቃላይም በሰላምና ጸጥታው፣ በሰው ኃይልና በኢንዱስትሪ ዘርፎች አስፈላጊው ዝግጅት ከተከናወነ የዓባይ ግድብ የሚገኝበትን አካባቢ ለኢትዮጵያውያን የሚበጅ ልዩ የልማት ቀዬ ማድረግ ይቻላል።

## ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ብሔራዊ ባንክ እንዲገባ በማድረግ ሀገራዊ ግዴታቸውን እንዲወጡም አቶ አሻድሌ አሳስበዋል፡፡

የክልሉ ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ዋና ዳይሬክተር አቶ ናስር መሐመድ በበኩላቸው፤ ማሽኑ ሥራ መጀመሩ በክልሉ የማዕድን ዘርፉን ለማዘመን እየተደረገ ያለውን ጥረት ያግዛል ብለዋል፡፡ ማሕበሩ ከኬሚካል ነጻ ማሽን መጠቀም መጀመሩ ለትውልድ እንደሚያስብ ማሳያ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

ከልዩ አነስተኛ ጀምሮ ዘመናዊ ወርቅ ማምረት ወደመጠቀም እየተደረገ ያለው ሽግግር ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባውም አስረድተዋል፡፡

የመንጌ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ ኢብራሒም መንሱር፣ ባለፉት ዓመታት በወረዳው ያለው ወርቅ ሀብት የአካባቢው ማሕበረሰብ በአግባቡ ሳይጠቅም መቆየቱን ጠቁመው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ወጣቶችን ጨምሮ የወረዳው ማሕበረሰብ መጠቀም መጀመሩን ተናግረዋል፡፡

መሠል ዘመናዊ የወርቅ ማምረቻ ማሽኖችን በማስፋት ወርቅ ምርቱን ከማሳደግ ባሻገር ሕገ-ወጥ ዝውውሩን መቆጣጠር እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

የቤኒሻንጉል ማዕድን ዘርፍ ልማት ማሕበር ስራ አስኪያጅ ሸህ ሱዑድ አብዱላሂ፣ ወርቅ ማምረቻ ማሽኑ ሙሉ በሙሉ ከኬሚካል ብክለትና ተጽዕኖ ነጻ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ማሕበሩ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2026 በክልሉ ብሎም በሀገሪቱ ተጽዕኖ ፈጣሪ የማዕድን አማካሪ ለመሆን እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመው፣ በተለያዩ ወረዳዎች ቅርንጫፎችን ከፍቶ እንደሚሠራም አስረድተዋል፡፡

## "በግድቡ ሳቢያ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አምባሳደር ዲና በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ የያዘችው የጋራ ትብብር ያልተዋጠላቸው ግብጽና ሱዳን በኢትዮጵያ ላይ ብርቱ ጫና ለማሳረፍ ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም።

ዳሩ ግን ኢትዮጵያውያን በየፊናቸው ባደረጉት እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ ከብዙ ውጣ ውረድና ፈታኝ ሁኔታ በኋላ ሶስተኛ ዙር የውሃ ሙሌት መከናወኑ ትልቅ ድልና አንገትን ቀና የሚያደርግ ክስተት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ግድቡ የትብብር እንጂ የንትርክ ምንጭ እንዳይሆን ብዙ ጥረት እያደረገች መሆኑን የገለጹት አምባሳደሩ፣ በተቃራኒው ወገን ግን ምንም እንኳ ግድቡን ማስቆም ባይችሉም ኢትዮጵያ ላይ የተለያዩ ጫናዎችን ከማድረግ ወደኋላ እንደማይሉ ብዙ ማሳያዎች መኖራቸውን አስገንዝበዋል።

ኢትዮጵያ ወንዙን በማልማት ሕዝቦቿን ከጨለማ ለማላቀቅ የምታደርገውን እንቅስቃሴ በተለይ ግብጽ እንደ ጉዳት በመቁጠር የዓለም አቀፉን ማሕበረሰብ እያደናገረች እንደምትገኝ የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፣ ለወንዙ 86 በመቶ የውሃ ድርሻ የምታበረክተው ኢትዮጵያ ግን እያደረገች ያለው ጥረት የታችኛው ዓባይ ተፋሰስ አገሮች በጎርፍ እንዳይጎዱ ከማድረጉም በላይ በኤሌክትሪክ አቅርቦት የጋራ ተጠቃሚነትን እንደሚያረጋግጥ ስትገልጽ መቆየቷን አውስተዋል።

የነበሩ ጫጫታዎችና መደናገሮች በተለይ ከ3ኛ ዙር የውሃ ሙሌት በኋላ መቀነሱ በአንድ በኩል በሁሉም ተቃዋሚ ሃይሎች ዘንድ የግድቡ ሥራ ወደኋላ እንደማይቀለበስ ከማመን የተነሳ ቢመስልም በሌላ በኩል ደግሞ የግብጽ ዋና አጋሮች ጭምር ዓለም እንደ ዩክሬንና ታይዋን ያሉ አንገብጋቢ አጀንዳዎች በመጠመዱ ምክንያት መሆኑን የተናገሩት አምባሳደር ዲና፣ ይህ ማለት ግን በጉዳዩ ተስማምተዋል ማለት እንዳልሆነና ነገ ግድቡ ተመልሶ አጀንዳ መሆኑ አይቀሬ በመሆኑ በሁሉ ረገድ ትንፋሽ በመሰብሰብ መዘጋጀት ያስፈልጋል ብለዋል።

በአንድም ይሁን በሌላ በውስጥም ሆነ በውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ላይ የሚሰነዘረው ጥቃት ሲጠቃለል ከህዳሴው ግድብ ግንባታና ከአገሪቱ እድገት ጋር የሚያያዝ መሆኑን የገለጹት አምባሳደሩ፣ ወደ እድገት የሚደረገው ጉዞ ሁሌም ፈታኝና አድካሚ በመሆኑ ከሁሉም በላይ የውጭውን ጫና ለመቀነስ የውስጥ አንድነት ማጠናከር ወሳኝ መሆኑን መክረዋል።

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፣ ግብጽ በቀና ከተገነዘበች ግድቡ በተመጣጣኝ ዋጋ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት እንድታገኝ ያስችላታል። በየዓመቱ የታችኛው የዓባይ ተፋሰስ የራስ ምታት የሆነውን የጎርፍ አደጋ ለመከላከልም የግድቡ ፋይዳ የጎላ ነው። የቀጠናውን አገሮች በማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ለማስተሳሰር ትልቅ አቅም አለው። ስለዚህ ለግብጽም ሆነ ለሱዳን የሚያዋጣው የጋራ ተጠቃሚነት መርህን መከተል ብቻ ነው።

በአንጻሩ ኢትዮጵያ የሚሰነዘርባትን ማንኛውም ኢ-ፍትሐዊ ትንኮሳዎች ለመግታት በዲፕሎማሲያዊ፣ በወታደራዊ አቅምና በውስጥ አንድነት ራሷን ማጠናከር ይጠበቅባታል ብለዋል፡፡

## ‹‹ወጣቶች ከተደመሩና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የመንግሥት የልማት ፕሮጀክቶች በርካታ ወጣቶች የስራ ዕድል ማግኘታቸውን በማስታወስ፤ ወጣቶች ከእነዚህ ተነስተው ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል፡፡

ኢትዮጵያ ብዙ ፈተናዎች ቢያጋጥማትም ተቋቁማ ብዙ አኩሪ ውጤቶችን ማስመዝገቧን ጠቁመው፤ ከእነዚህ መካካልም አረንጓዴ አሻራ፣ በበጋ ስንዴ፣ በመከላከያና በጸጥታ ተቋማት የተሰሩ የሪፎርም ስራዎች እንደሚገኙበትም ጠቅሰዋል፡፡

የኢትዮጵያን ሰላም የሚያምሱ ሶስት አይነት ሰዎች ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስተር ዐቢይ፤ አንደኛዎቹ ራሳቸው ሳይነቁ ሰው ላንቃ የሚሉና ሁሌም መፍትሄን ሳይሆን ችግርን የሚተነትኑ፤ ሁለተኞቹ ደረጃ የሚቀመጡት አላዋቂን እንደ አዋቂ ቆጥረው እነዚህን የሚከተሉ፣ በሶስተኛ ደረጃ የሚቀመጡት ደግሞ በሰፈር ጅላጅል የሚከተሉና የሚነዱ ዓላማና ግብ የሌላቸው ልክ እንደ ተጎታች ተሸከርካሪ የሚቆጠሩ ናቸው ብለዋል፡፡

ወጣቶች ከነዚህ ራሳቸውን በማራቅ ለአገራቸውና ለራሳቸው በሚጠቅም ስራ ላይ መጠመድ እንደሚኖርባቸው መክረዋል፡፡ የራሳቸውን ትናንትና በከንቱ አባክነው የወጣቶችን የዛሬ ጊዜ የሚቀሙ ፖለቲከኞችን ዞር በሉ ማለት ያስፈልጋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ አቧራ ከሚያስነሳ ፖለቲካ አሻራ ወደሚያኖር ፖለቲካ መቀየር ይኖርብናል ብለዋል፡፡

አሸባሪው ሕወሓትና ሸኔ በውጭ ሃይል ድጋፍ ኢትዮጵያን ለማተራመስ ያልፈነቀሉት ድንጋይ እንደሌለ ገልጸው፤ ሁሌም እውነትና ኢትዮጵያዊነት እንደሚያሸንፍ ጥርጥር የለንም ሲሉ ገልጸዋል፡፡ እንደ ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ የትግራይ ሕዝብም ሰላምና ልማት ፈላጊ ነው ያሉት ጠቅላይ ዐቢይ፤ ሕወሓት በያዘው ቆሞ ቀር ሀሳብና የጦርነት አባዜ ተጎጂ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

ከእንግዲህ በኋላ አሸባሪው ሕወሓት የፈለገው ድጋፍ ቢያገኝ ማሸነፍ እንደማይችል አረጋግጠው፤ መንግሥት ሁሉንም ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ቁርጠኛ ነው፤ ምክንያቱም ውጊያ ኋላቀርነትና ውድመትን ስለሚያስከትል ብለዋል፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ መንግሥት ለሰላም ባለው ቁርጠኝነት የተናጠል ተኩስ አቅም አድርጓል፡፡ መከላከያ ወደ ትግራይ ክልል እንዳይገባ ወስኗል፤ ሁሌም የሰላም ውይይት ለማድረግ ዝግጁ ነው፡፡

አሸባሪው ሸኔ የኦሮሞን ሕዝብ አይወክልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የኦሮሞን ገበሬ እየገደለ ኦሮሞን እወክላለው ማለት ሞራል እንደሌለው ያሳያል ብለዋል፡፡ ከሸኔ ጀርባም ብዙ የውጭ ጠላቶች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ የኦሮሞ ሕዝብ ከጸጥታ ሃይሎች ጋር በመተባባር ሊታገለው ይገባል ብለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ የማንነት፣ የአደረጃጀትና የልማት ጥያቄዎችም መንግሥት ደረጃ በደረጃ እየፈታቸው እንደሚሄድም ጠቁመዋል፡፡ መላው የኢትዮጵያ ወጣቶች ኢትዮጵያ ያሏትን የተፈጥሮ ሀብቶች በመጠቀም ለመበልጸግ የሚደረገው ጥረት ግንባር ቀደም ተሳታፊ መሆን እንደሚኖርባቸው አሳስበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ ከሁሉም አካባቢዎች ከተወከሉ ወጣቶች በርካታ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ተነስተውላቸው ሰፋ ያለ ማብራሪያና ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ወጣቶቹ ላለፉት ሦስት ቀናት በመዲናችን አዲስ አበባ የተከናወኑ የልማት ስራዎችንና በፌዴራልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያሉ የተለያዩ ተቋማትን መጎብኘታቸውን ገልጸው፤ በአዲስ አበባ ቆይታቸው በተመለከቱት የስራ እንቅስቃሴ አድናቆታቸውን ገልጸዋል፡፡ በጉብኝቱም በርካታ ልምድና ከፍተኛ መነሳሳት ያገኙበት በመሆኑ ወደ መጡበት አካባቢ ሲመለሱ በየተሰማሩበት የስራ መስክ የሚገለገሉበትና ለሌላው ወጣት የሚያካፍሉት መሆኑን በአስተያየታቸው ገልጸዋል፡፡

በሀገራችን የመጣውን ለውጥ ተከትሎ መንግሥት እያደረገ ያለውን የሪፎርምና የሰፋፊ ልማት እንቅስቃሴዎችን ከመስማት ባለፈ በአካል ተገኝተው ስራዎችን በተጨባጭ በመገንዘባቸውና ሀገሪቱ በህልውና ማስከበር ዘመቻ ውስጥ ሆና ጭምር ያከናወነችው በመሆኑ የይቻላል መንፈስ እንደፈጠረባቸው በውይይቱ አንስተዋል፡፡

በተመሳሳይ ወጣቶቹ ለጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ የሀገሪቱን የሰላምና የፀጥታ፣ የመሰረተ ልማትና እድገት፣ ወጣቱ ከሽብርተኞች ጋር በመዘናጋትም ይሁን ባለማወቅ እያደረገ ያለውን ተሳትፎ፣ የቱሪዝም ልማት ማሳደግ፣ የሀገሪቱን ዲፕሎማሲ፣ በከተሞች ውስጥና በመንገዶች ላይ የሚደረግ ዝርፊና ፀረ ሰላም እንቅስቃሴ፣ በተለያዩ አካባቢዎች እየተነሱ ያሉ የአደረጃጀት ጥያቄዎች፣ የወጣቶች የስፖርት ማዘውተሪያ ማዕከላት እና በርካታ የልማትና መልካም አስተዳደርን የተመለከቱ ጉዳዮች በጥያቄ ተነስተው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ማብራሪያና ምላሽ ሰጥተውባቸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአሸባሪው ሕወሓት አመራሮች ሰሞናዊ መግለጫ የሰላም መንገዱን ለማደናቀፍ ያላቸውን ፍላጎት ማሳያ ነው!

ሰላም ለሀገራችን ያለውን እጅግ የጎላ ፋይዳ በመረዳት መንግሥት ከሁሉ ነገር ቅድሚያ ለሰላም ሰጥቶ ስለሰላም በመስራት ላይ ይገኛል። ስለልማት፣ ዕድገትም ሆነ ብልጽግና ለማውራት ሰላም አጅጉኑ ያስፈልጋል። ሰላም ከጠፋ እንኳንስ ስለዕድገትና ልማት ሊወራ በሰላም ውሎ መግባትም እጅግ ከባድ ይሆናል።

ይህንን እውነታ በሀገራችን በተለያዩ ጊዜያት ከደረሱ የሰላም መደፍረሶችና በዓለም ላይ በሰላም እጦት እጅግ ወድ ዋጋ የከፈሉ ሀገራትን ሁኔታ በመመልከት በቀላሉ መረዳት ይቻላል። በሰላም ላይ ብቻ አተኩሮ የሚሰራ የሰላም ሚኒስቴር የተባለ ተቋም የተመሰረተውም ከዚሁ እውነታ በመነሳት ነው።

ከዚህ አንጻር በመላ ሀገሪቱ ሰላምን ለማስፈን የሚያስችሉ የጸጥታ ተቋማትን የማዘመንና በቴክኖሎጂ አቅም የማሳደግ እንዲሁም ሕዝብ የሰላሙ ዋነኛ ዘብ እንዲሆን የማድረግ ተግባራት ተከናውነው ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተመዝግበዋል።

ድህረ ለውጥ የሀገርን ሰላም ለማረጋገጥ ሲባል የዴሞክራሲ ምህዳሩን የማስፋት፣ የልዩነትና የግጭት ትርክቶችን የማክሰምና ሕብረብሄራዊ አንድነትን የማጠናከር ሥራዎች በስፋት ተሰርተዋል። ይህ በሆነበት ሁኔታ የዝርፊያና የፈላጭ ቆራጭነት መንገዱ የተዘጋበት አሸባሪው ሕወሓት በመጀመሪያ ተላላኪዎችን በመጠቀም በኋላ በግልጽ በራሱ ፈጻሚነትን የሀገርን ሰላምና ህልውና የሚጎዳ ተግባርን ፈጽሟል።

ይህ ቡድን ከዚህ የጥፋት መንገዱ እንዲመለስና የትግራይ ሕዝብም እንደሌሎች እህት ወንድሞቹ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ልቡና አቅሙ ወደ ልማት እንዲገባ መንግሥት ከግጭቱ መከሰት አስቀድሞ በርካታ የሰላም ዕድሎችን ፈጥሯል። የኢትዮጵያ እናቶች እንባቸውን እያፈሰሱ ግጭትና ጦርነት ለማንም አይበጅም ወደሰላም መንገድ ተመለሱ ሲሉ ብዙ ለምነዋል።

የሽብር ቡድኑ ሀገር በሚጠብቀው የሰሜን ዕዝ ላይ ክህደት ፈጽሞና ከጀርባ ወግቶ በተቀሰቀሰው ጦርነትም መካከል ለሰላም የተሰጠው ዕድል ተደጋጋሚ ነበር። አሁንም በተለይም የትግራይ ሕዝብ እንዳይጎዳ በማሰብ መንግሥት ከተናጠል የተኩስ አቁም ስምምነት ጀምሮ እስከሰላም ንግግሩ ብዙ ርቀት ተጉዞ ለሰላም ዕድል እየሰጠ ነው። ያለምንም ቅድመ ሁኔታም በየትኛውም ጊዜና ቦታ የሰላም ንግግር ለማድረግ ወስኖ አስፈላጊውን ዝግጅትም አድርጓል። መንግሥት ለአፍሪካዊ ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ በሚል የጸና አቋሙ የሰላም ደርድሩ በአፍሪካ ሕብረት ጥላ ስር እንዲሆንና ሕገ መንግሥቱን ባከበረ መልኩ መከናወን እንዳለበት ጽኑ አቋም ይዞ ለዚሁ ተግባራዊነት ተጨባጭ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው።

ከዚህ በተቃራኒው ይህ የሽብር ቡድን ለሰላም የሚዘረጉ እጆችን በክፋትና በሴራ ለመቁረጥ፤ ለፍቅር የተከፈቱ ልቦችን በጥላቻና መከፋፈል ድርሰት ለመድፈን፤ ለሰላም የተለቀቁ ርግቦችን በጥይት አሩር እየለቀመ ለመጣል በማሰብ የሰላምን መንገድ ለማደናቀፍ ሲንቀሳቀስ እየታየ ነው። የአሸባሪ ቡድኑ አመራሮች የአፍሪካ ሕብረትን የሰላም ጥረት በማጣጣል ብሎም የእነሱ የጥፋት ጦርነት ላይ የሚሳተፍና የማይሳተፍ የትግራይ ተወላጅ መካከል ልዩነት አለው ወዘተ በማለት የሚሰጡት መግለጫ አሁንም የሰላም ዕድሉን አጨልመው ለጥፋትና ለጦርነት እየተዘጋጁ መሆኑን ያመላክታል።

ይህ ሂደት ምናልባት ለሽብር ቡድኑ ሌላ ራሱን ማቆያ መንገድ መስሎት፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ሰላም ነስቶ ሃሳቡ ሰምሮለት የሚመኘውን አገኝበታለሁ ብሎ ያሰበው ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ሰላምን ገፍቶ ጦርነትን መምረጡና ለዚህም አታሞውን መጎሰም መጀመሩ፣ የሽብር ቡድኑን ሰላም ጠልነትን ብቻ ሳይሆን፤ የመጥፊያ ጊዜውን በራሱ ጊዜ እያፋጠነ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ስለ በጎነት ተዘርግተው የደሙ እጆች፣ ስለ ፍቅር ተከፍተው እንዲዘጉ የተገደዱ ልቦች፣ ስለ ሰላም ደጅ ጠንተው ሰሚ ያጡ የሰላም መልዕክቶች ከመገፋትና መከፋታቸው ማግስት የሚፈጠሩት ሕብረትና ኃይል የየትኛውንም ቡድን ቅስም ለመስበር፣ ሞቱንም ለማፋጠን እጅጉን የበረቱ መሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል፡፡ ለዚህም ነው የአሸባሪው ሕወሓት ተደጋጋሚ የሰላም ጥሪዎችን መግፋት፤ ሰላምን ገፍቶ የጦር ነጋሪትን መጎሰምና ጦርን ለውጊያ ማዘጋጀቱ ውድቀቱን የሚያፋጥን ብቻ ሳይሆን፤ የቡድኑን መጥፋት እውን የሚያደርገው ጉዞ የመጨረሻው መጀመሪያ መሆኑ አይቀሬ ነው የሚባለው፡፡

ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ቡድኑም ራሱን ማትረፍ የሚችለው በጦርነት ሳይሆን በሰላማዊ መድረክ መሆኑን ሊገነዘብ፤ በግድም ይሁን በውድ የሽብር ቡድኑ መጠቀሚያ ለመሆን የተዘጋጁ ኃይሎችም የሚያተርፉት ዓላማ ከሌለው ጦርነት ሳይሆን ከሰላምና በፍቅር አብሮ ከመኖር መሆኑን አውቀው ነፍጣቸውን ጥለው ወደሰላም ሊጓዙ፤ ዓለምአቀፍ ኃይሎችም በኢትዮጵያ የሰላም መንገድን ዘግቶ ጦርነትን እያወጀ ያለውን ኃይል ከዚህ የጥፋት ተግባርህ ታቀብ በማለት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# በዓባይ ዳግም የተወለደው የኢትዮጵያውያን አንድነት ለኢትዮጵያ ዓባይነት

ደበል ካሳ

"ታሪክ ማለት የሰው ልጅ ስለ ራሱ የሚያውቅበት ግላዊ ዕውቀት ነው… ሰዎች ምን ሊሰሩ እንደሚችሉ ለማወቅ የሚያስችለው ብቸኛው ፍንጭ ሰዎች ከዚህ ቀደም የሠሩት ሥራ ነው። ስለሆነም የታሪክ ዋነኛው ፋይዳ ሰው ምን ሠራ? የሚለውን ለእኛ ለሰው ልጆች ማስተማርና በዚህም 'ሰው ምንድነው? የሚለውን እንድናውቅ ማድረግ ነው" ይለናል አር. ጂ. ኮሊንግውድ የተባለ የታሪክ ሊቅ። አባባሉ የታሪክን ትክክለኛ ምንነትና ፋይዳ በሚገባ የሚያመላክት ነው።

ምክንያቱም አላዋቂዎችና የትንሽነትና ታህተ ሰብዓዊነት፣ የአጥንት ቆጠራና የኢ-ምክንያታዊና ግዑዛዊ መንገኝነት ፖለቲካ መስራችና አቀንቃኝ የሆኑት ትሕነግና መሰሎቻቸው እንደሚሉት ታሪክ ተራ ተረት ተረት ሳይሆን የፈለጉትን ማድረግና መሆን እንደሚቻል ሰዎች በተግባር መሆናቸውንና መቻላቸውን የሚያረጋግጡበት መንገድ ነው። ታሪክ ዛሬን ከትናንትናና ከወደፊቱ ጋር የሚያገናኝ፣ የአሁኑና መጭው ትውልድ መሆንና ማድረግ እንደሚቻል በወሬ ሳይሆን በድርጊት የሚማርበት ህያው የድርጊት ቤተ ሙከራ ነው።

ይህንን የታሪክ እውነታ ይዘን የሃገራችንን ታሪክ ስንመረምር እጅጉን ደስ የሚያሰኝና የሚያኮራ የታሪክ እውነትን እናገኛለን። ምክንያቱም ታሪካችን ሁሉ የአሸናፊነትና የመቻል ነውና! ከጥንት ከቅድመ ዓለም ጀምሮ እስከ የቅርብ ዘመኖቹ አድዋና የፋሽስት ወረራ ለሦስት ሺ ዓመታት በኢትዮጵያ ነጻነት ላይ ደጋግማ የዘመተችው ኢጣሊያ፣ አስራ ስድስት ጊዜ ሞክራ አስራ ስድስት ጊዜ የተሸነፈችው ታሪካዊ ጠላታችን ግብጽ፣ በኦቶማን ቱርክም ሆነ በዚያድባሬዋ ሶማሊያ… ክብሯንና ነጻነቷን ለመድፈር በሞከረ ማንኛውም ኃያል ነኝ ባይ ወይንም እብሪተኛ ምድራዊ ኃይል ኢትዮጵያ በታሪኳ ተሸንፋ አታውቅምና። ምክንያቱም እኛ ማድረግ ፈልገን ያልቻልነው፤ የተሸናፊነት ታሪክ የለንምና!

ታሪክ አሸናፊነትን በተግባር የምንማርበት የመቻል ቤተ ሙከራ ነው፣ ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን ማድረግ የቻሉትን እኛም ማድረግ እንችላለንና እኛም ዛሬ የገጠሙንን ፈተናዎች ሁሉ እያሸነፍን በመቻል ጎዳና ላይ እንገኛለን። ለዚህ ደግሞ ከገዛ ማህፀኗ ተወልዶ "ክብሯን ረግጬ በኃይል አንበርክኬ እኔ ብቻ እገዛታለሁ፣ ካልሆነ አፈርሳታለሁ" ብሎ በወጋን አሁናዊው ጠላታችን ትሕነግና ሌሎች ተባባሪዎቹ ላይ እያስመዘገብን የምንገኘው ድል አንዱ ማሳያ ነው። በአያሌ መሰናክሎችንና የውስጥና የውጭ ጠላቶቻችን ሴራ አሸንፈን ከሰሞኑ በድል ያከናወንነው የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዙር የውሃ ሙሊትና ሁለተኛ ተርባይን የኃይል ማመንጨት ሥራም ሌላው የአሸናፊነታችን ትልቅ ማረጋገጫ ነው።

የአሸናፊነት፣ የነጻነትና የጀግንነት አኩሪ ታሪካችን ሁለ ነገራችን የተመሰረተበት፣ ማንነታችን የተገነባበት ሥጋና ደማችን፣ አስተሳሰባችንና አመለካከታችን አጠቃላይ ሕዝባዊ ሥነ ልቦናችን የተሠራበት፣ በየትኛውም ጊዜ የማይለወጥ፣ በማንኛውም ጊዜ የማያስስ የታላቋ ሃገራችን የኢትዮጵያ ዘላለማዊ ሥሪት ነው። እኛም አሁን እንደአባቶቻችን በማሸነፍ ላይ እንገኛለን። ከምንም በላይ ታሪክ ሥነ ልቦና ነውና አባቶቻችን ባወረሱን የአሸናፊነት ሥነ ልቦናና የመቻል ውርስ በዚህም በዓለም ላይ ተከብረው እኛንም አስከብረው እንደኖሩ ሁሉ፤ በክብር ኖረው በክብር እንዳኖሩን ሁሉ እኛም ከሃዲውንና ዋናውን አሁናዊ የህልውና ጠላታችን ትሕነግን ጨምሮ የክብራችንና የነጻነታችን ጠላት የሆኑ ማናቸውንም የዘመናችንን ጠላቶች በማሸነፍ እንደአባቶቻችን በክብር መኖር ጀምረናል። እንደአባቶቻችን አንድ ላይ ተባብረን ጠላቶቻችን በመመከትና የታላቅነት መንገዳችንን ዓባይን እየገነባን በአንድነት ወደአሸናፊነት ወደታላቅነት ወደዓባነት እያመራን እንገኛለን።

የአሸናፊነታችንና የድላችን ሁሉ ሚስጥር ደግሞ አንድነታችን ነው። እጅግ የቅርቡንና በዓለም ላይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው የሰው ልጅ ፍጡር ዘንድ እንድንከበርና እንድንኮራ ያደረገንን አንዱንና ዋነኛውን የነጻነትና የክብር ታሪካችን በማሳየነት በማንሳት ልጀምር። እብሪተኞች እንደ ሰው የማይቆጥሩት የጥቁር ህዝብ "ምንጊዜም የበላይ ነን" ብሎ የሚያምነውን የነጭ ወራሪ በጦር ሜዳ ገጥሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ያሸነፍንና እናም ለጥቁር ሕዝብ ሁሉ ኩራት የሆነውን ከዚያም አልፎ ለመላው ሰው ልጆች ሁሉ የሰውነት ክብርን ያጎናጸፈውን አኩሪ ታሪክ የሠራነው በአንድነታችን ነው። ይህም አንድነታችን ለራሳችን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችንና ለመላው የሰው ዘር በሙሉ፣ ከራሳቸው ከነጭ ዘር የተገኙ ጭቁን ህዝቦች ሁሉ ለነጻነታቸው እንዲታገሉ ምክንያት፣ ድል አመላካች፣ የአሸናፊነት ምልክት እንድንሆን አድርጎናል።

እንደአንድ ልብ የመከረ ልባችን፤ በአንድነት የቆመ ኢትዮጵያዊ ምርኩዛችን፣ የተባበረ ክንዳችን ሁልጊዜ የአሸናፊነታችንና የክብራችን የታላቅነታችን ምንጭ ነው። እናም በአሁኗ ኢትዮጵያ የምንገኝ እኔና የእኔ ትውልድ ጀግንነታችንና ኩሩነታችንን አስጠብቀን ለመቀጠል እንደ አባቶቻችን በአንድነት መመከትና በጀግንነት ዋጋ በመክፈል የአባቶቻችን ልጆች መሆናችንን በተግባር ማረጋገጥ ይጠበቅብናል። ልክ የህልውና ጠላታችን ትሕነግን በተባበረ ክንድ አዋርደን እንደመለስነው፣ ልክ በተባበረ ክንድ ዓባይን በራሳችን አቅም እየገነባንና ድል እየተቀዳጀን እንደምንገኘው በአንድነት መቆም ስንችል ነው እንደ አባቶቻችን አኩሪ ታሪክ መስራት የምንችለው። በዚህ መንገድ ነው ወደቀደመ የታላቅነት የ "ዓባይነት" ታሪካችን መመለስ የምንችለው።

በተከፋፈለ ግንጥል ማንነታችን ሳይሆን በሙሉ ኃያል ኢትዮጵያዊ አንድነታችን ኢትዮጵያዊ ክብራችንን ዝቅ የሚያደርጉ ነገሮችን ሁሉ እንደ አባቶቻችን በጀግንነት ታግለን በድል መወጣት ስንችል ነው እኛም በኩራት ኢትዮጵያም በክብር መኖር የምትችለው። ትውልዱ እንደቀደምቶቹ አባቶቹና እናቶቹ ጀግና ነኝ ለማለትና ኩሩ ሆኖ ለመገኘት በምኞት ሳይሆን እንዲህ እንደአሁኑ በተግባር ማድረግ የሚገባውን አድርጎ መገኘት፤ የራሱን ዘመን ሥራ ሠርቶ ጀግንነትን ፈጽሞ እንደ አያት ቅድመ አያቶቹ፣ እንደ እናት አባቶቹ አኩሪ ታሪክ ፈጽሞ በኩራት በክብር ለመኖር የሚያስችለውን ታሪክ አድርጎና ሆኖ መገኘት አለበት። በዓባይ ላይ ያሳየነውን ኢትዮጵያዊ አንድነት አጠናክረን ከቀጥልን ደግሞ አሸናፊነትን ብቻ ሳይሆን የጥንቱን ዓባይነታችን የማንጎናጸፍበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም። ኢትዮጵያም ዛሬም ጠላቶቿን አሸንፋ በክብርና በነጻነት ከፍ ብላ ትኖራለች! በዓባይ አንድ ሆናለች፣ በአንድነቷም ዓባይ ሆና ለዘላለምም በክብር ትኖራለች!

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ዳግም ፋሽን ሆኖ የመጣው ንቅሳት

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ንቅሳት ድሮ ድሮ የገጠር ሴቶች ማጌጫ፣ ውበትን አጉልቶ ማሳያና የተለያዩ አካባቢዎች ባህላዊ ጌጥ ነበር። በገጠር ለኮረዳዎች የሚደረገው ንቅሳት እድሜ ልክ የማይጠፋ ኪንና ስን የታከለበት ማጌጪያ ነው። በእንቆቅልሽም «ስኖርም ስሞትም የማይለየኝ ጌጤ» ተብሎ የሚጠየቀው ንቅሳት ዕድሜ ዘመን የማይጠፋ መሆኑን ለማመላከት ነው። ‹ንቅስ ያለች› ሲባልም ቆንጆ ለማለት ነው። ንቅሳት በፈረንጆች ታቱ ተብሎ ይጠራል። ስያሜው ከፓሲፊክ ውቅያኖስ የታሂቲ ደሴት ነዋሪዎች የመጣ መሆኑም ይነገራል። ንቅሳት የሰዎችን የሰውነት አካል በስዕል፣ በፊደልና ሌሎችም ነገሮች የማስዋብ ጥበብ ነው። ማንም ሰው ዘው ብሎ ሊገባበት የሚችል ሙያም አይደለም። ነቃሽ ለመሆን የስዕል ዝንባሌ ሊኖር ይገባል።

ባህላዊው ንቅሳት ፤ ኩል፤ የወይራ ጭስና ኑግ ተወቅጦ በአጠፉሪስ ቅጠል ጭማቂ ተለውሶ ይዘጋጃል። ከዛም በአጋም እሾህ ፣ መርፌ፣ ወይም ወስፌ ወይዛዝርት ይነቀሱታል። የአገራችን ጥንታዊ ስነ ግጥሞችም ይህንኑ ይገልፃሉ፡-

**ተነቀሽ ተነቀሽ ተነቀሽ በሾክ፣**
**ትሆኝ እንደሆን የእናትሽ ምትክ።**
**ንቅሳትሽማ መቁጠርያ የሚመስለው፣**
**ያን ውበትሽን አስበለጠው ከሰው።**

ኮረዳዎቹ ሲነቀሱት ለህመማቸው ማስታገሻ አስካሪ መጠጥ ጠጥተው እንዲደነዝዙ ተደርጎ ነው። በተነቀሱበት አካላቸውም ላይ ስስ ሻሽ ተከናንበው ሦስት ቀን ከበዛም ሳምንትም ይቆዩበታል። ይህም እንዳይደማ፣ቁስሉ እንዲደርቅና ንቅሳቱ እንዳይጠፋ ለማድረግ መሆኑን እናቶች ይናገራሉ።

በገጠር በእግር፣ በደረት፣ በግንባር ፣ በአንገት ፣ በእጅ (አይበሉባ)፣ በባት፣ በድድና በክንድ፣ እንዲሁም በአገጭና በጉንጭ ላይ ንቅሳት ሊሰራ ይችላል። በተጠቀሱት አካላት የሚነቀሱ እንዳሉ ሁሉ ፤ በአንድ ወይ ሁለት ቦታ የሚነቀሱ ወይዛዝርትም አይጠፉም። በግንባር ላይ የመስቀል፣ የክብና የኮኮብ ምልክት መነቀስ የተለመደ ነው። በአንገት እና በአገጭ ላይ መሰላል ወይም ሀዲድ መሳይ ስዕልን ለጌጥን ብዙ ወይዛዝርት ተነቅሰውም ማየት የተለመደ ነው። ንቅሳታቸውን ብቻ በማየት የየት አካባቢ ነዋሪ እንደሆኑ የሚለዩም አሉ።



በሰሜኑ የኢትዮጵያ አንዳንድ አካባቢ መበጣት እንደ ንቅሳት ይታያል። ንቅሳት ውበትን እምነትን፣ ጀግንነትን፣ ፍቅርን ቅጣትን እንዲሁም ከለላን አመላካች ሆኖ ለበርካታ ዘመናት ማገልገሉ ይገለጻል። ቀደም ብሎም ንቅሳት የባሮችና የእስረኞች መለያ ሆኖ ማገልገሉን አንዳንድ ጽሁፎች ያሳያሉ።

በዘመናችን በከተሞች አካባቢ በሴቶች ዘንድ ባህላዊው የመነቀስ ልምድ እየቀነሰ መምጣቱን የሚናገሩ ቢኖሩም ቀድሞም ከገጠር ተነቅሰው የመጡ እንጂ በከተሞች ንቅሳት እንዳልነበረ የሚናገሩ አልጠፉም። አሁን አሁን ግን መልኩን ቀየረ እንጂ በተለያዩ ከተሞች ንቅሳት በዘመናዊ መልኩ በወጣቶች ላይ በስፋት እየታየ ነው። ከድሮው በተለየም ወንዱም ሴቱም እንደ ፋሽን ወደ ንቅሳቱ ጠጋ ጠጋ እያለ መሆኑን ማስተዋል ይቻላል።

አሁን አሁን በመላው ዓለም ሊባል በሚችል ደረጃ ንቅሳት እንደ ዘመናዊና ፋሽን ተከታይነት ሲቆጠር ይታያል። በተለይም በስፖርተኞች፣ በተዋንያን በታዋቂ ሰዎች ዘንድ በስፋት ይስተዋላል። በሀገራችንም የነዚህን ዝነኛ ሰዎች ንቅሳት በማየት በከተሜው ወጣቶች ዘንድ ፋሽኑን የመከተል ባህል እየሰፋ ይገኛል። ንቅሳት መነሻው ከአፍሪካ ቢሆንም ምንጩ ግን መበጣትም (ውቅራት) ሆነ ንቅሳት በኢትዮጵያ መሆኑን የሚናገሩ አሉ።

ሰውነትን በንቅሳት ማስዋብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዘመናዊ መልኩ እንደፋሽን በበርካታ የዓለማችን ክፍሎች እንደተስፋፋ ጽሁፎች ያመለክታሉ። በተለይ በአሜሪካ፣ በጃፓን፣ በአውሮፓ ተወዳጅ ሆኗል። የንቅሳት ባህል እንደ ፋሽን ሊስፋፋ የቻለው የቴክኒክ እና የስነ-ጥበብ ስልጠና ያላቸው አዳዲስ ባለሞያዎች ወደ ዘርፉ በመግባታቸው ነው ተብሎ ይታመናል። በተጨማሪም የሚነቀሱ ዝነኛና ተፅእኖ ፈጣሪ ሰዎች በቴሊቪዥንና በፊልም ወይም በፎቶ ሲታዩ ንቅሳታቸውም ጭምር መካተቱ በከተሞች መነቀስን በርካቶች እንደፋሽን እንዲከተሉ ተፅዕኖ ማሳደሩ ይታመናል።

ዘመናዊ የንቅሳት ቀለም እና መሣሪያ በየግዜው መሻሻሉም ለጥበቡ ማደግ አስተዋጽኦ አድርጓል። በመዲናችን ወጣቶች ከሚስተዋሉ የንቅሳት አይነቶች መካከል ሃይማታዊ ምስሎች፣እርግብ አእዋፍትና ሌሎች እንስሳቶችን በስፋት ማየት ይቻላል።

በአዲስ ከተማ አብነት አካባቢ ዘመናዊ ንቅሳት የሚሰራው ወጣት ሚኪያስ አሸናፊ ወደ ሙያው የገባው ከስምንት ዓመት በፊት ተማሪ እያለ መሆኑን ይናገራል። ሙያውን በአካባቢው ንቅሳት ከሚሠሩ ሰዎች የለመደው ሲሆን ራሱ ላይ ሞክሮ ጓደኞቹን መነቀስ እንደጀመረ ያስታውሳል። በማኅበራዊ ገፆች በሚለቃቸው ምስሎች እንዲሁም የተነቀሱ ሰዎችን በማየት ወጣት ወንዶችና ሴቶች ለመነቀስ እሱ ጋር እንደሚመጡ ይናገራል።

በከተሞች እንደፋሽን ወጣት ወንዶችና ሴቶች በስፋት እንደሚነቀሱ የሚናገረው ወጣት ሚኪያስ፤ መንቀሻ መሣሪያው ከውጪ አገር እንደሚመጣና በአገር ውስጥም ተመሳስሎ የሚሰራ እንዳለ ያስረዳል። የመነቀሻ መርፌዎችን እንዲሁም ቀለሞችን አንድ ሰው ከተነቀሰባቸው በኋላ ሌላ ሰው እንደማይጠቀምባቸው የሚናገረው ሚኪያስ፣ ይህም የደንበኞችን ጤንነት ለመጠበቅ ሲባል እንደሚደረግ ያብራራል። ‹‹ሰው እንደየፍላጎቱ ይነቀሳል›› የሚለው ወጣት ሚኪያስ የሌሎችን አይተው የሚነቀሱ እንዳሉ ሁሉ እሱ በሚያቀርብላቸው ምርጫ የሚነቀሱም እንዳሉ ይናገራል።

እንደ ሚኪያስ ገለፃ ክንዳቸው ላይ፣ጀርባቸው ላይ፣ ደረት አካባቢ፣ ከጡታቸው ከፍ ብሎ የሚነቀሱ ወጣቶች አሉ። በአንገት ጎን የሚነቀሱ ወንዶች ፤ ከጆሮ ጀርባ በኩል መስቀል ፣ኮከብ ነገሮች የሚነቀሱ ሴቶችም አሉ። የወዳጃቸውን ወይም የፍቅር አጋራቸውን ስም የሚነቀሱም አሉ። አበባ፣ የሃይማት ምስሎችንና እንስሳትን መነቀስም የተለመደ ነው። መነቀስ ሕመም ቢኖረውም ሰዎች ችለው ከመነቀስ ወደ ኋላ እንደማይሉም ወጣት ሚኪያስ ይናገራል። ሰዎች ሲነቀሱ በሚፈጠርባቸው ሕመም የሚያሳዩት የተለያየ ስሜት አለ። መጮኸም፣ መወራጨትም፣ አንዳንዴ ማልቀስም ይኖራል።

እጅዋን አበባ ስትነቀስ ያገኘኋት ሰሎሜ ሚደቅሳ ፤የጓደኛዋ ሜሮን ግደይ ንቅሳትን በማየት በበጎ ቅናት ለመነቀስ እንደወሰነች ትናገራለች። ሜሮን በበኩሏ በክንዷ ላይ የሃይማኖታዊ ምስልና በእጇ ላይ ደግሞ የእንቡጥ አበባ ምስል ተነቅሳለች። ‹‹መነቀስ ፈልጎ ሕመምን መሸሽ አይሆንም›› ትላለች። ‹‹የምትነቀሰው በመርፌ እየተወጋህ ስለሆነ መታገስ ግድ ነው›› በማለትም ያለውን ስሜት ትናገራለች።

የሙያው ባለቤት ሚኪያስ ፤ ሰዎች የሚነቀሱት የእረፍት ጊዜ ሲኖራቸው መሆኑን ይናገራል። ሰዎች ንቅሳትን የሚጠቀሙት እንደፋሽንና ቆዳን ለማስዋብ ከመሆኑ በተጨማሪ ጠባሳ ነገር ያለባቸውም ጠባሳቸውን ለመሸፈን ብለው እንደሚነቀሱ ያስረዳል። ‹‹ክረምት ላይ ብዙም የሚነቀስ የለም፣ ንቅሳቱም ሕመም ነገር ስላለው ሰዎች ከመስከረም በኋላ ያለውን ጊዜ ይመርጡታል›› ይላል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ራሳችንን በትክክል እንመልከት

**አቤል ገ/ኪዳን**

ሰሞኑን ሮይተርስ ላይ አንድ ዜና እያነበብኩ ነበር። ዜናው ከዩክሬን ጋር ይፋዊ ጦርነት ከምዕራባውያን ጋር ደግሞ የእጅ አዙር ጦርነት የገጠመችው ሩሲያ በዓመት ውስጥ በነዳጅ ሽያጭ ብቻ 337 ቢሊየን ዶላር ማግኘት መቻሏን የሚያሳይ ነው። ገረመኝ። ኢትዮጵያ ዘንድሮ ታሪካዊ የሆነ ኤክስፖርት አድርጋ ያገኘችው 4 ነጥብ 1 ቢሊየን ዶላር ነው። ሩሲያ ከነዳች ብቻ ያገኘችው ገቢ 83 እጥፍ ይበልጣል ማለት ነው። ይሄ የነዳጁ ብቻ ነው። ሩሲያ ከነዳጅ ባለፈ ስንዴ ፤ ማዳበሪያ ፤ ብረት፤ የጦር መሳሪያ እና ሌሎች ነገሮችንም ትሸጣለች። ይሄ ሲጨመር አመታዊ ገቢዋ የትና የት ይሆናል። ከዚያ አንጻር ሲታይ የእኛ ኢኮኖሚ ታላላቅ አውሮፕላን ተሸካሚ የጦር መርከቦች ባሉበት ባህር ላይ ትንሽዬ የእንጨት ጀልባ ይዘን የምንንቀሳቀስ ግለሰቦች እንሆናለን። እንዲያም ቢሆን ግን እኛ ኢትዮጵያውያን አሁንም ቢሆን እጅግ ሀብታም እንደሆንን ፤ በዚህም የተነሳ አለም የኛ ዋነኛ ጠላት እንደሆነ እና እኛን ለማጥፋት ሲደክም እንደሚውል እናምናለን።

እርግጥ ነው ኢትዮጵያ ታላቅ ሀገር ናት። ባለብዙ ታሪክ ፤ ባለብዙ ሀብት ፤ ባለብዙ ተስፋ። ነገር ግን ደግሞ በብዙ በኩል ወደኋላ የቀረን እንደሆንንም መረዳት አለብን። ይህ ሲባል ከብዙ ነገር አንጻር ነው። እስኪ ጥቂቱን በምሳሌ እንመልከት። በቅርቡ ቅዱስ ጊዮርጊስ የእግር ኳስ ክለብ የወዳጅነት ጨዋታ ለማድረግ ወደ ታንዛንያ አቅንቶ ነበር። ታንዛንያ የህዝብ ብዛቷ ከኢትዮጵያ ግማሽ ቢሆን ነው። መዲናዋ ካምፓላም እንደዚያው። ነገር ግን ጋባዡ ክለብ ሲምባ ከቅዱስ ጊዮርጊስ ጋር የሚያደርገውን ጨዋታ ለመታደም በመዲናዋ በሚገኘው ቤንጃሚን ምካፓ ስቴድየም 60ሺ ህዝብ ተገኝቶ ነበር። ይሄ አዲስ አበባ ላይ የማይሳካ ነው። አንድም ያን ያህል ህዝብ የሚይዝ ስቴድየም የለንም ፤ ሁለተኛ በዚያ ልክ የሚሞላ ህዝብ ለብሄራዊ ቡድን ጨዋታ ካልሆነ በክለብ ጨዋታ በመደበኛነት አይገኝም። ከዚያ ደግሞ ሌላኛው አስገራሚ ነገር ጋባዡ ክለብ የፌስቡክ ገጹ 1 ነጥብ 1 ሚሊየን የኢንስታግራም ገጹ ደግሞ 1 ነጥብ 9 ሚሊየን ተከታይ አለው። ይህ ቁጥር በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ የሚሳተፉ ክለቦች ካላቸው ተከታይ ጠቅላላ ድምር ይበልጣል። ክለቡ በአመት 5 ነጥብ 3 ሚሊየን ዶላር ገደማ ያለው ሲሆን ይሄም እንደዚሁ በኢትዮጵያ እግር ኳስ በአንድ ክለብ ደረጃ ያልተደረሰበት ከፍተኛ ገንዘብ ነው። እንዲያም ቢሆን ግን አሁንም ኢትዮጵያውያን አሁንም እግር ኳስን በጣም እንደምንወድ እና ለእግር ኳሱ ከፍተኛ ገንዘብ እንደምናወጣ ነው የምናስበው። ይሄ ራስን ያለመመልከት ውጤት ነው።

አሁንም ኳሱ ላይ እንቆይና ሌላ የተሳሳተ ምልከታ እንይ። ብዙዎቻችን ኢትዮጵያውያን በእግር ኳስ ተሰጥኦ እንዳለን እናምናለን። ይህን ግን የሚሞግተን ኳሱን በደንብ ከሚያውቁ ሰዎች መካከል አንዱ የሆነው የቀድሞው ኮከብ ሙሉአለም ጥላሁን ነው። ”በአሁኑ ወቅት በውጭ ሀገር የሚኖረው ሙሉአለም እንዲህ ይላል አንዳንድ የሀገራችን የእግር ኳስ ቤተሰቦች እኛ ኢትዮጵያውያን ያለን የኳስ ታለንት ከአውሮፓዊያኑም ሳይቀር ይበልጣል እያሉ በተደጋጋሚ ሲናገሩ እያደመጥን ሲጽፉም እያየን ነው ። የእኔ እይታ ግን ከዚህ ሃሳብ ፍጹም ተቃራኒ ነው በእራሱ የእግር ኳስ ክህሎት ፤ ተጋጣሚን በማለፍ ፤ መምታት ፤ ኳስ ማቀበል ፤ኳስ መቆጣጠር፤ ኳስ መግጨት ፤ ሩጫ በየትኛው ነው እኛ የምንሻለው? እነሱ የደርሱበት ለመድረስ ከቻልን በብዙ ስራ እንጂ በማይረባ ግምት እና ምኞት አይሆንም። ፡ ይላል። ሙሉአለም ይህን ያለው እንዲሁ ለመተቸት በመፈለግ ሳይሆን እግር ኳሱን በተግባር ከማወቅ እና በኳሱ ብዙ የሰሩትን ሀገሮች ከማየት ነው።

ከስፖርቱ ወጥተን ወደ ኪነ ጥበቡ ዘርፍም ብንሄድ ነገሩ ተመሳሳይ ነው። በሲኒማው ዘርፍ ከአጼ ምኒሊክ ዘመን የሚጀምር ታሪክ እንዳለን እና ሲኒማን በማወቅ ረገድ በአፍሪካ ቀዳሚ ከሚባሉት እንደምንመደብ እንናገራለን። በአሁኑ ወቅት በከተማው የፊልም ሰሪ ቁጥርም እንደበዛ እና ኪነ ጥበቡ በኢኮኖሚ እየጎለበተ እንደሆነ ፤ የአሁን አርቲስት የድሮ ተዋንያን ሊያገኙት ቀርቶ ሊያስቡት የማይቻላቸውን ገንዘብ እያገኘ እንደሆነ እንናገራለን። ነገር ግን ነባራዊው ቁጥር እንደሚያሳየው የአፍሪካ መዲና በምትባለው አዲስ አበባ ውስጥ ያሉት ሲኒማ ቤቶች ቁጥር 34 ብቻ ነው። እዚሁ ባላንጣችን ግብጽ ግን ከመቶ በላይ ሲኒማዎች ያሏት ሲሆን በአመት ከአስር በላይ የፊልም ፌስቲቫሎች ታዘጋጃለች። የፊልም ኢንደስትሪውም በአመት ከ50 ሚሊየን ዶላር በላይ ገቢ ለሀገሪቱ ያስገኛል።

በዚህ መልኩ በትምህርት ፤ በጤና ፤ በመንገድ ፤ በቴክኖሎጂ ወዘተ ብንሄድ ሀገራችን ያለችበት ደረጃ እኛ ከምናስበው ትልቅነት አንጻር ጨርሶ የማይገናኝ እንደሆነ እንገነዘባለን። ነገር ግን አሁንም ጨክነን እውነታውን ከመጋፈጥ ይልቅ ሌሎች የተሳካላቸው ሰይጣንን ስለሚያመልኩ ፤ ኢሉሚናቲ ስለሆኑ ወዘተ እንደሆነ ለራሳችን እንናገራለን። ይህ የትም አያደርስም። እንኳን እኛ ብዙ የቤት ስራ ያለብን በስልጣኔ ማማ ላይ ጫፍ ደርሰናል የሚሉት ሀገራት እንኳን በስኬታቸው ከመኩራራት በላይ ያልተሳካላቸው ነገር ላይ አተኩረው ነው የሚሰሩት።

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆን አንድ ነገር ልጥቀስና ጽሁፌን ልቋጭ ። በ2012 እ.ኤ.አ የተለቀቀ ዘ ኒውስሩም የተሰኘ ተከታታይ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ድራማ ነበር። በዚያ ፊልም ላይ በአንድ አዳራሽ ውስጥ የተሰበሰቡ ተማሪዎች ለምሁራን ጥያቄ ያቀርባሉ። አንዲት ተማሪም እድሉ ደርሷት ምሁራኑን አሜሪካ የአለም ታላቋ ሀገር ያሰኛት ምንድን ነው የሚል ጥያቄ ታቀርባለች። አንዳቸው ዴሞክራሲያዊ መሆናችን ነው አሉ ፤ ሌላኛው ምሁር ብዝሀነት እና እድል ናቸው አሉ። ሶስተኛው ሰው ግን በዚህ አልስማማም አለ። አሜሪካ የአለም ትልቋ ሀገር አይደለችም አለ። ከዚያም አሜሪካ አለምን የምትመራው በሳይንስ ወይም በኢኮኖሚ ወይም በሌላ ሳይሆን በእስር ላይ ባሉ ዜጎች ብዛት እና በሰራዊቷ ብዛት እንደሆነ ተናገረ። ከዚያ ውጭ ባለው ነገር ግን ሌሎች ሀገራት እንደሚመሯት ተናገረ። ከዚያ ባለፈ አሜሪካ ትልልቆቹ እሴቶቿን እያጣች እንደሆነ ተናገረ። ተመልካቹ የሰውየውን ንግግር መቃወም አልቻለም።

እኛም እንዲህ አይነት ወደ ራስ የሚያሳይ ንግግር ያስፈልገናል። እኛ ከአለም ምርጥ የሆንነው በምንድን ነው ከሩጫ ውጭ የምንጠቅሰው በጎ ነገር ያለ አይመስልም። በሌሎቹ ነገሮች ላይ በማስረጃ ልንከራከርበት የምንችለው አስተማማኝ ጉዳይ የለንም። ስለዚህም ራሳችንን መመልከት ያስፈልገናል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# ትምህርትና መምህርነት

መኩሪያ አለማየሁ

ትምህርት የሰው ልጅን ወደተሻለ ልዕቀትና ልዕልን የሚያሻግር መሣሪያ ነው። ሁሉም ሀገር ያደገውና የበለጸገው በትምህርት ነው። የትምህርት ባሕል/መሠረት የላቸውም የሚባሉ ሀገራት ቢያድጉ እንኳን ከተፈጥሮ ሀብታቸው ጋር ከሌላው ማኅበረሰብ የተማረውን ኃይል ይዘው ነው። በአንድ ሀገር የተሳካ ትምህርት ከሌለ ጥሩ ዜጋ ማፍራት፣ የሰለጠነ ሀገር መገንባትና የሀገርን የተፈጥሮ ሀብት መጠቀም አይቻልም። የአንድ ሀገር የድኅነት መገለጫውም የትምህርት ውድቀት ነው። የተሳካ ትምህርት ባለበት ሀገር ዕድገትና ብልጽግና፣ ሥልጣኔና መራቀቅ፣ ሀብትና ባለጠግነት በሀገሩ ይኖራል።

የአስኳላው ትምህርት በኢትዮጵያ የተጀመረው በዳግማዊ አጼ ምንልክ ነው። ንጉሡ በጊዜው ሃይማኖታዊና ሀገር በቀል ትምህርት በሀገሩ ቢኖርም ለአውሮፓው ትምህርትም ልዩ ትኩረት ነበራቸው። ለዚህም እንዲህ ብለው ነበር ‹‹በጣም ወደኋላ የቀረን ሕዝቦች ነን፤ ገና ብዙ ስራ ስላለብን ወጣቶች መማር አለባቸው ›› በዚህ ብቻ አላበቁም ተተኪው ትውልድ ዘምኖ ለመኖር፣ በልቶ ለማደር፣ ሀገር ለማቅናት የሚችለው ሲማር ብቻ ስለሆነ እንዲህም ይመክሩ ነበር ‹‹እኔ ቤት እንጀራ የለም፤ እንጀራ ያለው ትምህርት ቤት ነው፤ ስለሆነም እሰራሁት ትምህርት ቤት ልጆቻችሁን እያስገባችሁ አስተምሩ ››

በዚህ አጭር የዘመናዊ ያልነው የትምህርት ታሪካችን ውስጥ በቅጡ የትምህርት ብርሃን በሀገሩ ሳይወጣ የትምህርት ፍቅርና ዓላማ እያደር አሽቆልቁሏል። የዛሬው አብዛኛው ተማሪ በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች የምረቃ ከንፈር ላይ ሆኖ እንኳ በሙያው ከመስራት ይልቅ ‹ምን ሰርቼ፣ እንዴት ብዬ ገንዘብ ማግኘት እችላለሁ› የሚለውን ሐሳብ ከተገቢ የሙያዊ ክፍያ ጋር ያለውን ሁኔታ የሚመለከተው አካል ቆም ብሎ ማሰብ አለበት። አደጉ ያልናቸው ሀገራት ያደጉት በትምህርት ስለሆነ በሀገር ላይ በጎ ነገር ለማየት፣ የውስጥን ጥያቄ የሚያርስ መልስ ለማግኘት፣ በትውልድም ተስፋ ለማድረግ፣ ለአንድነታችን መልካም ነገር ለማሰብ፣ መጪው ጊዜ ብሩሕ ይሆናል ብሎ ለመመኘት፣ ጥሩ የታሪክ ገጽታም ከፊታችን እንዲገጥመን፣ ሕዝብ በፍቅርና በሐሴት ተሞልቶ እንዲኖር ትምህርት ቁልፍ መሣሪያ ነው። ለዚህም የትምህርት አመራሮች ድርሻችሁ ሰፊ ነው።

ትምህርት በአንድ ሀገር ላይ የሰለጠነ የሰው ሀብት ማፍሪያ፣ ምርታማ ስራ መከወኛ፣ በቴክኖሎጂ መበልጸጊያ፣ በክዕሎትና በዕውቀት መዳበሪያ፣ ለሚገጥሙን ሀገራዊ ተግዳሮቶች መፍትሔ አምጪና ጠቋሚ በመሆን በማኅበራዊ ኑሮና በፖለቲካው ባሕል ላይ ዓለምን የሚመጥን ሥልጡን ትውልድም ማፍሪያ ነው። ለዚህ ትሩፋት ደግሞ ትምህርቱን፣ የሙያው ባለቤት መምህሩንና መምህርነትን ማክበር ተገቢ ነው።

መምህርነት ሙያ ነው። ለዛውም ኀሩይና የተከበረ ሙያ። የሙያዎች ሁሉ ፈጣሪና አባት። ሀገር መሪው ሳይንቲስቱ፣ ፖለቲከኛው የኪነጥበብ ባለሙያው፣ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ሊቁ፣ እንዲሁም የተለያዩ የክህሎትና የዕውቀት ባለቤቶች ...ሁሉም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የመምህራን አሻራ ያረፈባቸው ናቸው።

ማንኛውም ሙያ ባለቤት አለው። አንድን ሙያ ደግሞ የምናከብረውን ያህል የሙያውን ባለቤት ልናከብረው ይገባል፤ ስናከብርውም ዕውቀቱን፣ ክዕሎቱን፣ አመለካከቱን፣ ልምዱንና የሙያውን ፍቅር ጭምር ልናከብረው ይገባል። በዋናነት የትምህርት ባለሙያዎችና ባለቤቶች ደግሞ መምህራን ናቸው። መምህራን እንደማንኛውም የተከበሩ ባለሙያዎች ሊታዩ ይገባል። ምክንያቱም የማስተማር ዓላማ የሰው ልጅ ሕይወቱና ስራው እንዲሻሻል፤ በሀገር ላይ ዕድገትና ሥልጣኔ እንዲመጣ፤ ዓለም እንዲቀና፤ የሰውልጅ የመልካም አመለካከት ባለቤት እንዲሆንና በጥበብ እንዲያብብ የሚያግዝ ነው።

በሌላው ሀገር ብዙኀኑ መምህራን የተስተካከለ ገቢ የሚያገኙ፣ መንግስትና ሕዝብ የሚንከባከባቸው፣ ከመሠረታዊ ፍላጎታቸው በላይ የሆኑ፣ ማኅበራዊ ከፍታና ከበሬታ ያላቸው፣ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነታቸው የማይነጥፍባቸው ናቸው። ለዚህም ሙያቸውን ወደውና አክብረው ይሰራሉ። እንደኛ ሀገር መምህራን በብዙ ዘመናት በተስፋ እየተሞሉ ጥቂት ተለግሷቸው በብዙ እየጎደላቸው ትኩረትና ክብር የተነፈጋቸው ይመስላሉ። በዚህ ሁሉ ከባድ ተግዳሮት እንኳን ለሙያው ትኩረት የሰጡና ራሳቸውን መስዋዕት ያደረጉት ለሙያው ካላቸው ፍቅር የተነሳ ነው።

> ትምህርት በአንድ ሀገር ላይ የሰለጠነ የሰው ሀብት ማፍሪያ፣ ምርታማ ስራ መከወኛ፣ በቴክኖሎጂ መበልጸጊያ፣ በክዕሎትና በዕውቀት መዳበሪያ፣ ለሚገጥሙን ሀገራዊ ተግዳሮቶች መፍትሔ አምጪና ጠቋሚ በመሆን በማኅበራዊ ኑሮና በፖለቲካው ባሕል ላይ ዓለምን የሚመጥን ሥልጡን ትውልድም ማፍሪያ ነው

አንድ ክፍለ ዘመን ያለፈው ይህ ግዙፍ ተቋም ሙያውን ሀ ብሎ ከጀመረበት እስከ ዛሬ እያደር በየመንግስታቱ ዘመናት የመምህራን ኑሮ፣ ክብር፣ ሞራል፣ ማኅበራዊ ተቀባይነትና የትምህርት ፍቅር እየወረደ ቢመጣም እንደዛሬ ዘመን የባሰበት ጊዜ ግን የለም ማለት ይቻላል። የዚህ ሁሉ ምክንያት ደግሞ እያደር ሙያውና ሙያተኛው ተገቢውን ክብር ስላላገኙ ነው። መምህርነት እንደሻማ ለሌላው እያበሩ ተቃጥሎ መሞት ሳይሆን፤ እንደ ፀሐይ ሰርክ አዲስ ብርሃን በመሆን የማይነጥቡበት ሕይወት ነው መሆን ያለበት።

## ሁሉም ሙያ የራሱ ክብርና ልክ አለው

ሁሉም ሙያ በራሱ ልክ ተከባሪነት፣ ተደማጭነትና ታማኝነት አለው። ይብዛም ይነስም አንድ መሐንዲስ የሚገነባው ቤት ለዚህ ያህል ዓመት በምቾትና በጥራት ይቆያል ቢል ይታመናል። አንድ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ የሀገሪቷን የምጣኔ ዕድገት መንገድ ቢያመላክት ቅቡልነትን ያገኛል። አንድ የግብርና ባለሙያ የምርት ውጤት የሚለካው በዚህ መንገድ ነው ቢል ታምኖ ስራ ላይ ይውልለታል። አንድ የቤተ ሙከራ ባለሙያ የሰጠንን ውጤት እናምነውና እንጠቀምበታለን።

አንድ ሐኪም መርምሮ የነገረንን እንቀበላለን። የሰጠንን መድኀኒት አምነን እንወስዳለን። መምህራን ግን ለሥርዓተ ትምህርቱ፣ ለትምህርት ጥራት፣ ለተማሪው ለውጥ፣ ለትምህርት ውጤትና ለመማር ማስተማር ሂደት ሁሉ የሙያው ሐኪሞች ሆነው ሳለ ግን እንደሌሎቹ ባለሙያዎች አይታዩም። አንድ ታማሚ በሥነ-ባሕራዊም ሆነ በሳይንሳዊ መንገድ ፈውስ የሚያገኘው ሐኪሙ ላይ እምነት ሲጥል ብቻ ነው። እንዲሁም መምህራንም ለተማሪዎች የዕውቀት፣ የክዕሎት፣ የአመለካከት፣ የዕድገትና የልዕልና ሐኪሞች ናቸው።

በትምህርት ሥርዓት ውስጥ ከታች ጀምሮ ያሉ መምህራን ሊደመጡ ይገባል ። ይህን ያህል የትምህርት ጊዜ፣ ይህ የትምህርት ይዘት፣ ይህ ትምህርት ሥርዓት፣ ይህ አይነት የማስተማሪያ መንገድ ይሻላል የሚሉት ነገር ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባዋ ልክ እንደ ሐኪሙ። ሐኪሙ ከታመነ ሐኪሙን የፈጠረው መምህርም ሊታመን ይገባዋል።

በተለይ ከቅድመ መደበኛ እስከ መሰናዶ ድረስ ያሉ እንደ ሙያው ልክ በክብር ሊያዙና ሊከበሩ ይገባል። ትንሽ የተሻለ የሆነው በኮሌጆችና በዩኒቨርሲቲዎች ላይ ላሉት ነው። እሱም ቢሆን የአካዳሚው ነጻነት የሚያጠያቅ ይመስላል።

## የመምህራን ልዩነት የሚመስል ከየት መጣ?

ዛሬ ብዙኀኑ የትምህርት ጥራት መውረድ መምህሩን ተጠያቂ የሚያደርጉ እንደሚበዙ ይታወቃል። በዚህ የሙያ መስክ ውስጥ ግን ለሙያው በቂ የሆኑ ባለሙያዎች ሞልተዋል። በመንግስትም ሆነ በግል የትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ መምህራን በመንግስት ወይም በግል ኮሌጆች ውስጥ የተማሩ ናቸው። የትምህርት ጥራት በመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ ብዙኀኑ ተጠያቂ መምህራንን ሲደርጉ ይደመጣል። ግን የምንግሥት ትምህርት ቤት በሀገሪቱ ያበረከተው አስተዋጽኦ ቀለላል አይደለም።

ለምሳሌ ያህል በመንግስትና በግል የትምህርት ተቋማት ውስጥ የትምህርት ውጤት ልዩነት የመጣው በትምህርት አሰጣጥ ነጻነት፣ መምህሩ በሚኖረው ጥቅማጥቅምና የተማሪዎች የኑሮ ዘይቤ ምክንያት እንጂ በሌላ አይደለም። ለአብነት ያህል የሀገራችን መሪዎችና ባለስልጣናት ከመንግስት ትምህርት ቤት ተምረው የወጡ ናቸው። ለምሳሌ ያህል ዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ በከፈቱት ትምህርት ቤት ውስጥ ቀዳማዊ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ ተምረዋል። /ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ቋንቋ እንደተማሩ መስማቴ እንደመረጃ ወስጄዋለሁ/ ዐፄ ኃይለ ሥላሴ በከፈቱት ትምህርት ቤት ውስጥ ኮሌሬል መንግስቱ ኃይለማርያም፣ የቀድሞዎቹ ጠቅላይ ሚኒስተሮች አቶ መለስ ዜናዊና አቶ ኃለማርም ደሳለኝ ተምረዋል።

ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ ባስፋፉት ትምህርት ተቋም ውስጥ ጠ/ሚ ዶ.ር ዐብይ አሕመድ ተምረዋል። ሌሎችም ባለስልጣናት ከዚህ የተለየ ዕድል አላገኙም። /ተጨማሪ ውጭ ትምህርት ዕድል እንዳለ ሆኖ እሱም በለሱ ለቀናው ነው። / ታዲያ የመንግስት መምህራን ይህን ዐይነት ፍሬ ያፈሩ ከሆነ የመንግስት ትምህርት ቤትን ውጤት አልባ ማድረግ ምን ያህል ያሳምናል? በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት ታሪክ ውስጥ የትኛው ዶክተርና ፕሮፌሰር፣ ተመራማሪና ሊዕቃን በጥናትና ምርምሩ ዘርፍ በሀገርና በዓለም አቀፍ የሚታወቁ ምሁራን ወይም የሀገር መሪዎች ከግል ትምህርት ቤት ወጡ? ዛሬ ያለው መሪ፣ ምሁርና ሌሎችንም ያስገኘው የመንግስትን የትምህርት ተቋምና መምህር ለምን ይወቅሳል?።

ከመንግሥት አካላት እስከ ማኅበረሰቡ ልጆቹንስ ለማስተማር ለምን አይደፍርም? ዛሬ እንደፈለጋችሁት አልሆን ካላችሁ ለምን አትለውጡትም ? ለነገሩ ማኅበረሰባችን ውድ ነገር የመውደድ አባዜ አለበት። ነገሮች በነጻና በቅናሽ ሲሆንበት አይወድም ለምሳሌ ለነርሰሪና ለዩኒቨርሲቲ ተማሪ ልጆቹ እኩል ክፍያ ከፍሎ ያስተምራል። በግል ትምህርት ቤት ለአንድ ሕጻን ምግብ፣ አልባሱና የትራንስፖርቱን ዋጋ ትተን በሺዎች ከፍለን የምናስተምረው ሕጻን አድጎ በዲግሪ ተመርቆ ስራ ሲይዝ ወርሃዊ ደመውዙ አራት ሺህ ብር አካባቢ ነው/ በመንግስት የደመወዝ እስኬል/። ሁሌ ውድ የከፈልንባቸው ነገሮች ትርፍ አይደሉም፤ ነጻና ዝቅተኛ ክፍያ ያደረግንበት ደግሞ ኪሳራ አይደለም። ብልህነት ነባራዊ ሁኔታውን ማሰብ ነው።

ዛሬ ብዙኀን የመንግስት መምህራን ለሙያው ኀሩይ ሆነው የተፈጠሩለትን ያህል በብዙ ፈታኝ ነገሮች ውስጥ ሆነው እንኳን ሀገርን እያገለገሉ ይገኛሉ። ለሀገር፣ ለትውልድ፣ ለሙያው ሟች ሆነው ሁሌም አሸናፊና የሙሉዕነት፣ የመሪነት፣ የተመራማሪነት ስሜት ተሰምቷቸው የሚታገሉ ባለሙያዎች አሉበት። በሚገጥማቸው ተግዳሮት እየተፋለሙ ለሙያው ሲሉ በነፍሳቸው ሰይፍ እንደሚልፍ እያወቁ እንኳን ለመከራዎቹ እጅ አልሰጡም። ዓላማቸውም ልክ ታላቁ ደራሲ ጋሽ ስብሐት ገ/እግዚአብሔር እንዳለው ነው።

“የመምህርነትን ሙያ አቤት ስወደው ለምን መሰለህ ሽኩቻህና ፍልሚያህ ከማወቅና ካለማወቅ ጋር ነው። እምትመቀኘው ሌላውን ሳይሆን ድንቁርናን ነው። የሚያስደስተውም ደግሞ የዘራኸው አድጎ ሲያፈራ በማየት ነው። ስለዚህ በጣም እወደዋለው”

የሙያ ባለቤቶች ይህ ነው የሚባል ሀብትና ንብረት ሳይኖራቸው ንጹህ እረኛ ሆነው በጎችን በድንቁርና ተኩላ እንዳይነጠቁ የሚታደጉ ናቸው። ታዲያ በዚህ መስክ ውስጥ ይህንን ሙያተኛ ሐሳቡን መስማት፣ ተገቢ ክፍያና ጥቅማ ጥቅም መስጠት፣ ማኅበራዊ ከፍታ እንዲገኝ ማድረግ ካልተቻለ በትምህርት የታለመለት ግብ ላይ እንዴት መድረስ ይቻላል? ዓለም የተለወጠው በትምህርትና በትምህርት ብቻ ነው።

ትምህርት ያለወጠው ግለሰብ፣ ማኅበረሰብ፣ ሀገርና ዓለም የለም። በተለይ ዛሬ ዓለም ራሷን ለውድድር ያዘጋጀችው በትምህርት ነው። ትምህርት ለዕድገት፣ለብልጽግና ለሥልጣኔ መሠረት መሆኑ ከታመነ ሊታሰብበት ይገባል። ለዚህም ከዛሬ በላቀ ብቁ መምህራን፣ ጥሩ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች፣ መሰናዶዎችና ሃይስኩሎች እንዲሁም አንደኛ ደረጃና ደረጃቸውን የጠበቁ የመንግስት መዋዕለ ሕጻናት ሊፈጠሩ ይገባል / በዚህም ማኅበረሰቡ ያላግባብ ከመበዝበዝ ይድናል/።

በአጠቃላይ የድህነት፣ የኋላ ቀርነት፣ የበታችነት ታሪክ የሚታደሰውና ዕድገትና ሥልጣኔ የሚመጣው በትምህርት ነው። ለትምህርት ዕድገት ደግሞ ባለሙያውን መምህሩን ልናከብረው ይገባል።

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# ኢትዮጵያን አረንጓዴ ያለበሱ አረንጓዴ አሻራዎች

ጌትነት ምህረቴ



ጠቅላይ ሚኒስትደክተር ዐብይ አህመድ  በድሬዳዋ በተካሄደው የዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ማጠቃለያ በመገኘት ችግኞችን ተክለዋል፡፡

በደን የተሸፈኑ አረጓዴ ተራሮችንና የለመለሙ መስኮችን ማየት ያስደስታል፤ መንፈስን ያረካል፤ እንደ ስጋጃ የተነጠፈ አረጓዴ ደን ሲያዩት ያምራል፤ ቀልብን ይማርካል። በተለይ እንደ ማንጎ፣ አቮካዶ፣ ወይን፣ ፓፓያ፣ ብርቱካንና ቡና ባሉ ዛፎች የተሸፈነ ደን ከሆነ ደግሞ ምጣኔ ሀብታዊ ጥቅሙ እጥፍ ድርብ ይሆናል። ቋሚ የገቢ ምንጭ በመሆንም ያገለግላል። ደኑ የሀገር በቀል የዛፍ ዝርያዎች የተካተቱበት ሲሆን ደግሞ ዝርያዎቹ ለመዳህኒት፣ ለፍራፍሬ፣ ለአካባቢ ጥበቃ፣ወዘተ. ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸው እንደመሆናቸው ፋይዳው የበለጠ እየጎላ ይመጣል።

በኢትዮጵያ በአረጓዴ የተሸፈኑ አካባቢዎችን ማየት ብርቅ መሆን ከጀመረ በርካታ አመታትን ተሻግሯል። በተለይ በስሜንና በምስራቅ የአገሪቱ ክፍል ችግሩ ጎልቶ ይታያል። ይህ ደግሞ አካባቢው ለተደጋጋሚ ድርቅ መከሰት፣ለመሬት መራቆትና ለምንጮችና ወንዞች መድረቅ በምክንያትነት ይጠቀሳል።

ችግሩን ለመፍታትም በኢትዮጵያ ዘላቂነት ያለው የዛፍ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብር መካሄድ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል። ለዚህም ነው በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ አነሳሽነት የዛሬ አራት ዓመት የአረጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ተግባራዊ መደረግ የጀመረው። ኢትዮጵያ በአራት ዓመታት በአረጓዴ አሻራ መርሃ ግብር ከ25 ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከሏም በቅርቡ ይፋ ተደርጓል።

በአራት ዓመታት በአረጓዴ አሻራ መርሀ ግብር 20 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ ከ25 ቢሊዮን በላይ ችግኝ መትከል መቻሉን የሚገልጹት የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ዑመር ሁሴን፤ እስከ ነሀሴ 8 ቀን 2014 ዓ.ም ድረስም በአራተኛው አረጓንዴ አሻራ መርሀ ግብር ሰባት ነጥብ0 8 ቢሊዮን ችግኞች ተተክለዋል ይላሉ። ይህም የህዝብ ተሳትፎ ያስገኘው ትልቅ ስኬት መሆኑን ያስታወቁት።

በአሁኑ ጊዜ ያልተተከሉ አምስት መቶ ሚሊዮን ችግኞች መኖራቸውን ጠቅሰው፤ እነዚህ ቀሪ ችግኞችም በቀጣይ ዝናብ በሚጀምርባቸው የአገሪቱ ክፍሎች እስከ መስከረም ወር ድረስ እንደሚተከሉም ይጠቁማሉ። ችግኝ የመትከሉ ባህል በህብረተሰቡ ዘንድ ሰርፆ የዘወትር ተግባር እስኪሆን ድረስ በቀጣይም በችግኝ ተከላው ላይ በትኩረት ይሰራል ነው ያሉት።

25 ሚሊዮን ያህል ኢትዮጵያውያንም ችግኝ በማፍላት፣ የችግኝ ጉድጓድ በመቆፈር እና የተተከለውን በመንከባከብ መሳተፋቸውም ነው ሚኒስትሩ የጠቀሱት። የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ ስኬታማነት ማሳያዎች ብለውም፥ ዘመቻው ሲጀመር 40 ሺህ ብቻ የነበሩት የችግኝ ማፍያዎች አሁን ላይ ወደ 121 ሺህ ማደጋቸውን፣ በዓመት 7 ነጥብ 6 ቢሊዮን ችግኞችን የማፍላት አቅም መፈጠሩን ጠቅሰዋል።

የችግኝ ተከላው በስፋት በመላ አገሪቱ በየዓመቱ በተከታታይ በመካሄዱ ብዙ ለውጦች መገኘታቸውን፣ ከእነዚህ መካከልም የደን ሽፋን ማድጉን፣ የፍራፍሬ ዛፎች በየቦታው መተከላቸውን፣ የመሬት መሸርሸር እየቀነሰ መሄዱንና የግብርና ምርታማነት እየጨመረ መምጣቱን ሚኒስትሩ በአብነት ጠቅሰዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ በበኩላቸው ባለፈው ሳምንት በድሬዳዋ ከተማ በተካሄደው አራተኛው የአረጓዴ አሻራ ማጠቃለያ መርሀ ግብር ላይ እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ በአራት ዓመታት በአረጓዴ አሻራ ያስገኘችው ውጤት ስኬታማ ነው። የተተከሉ ችግኞች የአየር ንብረት ተፅእኖን በመቋቋምና የግብርናን ምርታማነት በማሳደግ ረገድ ለውጥ እያመጡ ናቸው።

ጥቂት ሚሊዮኖች ችግኞችን መትከልን እንደ ድል በምትቆጥር ዓለም ላይ በአራት ክረምት 25 ቢሊዮን ችግኞችን በመትከል ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ዓላማን ማሳካት እንደሚቻል አሳይተንበታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በሀገራችን አረንጓዴ ዐሻራ መጀመሩ ለኢትዮጵያ ሁለት ወሳኝ እድሎችን ፈጥሯል ይላሉ። አንደኛው በትልቁ አስበን ከተባበርን በትልቁ ማሳካት እንደምንችል ምስክር ሆኖናል ፤ሁለተኛው ለብልጽግና መሠረት የሚሆን ባህል መፍጠር ተችሏል ሲሉ አብራርተዋል።

ችግኝ የመትከል ባህል ሲውል ሲያድር በምግብ ራሳችንን እንድንችል፣ ግድቦቻችን ዘላቂ ዝናብ እንዲያገኙ፣ ለም አፈራችን እንዳይሸረሸር ያደርጋም ነው ያሉት። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአራት ተከታታይ ዓመታት በኢትዮጵያ ሲካሄድ የቆየው የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻ በሀገሪቱ አረንጓዴ ባህልን በመፍጠር ስኬታማ ቢሆንም፣ አሁንም ብዙ ስራ ይጠብቀናል ብለዋል።

ባለፉትን ጥቂት ሳምንታት ብቻ በዓለም ዙሪያ የተስተዋሉት የጎርፍ አደጋ፣ የደን ቃጠሎ፣ ሀይለኛ ማዕበል እና ያልተለመደ ሙቀትን የመሳሰሉ ክስተቶች ለአየር ንብረት ለውጥ ዓይነተኛ ማሳያዎች መሆናቸውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመልዕክታቸው አስገንዝበዋል። የአፍሪካ ቀንድን ያጠቃው ድርቅም የዚሁ የአየር ንብረት ለውጥ ውጤት መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ በኢትዮጵያም የአየር ንብረት ለውጥ የውሃ ምንጮችን አድርቋል፤ በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎችም የድርቅ አደጋን አስከትሏል ። አሁን ላይ ዓለም እየተሰቃየ ያለበትን ይህን ችግር ለመፍታት ከስብሰባዎች ያለፈ ተግባራዊ መፍትሄ መውሰድ ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ በ2011 ዓ. ም ላይ ተፋሰስን ለማልማት፣ የደን ሽፋኗን ለማሳደግ፣ ኢኮቱሪዝምን ለማስፋፋት እና የከተሞቿን የአረንጓዴ ሽፋን ለማሳደግ የአረንጓዴ አሻራ ዘመቻን ጀምራለች። እንዲህ ዓይነቱ ተግባራዊ መፍትሄ በመውሰዱ ኢትዮጵያ ውጤታማ ሆና ትጠቀሳለች።

ሀገሪቱ ለአራት ዓመታት በዘለቀው ዘመቻ 20 ቢሊየን ችግኞችን ለመትከል ወጥና ብትነሳም፥ ዜጎቿ 25 ቢሊየን ችግኞችን በመትከል ካስቀመጡት ግብ በላይ ፈጸመዋል። ለችግኝ ተከላ የሚያስፈልጉ ቦታዎችን በመምረጡ እና ለተከላ በማዘጋጀቱ ረገድም የታየው እምርታም ሌላው የሚደነቅ ተግባር ነው። በዚህ ስኬት ውስጥ የፖለቲካ ፍላጎት እና ቁርጠኝነት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል።

አሁንም ብዙ ስራ ቢጠበቅም በሀገሪቱ አረንጓዴ ባህልን በመፍጠሩ ረገድ ዘመቻው እንደተሳካ ጥርጥር የለንም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በመላው ሀገሪቱ የሚገኙ ከተሞች አሁን ላይ የአረንጓዴ ስፍራ አስፈላጊነትን ተረድተው ቦታ እያዘጋጁለት መምጣታቸው ለተፈጠረው አረንጓዴ ባህል ማሳያ ነው ብለዋል። ይህ አረንጓዴ ባህል ለቀጣዩ ትውልድም የሚቆይ መሆኑንም አንስተዋል።

አረንጓዴ ባህልን ከመፍጠር ባለፈ ዘመቻው ለ767 ሺህ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ያበረከተውን ኢኮኖሚያዊ አስተዋፅኦም በቀላሉ የሚታይ አይደለም ሲሉም ነው የተናገሩት። ይህ የኢትዮጵያ የችግኝ ተከላ ጥረት ለዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ሰበብ የሆነውን የበካይ ጋዝ ልቀት ለመቀነስ አንዱ መፍትሄ መሆኑን አስታውቀዋል።

የታዳሽ ሃይል በሆኑት የውሃ፣ ንፋስ፣ ፀሃይ እና የእንፋሎት የሀይል ማመንጫ ጣቢያዎች ላይ የምታውለው መዋዕለ ንዋይም ሌላው የዓለም አየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል በበኩሏ እየተወጣች የምትገኘው ሀላፊነት መሆኑን ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስገነዘቡት።

አፍሪካ ብሎም ዓለም ተፅዕኖው እየከፋ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከል እንዲህ ዓይነቱን ተግባራዊ መፍትሄ እንዲጠቀሙ ጥሪ አቅርበዋል። በተለይ የአፍሪካ ሀገራት በአየር ንብረት ለውጥ ችግር ላይ ለሚወያዩ ስብሰባዎች መዋዕለ ንዋያቸውን ከሚያፈሱ ይልቅ፥ ለችግኝ ተከላ ስራዎች እንዲያውሉ ጠይቀዋል። የአየር ፀባይ ለውጥ ተፅዕኖን ለመቋቋም ከኮንፈረንስ እና ከጉባኤዎች ባሻገር ተጨባጭ ተግባርን የሚጠይቅ መሆኑን ነው ያመለከቱት።

ባለፉት ሳምንታት የታዩ ክስተቶች የአየር ፀባይ ለውጥ እየተከሰተ ስለመሆኑ ካላሳመኑን ሌላ ምንም ነገር ሊያሳምነን አይችልም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሀገራት ጎርፍ፣ ሰደድ እሳት፣ ኃይለኛ አውሎ ንፋስ፣ ያልተጠበቀ ሙቀት፣ በረሃማነት እና ሌሎች ከፍተኛ የአየር ፀባይ ለውጦች እየደረሰባቸው እንደሆነ ነው የገለጹት።

እነዚህ በተደጋጋሚ እና በከፍተኛ መጠን የሚከሰቱ የአየር ፀባይ ለውጦች በሰው ልጅ አኗኗር እና ጤና ላይ ተፅዕኖ እያሳደሩ ነው። እዚሁ ቅርባችን የሚገኙ የምሥራቅ አፍሪካ እና የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት እየተጠናቀቀ ባለው አመት ባገጠማቸው የአየር ፀባይ ለውጥ ለድርቅ መዳረጋቸውን፣ በሀገራችንም በአንዳንድ አካባቢዎች የተፈጠረው የአየር ፀባይ ለውጥ የውኃ ምንጮች እንዲደርቁ እና ድርቅ እንዲከሰት ምክንያት ሆኗል።

የአየር ፀባይ ለውጥ በሰው ልጆች ላይ እያደረሰ ያለውን ተፅዕኖ ዛሬ እንደ ዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ እውነታውን የምንኖርበት ወሳኝ ደረጃ ላይ ደርሰናል ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ጠቁመው ፤ችግኞችን በስፋት ሁሌም መትከል የሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ቁርጠኝነት እና ንቁ ተሳትፎን ይፈልጋል ነው ያሉት።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ በሁሉም ደረጃ የሚገኙትን የኅብረተሰብ ክፍሎች በማንቀሳቀስ ውጤታማ የሆነችበት ሁኔታ ተፈጥሯል። የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብርም የተፋሰስ ልማት ላይ አዎንታዊ ለውጥን ለማምጣት፣ የደን ሽፋንን ለማሳደግ፣ ለምግብነት የሚውሉ ተክሎችን ለማስፋት፣ የኢኮ-ቱሪዝምን ለማጠናከር እና ከተሞችን አረንጓዴ ለማልበስ ታስቦ የተጀመረ ነው።

ለዚህም በአራት ዓመታት ጊዜ ውስጥ 20 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ለመላው ኢትዮጵያውያን በቀረበው ጥሪ መሠረት በችግኝ ተከላው ከ25 ሚሊዮን ሰዎች በላይ ተሳትፈዋል። በዚህም በየዓመቱ ለመትከል ከታቀዱ ችግኞች በላይ በመትከል በአራት ዓመታት 25 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል።

የአየር ፀባይ ለውጥ ጫናን በጋራ ለመከላከል የአፍሪካ ሀገራት እና ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ኢትዮጵያ የወሰደችውን ዓይነት ተጨባጭ እርምጃዎችን እንዲወስዱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

የአረንጓዴ አሻራ ውጤት የደን ሽፋንን ከማሳደግ ባለፈ ምርታማነት እንዲጨምር ማድረጉን አመልክተው፣ የምግብ ዋስትናን በአስተማማኝ መልኩ ለማረጋገጥ በፍራፍሬ ችግኞች ላይ ማተኮር ይኖርብናል የሚል መልዕክትም አስተላልፈዋል። በቀጣይ የአረጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ለገበያ በሚውሉ ችግኞችና ጥራት ላይ በማተኮር ስንዴ ብቻ ሳይሆን እንደ ወይን፣ አቮካዶና ሻይ ቅጠል ያሉ ምርቶች በስፋት ለወጪ ገበያ ማቅረብ እንችላለን ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አመልክተዋል ።

**ሀገሪቱ ለአራት ዓመታት በዘለቀው ዘመቻ 20 ቢሊየን ችግኞችን ለመትከል ወጥና ብትነሳም፥ ዜጎቿ 25 ቢሊየን ችግኞችን በመትከል ካስቀመጡት ግብ በላይ ፈጸመዋል። ለችግኝ ተከላ የሚያስፈልጉ ቦታዎችን በመምረጡ እና ለተከላ በማዘጋጀቱ ረገድም የታየው እምርታም ሌላው የሚደነቅ ተግባር ነው። በዚህ ስኬት ውስጥ የፖለቲካ ፍላጎት እና ቁርጠኝነት ቁልፍ ሚና ተጫውቷል**

ማህበራዊ

# አስኳላ



መምህርት ደመቀ ሙሄ፤



ፎቶ፡- አስናቀ ፀጋዬ

ርእሰ መምህር በላይ አስፋው፤



ተማሪ ሃምዛ መሀመድ፤

# አዲሱ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች አካሄድ

**አስናቀ ፀጋዬ**

እድሜው ከአስር አይበልጥም። በፊቱ ላይ ደማቅ ፈገግታ ይታያል። ከሌሎች አቻ ጓደኞቹ ጋር እንደበፊቱ እየቧረቀ ነው። ደስታው ከልክ አልፎ የናፈቃቸውን የክፍል ጓደኞቹን አሁንም አሁንም ያቅፋቸዋል። ከጓደኞቹ ተለያይቶ ስለከረመ ጊዜውን እንዴትና በምን ሁኔታ እንዳሳለፉ የሚጠይቃቸው ይመስላል።

ጓደኞቹም እርሱን ተመሳሳይ ጥያቄ እየጠየቁት እንደሆነ ያስታውቃል። አይ የልጅ ነገር! ከፊቱ ፈገግታና ደስታው ጋር ተዳምሮ ምንም ነገር የደረሰበት አይመስልም።

ሕፃን ሃምዛ መሀመድ ይባላል። የአስር ዓመት ልጅ ሲሆን፤ የዛሬን አያድርገውና በሰሜን ወሎ ዞን ሀብሩ ወረዳ መርሳ ከተማ የመልካ ጨፌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአራተኛ ክፍል ተማሪ ነበር። ምን ያደርጋል አሸባሪው የህውሓት ቡድን ስፍራውን ሲቆጣጠር ትምህርት ቤቱን በማውደሙ ከትምህርት ገበታው ለመፈናቀል ተገዷል። ለስድስት ወራት ያህልም ከሚኖርበት አካባቢ ከቤተሰቦቹ ጋር ሸሽቶ ሌላ ቦታ ቆይቷል።

አሁን ግን የህወሓት አሸባሪ ቡድን በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ አማራ ልዩ ሃይልና ፋኖ በደረሰበት ጠንካራ ምት አካባቢውን ለቆ ከወጣ በኋላ በፈራረሰ ትምህርት ቤት ውስጥ ባልተመቻቸ ሁኔታ ከስምንት በማይበልጡ ወራቶች ውስጥ የዓመቱን የትምህርት መርሃ ግብር አጠናቋል።

ሆኖም የትምህርት ሚኒስቴር የወደሙ ትምህርት ቤቶችን መልሶ የመገንባት መርሃ ግብር በቅርቡ ሲጀምር ከሚታደሱ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሕፃን ሃምዛ ሲማርበት የነበረው የመልካ ጨፌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንዱ በመሆኑ አዲስና የተሻለ የመማር ተስፋ ጭሮበታል።

መምህርት ደመቁ ሙሄ በሰሜን ወሎ ዞን ሀብሩ ወረዳ የመልካ ጨፌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የስድስተኛ ክፍል ሳይንስ መምህር ናቸው። ወራሪው የህወሓት ቡድን አካባቢው ከመያዙ በፊት ትምህርት ቤቱ በወረዳው ከ2 ሺህ 250 በላይ የሚሆኑ ተማሪዎችን ተቀብሎ ሲያስተምር እንደነበር ያስታውሳሉ።

በተሟላ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ለተማሪዎች ትምህርት ይሰጥ እንደነበርም ያስታውሳሉ። ሆኖም ወራሪው ኃይል ቦታውን ከተቆጣጠረ በኋላ የትምህርት ቤቱን ቤተ ሙከራ፣ መፅሃፍት ቤትና የመማሪያ ክፍሎችን ሙሉ በሙሉ እንዳወደመና አስፈላጊ የሚባሉትን ሌሎች የትምህርት ግብአቶች እንደዘረፈ ይናገራሉ። በዚህም ወራሪ ቡድኑ ተመቶ አካባቢውን ከለቀቀ በኋላ የመማር ማስተማር ሂደቱ ሲጀምር አብዛኛው የትምህርት ቤቱ ንብረት በመውደሙ ተማሪዎችን ለማስተማር እጅግ አስቸጋሪ እንደነበርም ይገልፃሉ።

ከጥር ጀምሮ ከውድመት በተረፈው ትምህርት ቤት ውስጥ ተማሪዎችን እንደገና በመመለስ ማስተማር እንደተጀመረ መምህርት ደመቁ ተናግረው፤ የተሰበሩ ወንበሮችን በመጠገን፣ የትምህርት ቤቱን አጥር በሕብረተሰቡ ድጋፍ በማጠር፣ ከውድመት ተርፈው የወዳደቁ መፅሃፍትን በመልቀምና ለተማሪዎች በመስጠት ትምህርቱ እንዲቀጥል መደረጉን ያስረዳሉ። ይህንንም በማድረግ ከጥር ወር ወዲህ ባሉት ስደስት ወራት ውስጥ የዓመቱን ትምህርት ለተማሪዎቹ በመስጠት ማጠናቀቅ እንደተቻለም ይናገራሉ።

በትምህርት አሰጣጡ ሂደት ተማሪዎች በጦርነቱ ምክንያት ተፈናቅለው የቆዩ በመሆናቸው ስነ ልቦናቸው ተጎድቶ እንቆየ ማየታቸውንና የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ



ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፤

ተማሪዎቹን በመምከርና በመደገፍ ትምህርታቸውን በአግባቡ እንዲከታተሉ መደረጉንም ያመለክታሉ።

በወራሪ ቡድኑ የወደመውን ትምህርት ቤት ወደነበረበት ለመመለስ የትምህርት ሚኒስቴር የጀመረውን ተግባር እንደሚያደንቁ መምህርት ደመቁ ገልፀው፤ ከመንግስት በዘለለ ሕብረተሰቡ፣ የግል ድርጅቶችና ባለሃብቶች በመልሶ ግንባታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪያቸውን ያቀርባሉ።

የመልካ ጨፌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር አቶ በላይ አስፋው እንደሚናገሩት፤ ወራሪው ቡድን በወረዳው ከገባ በኋላ በትምህርት ቤቱ ያደረሰው ጉዳት እጅግ ከፍተኛ ነው። ሁለት የመማሪያ ክፍሎችን አፍርሷል። በክፍሎቹ ውስጥ የነበሩትን የተማሪዎችን ወንበሮች፣ የመምህራንን ሼልፎች፣ ጠረጴዛዎችንና ወንበሮችን ለማገዶነት አውሏዋል። የማባዣ ማሽኖችን፣ ኮምፒዩተሮችንና ሌሎች የአይ ሲ ቲ መሳሪዎችን በሙሉ ዘርፎ ሄዷል።

የተማሪዎችን መረጃና መዛግብቶችን በሙሉ አውድሟል። የመማሪያ ክፍሎችንም በማፈራረስና የአንድን ብሔር የበላይነት ብቻ የሚገልፅ ፅሁፍ በግድግዳዎቻቸው ላይ በመፃፍ መጥፎ ገፅታ እንዲኖራቸው አንድርጓል። በትምህርት ቤቱ አካባቢ ማህበረሰብ ላይም የስነ ልቦና ጫና አድርሷል። በዚሁ ምክንያት ከወረራው በኋላ የተማሪዎች ቁጥር ከ2 ሺ 250 ወደ 1 ሺ 782 እንዲያሽቆለቁል አድርጓልም ይላሉ።

እንደ ርዕሰ መምህሩ ገለፃ፤ ወራሪ ቡድኑ በትምህርት ቤቱ ላይ ባደረሰው ጉዳት ከ3ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት ሀብት ወድሟል። ከዚህ አኳያ ትምህርት ቤቱን በአዲስ መልክ መልሶ ለመገንባት ከዚህ የበለጠ ወጪ ይወጣል ተብሎ ይጠበቃል። ትምህርት ሚኒስቴር ባስጀመረው በዚህ የመልሶ ግንባታ መርሃ ግብር በሰዎች ለሰዎች ድርጅት የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት ሁለት የመማሪያ ክፍሎች፣ አንድ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት፣ የአይ ሲ ቲ ክፍል ይገነባሉ ተብሎ ይታመናል። ከዚህ ባለፈ የአይ ሲ ቲ ክፍል ኮምፒውተሮች፣ ማባዣዎች፣ ማተሚያዎች ይሟላሉ ተብሎም ይታሰባል። በተጨማሪም ቤተ ሙከራዎች፣ ቤተ መፅሃፍት፣ የስፖርት መስሪያ ሜዳዎችና ጂምናዚየም በመልሶ ግንባታው ይካተታሉ ተብሏልም።

ከወረራው በፊት ትምህርት ቤቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተማሪ ያስተናግድ የነበረ ቢሆንም ከወረራው በኋላ 468ቱ በወረራው ምክንያት ትምህርታቸውን አቋርጠዋል። ለትምህርት አስፈላጊ ግብአቶች ባለመሟላታቸውም የተማሪ መምህር ጥምርታ 1 ለ 60 በመሆኑ ትምህርቱ በበቂ ሁኔታ እንዳይሰጥ ማድረጉንም ይናገራሉ።

ትምህርት ቤቱ በአዲስ መልክ የሚገነባና አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ ግብአቶች የሚሟሉለት ከሆነ ቀደም ሲል ከነበረው የተማሪ ቁጥር በላይ ተቀብሎ ሊያስተናግድ ይችላል። ቀደም ሲል በወረራው ምክንያት ያቋረጡ ተማሪዎችን የመመለስ እድልም ይኖራል።

ርዕሰ መምህሩ እንደሚሉት፤ ጦርነቱ ምንም እንኳን የራሱ ተፅዕኖና ጫና ቢኖረውም ከወረራው በኋላ የዓመቱን ትምህርት በስደስት ወራት ውስጥ ቅዳሜና እሁድን ጭምር በማስተማር ማጠናቀቅ ተችሏል። መምህራንና ሌሎች የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ሰራተኞች ሙያዊ ግዴታቸውን ለመወጣት የበኩላቸውን ጥረት አድርገዋል።

ትምህርት ቤቱ በጊዜያዊነትም ቢሆን ባለው መሰረተ ልማት ተማሪዎችን መቀበሉን ይቀጥላል። ተማሪ ለመማር ብሎ መጥቶ አይመለስም። ግንባታው ሲጠናቀቅ ደግሞ ቅበላውን በማሳደግ በተሻለ የመማር ማስተማር ከባቢ ላይ ተማሪዎችን ያስተምራል። ከዚህ አንፃር ትምህርት ሁሉንም ባለድርሻ አካላት የሚመለከት እንደመሆኑ ለትምህርት ቤቱ ዳግም ግንባታ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ግለሰቦች፣ ባለሃብቶችና ሕብረተሰቡ የበኩሉን አስተዋፅኦ እንዲያበርክት ጥሪያቸውን ያስተላልፋሉ።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በበኩላቸው እንደሚገልፁት፤ ከወረራው ጋር በተያያዘ በሰሜን ወሎ ላይ የደረሰው ችግር ከፍተኛ ነው። ወያኔዎች ከምንም ነገር አስቀድመው መጀመሪያ ማጥፋት የሚፈልጉትም ትምህርትን ነው። የተማረ፣ እውቀት ያለውና ማገናዘብ የሚችል ሰው ደግሞ በቀላሉ አይገዛም፤ ነፃነቱንም ይወዳል። ኃላፊነትን፣ መብትንና ግዴታን አብሮ አያይዞ ያያል። እንዲህ አይነት ሰዎች ያሉበት ሀገር ዝምብሎ በጨበጣና በጉልበት የሚያስተዳድር ኃይል ለረጅም ጊዜ አይቆይም።

በዚህ ምክንያት ወያኔዎች ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ከሰሩት ሥራዎች ውስጥ ሁለቱና ዋናዎቹ እንደማህበረሰብ ኢትዮጵያውያንን አብረው እንዳይኖሩ በዘር እየከፋፈሉ እርስበርስ ማባላትና የትምህርት ስርአቱንና ጥራቱን ማጥፋት ናቸው። «ትምህርት ብዙ ሥራ የሚጠይቅ ነው። አንድ ሀገር ትምህርት ላይ መዋዕለ ነዋይ ላፍስ ሲል ህንፃውን ማቆም አይደለም። ልጆቹ መማር የሚችሉበት አካባቢ መፍጠር ነው። ከንፅህና ጀምሮ ጭቃ የሌለው ቦታ ኳስ መጫወት የሚችሉ ልጆች፣ በንፅህና ክፍል ውስጥ ገብተው የወደፊቱ ሕይወታቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ማየት የሚችሉበት፣ በትምህርት ቤታቸው መጠነኛ እርሻ ቦታ ተዘጋጅቶላቸው ከትምህርት ውጪ ትንሽ ዘመናዊ እርሻ የሚሞክሩበት፣ የእጅ ሥራ የሚማሩበት፣ ከትምህርት ቤት ሲወጡም ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ባይገቡም ማህረሰቡን ቢቀላቀሉ ትንሽ እውቀትና ክህሎት ይዘው የሚሄዱበት የትምህርት ስርአት ለመፍጠር ነው ትምህርት ሚንስቴር የተነሳው። » ይላሉም።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ አዲሱ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ተብሎ የተጀመረው አካሄድ በአንድ ቦታ ላይ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን፣ ማህበረሰቡና ተማሪዎች የሚገናኙበት አዳራሽ፣ የእጅ ሙያ መስሪያ፣ የእርሻ ቦታ፣ ከእርሻው ደግሞ የሚመረተውን እዛው ተማሪዎችን ማብላትና ትምህርት ቤቱ ውስጥ እንዲቆዩና እውቀትን መከታተል የሚችሉበትን አካባቢን መፍጠርን ያካትታል። የሚቀጥለው ትውልድ የትምህርት መሰረትም ይህ ነው የሚሆነው።

በወረራው ምክንያት በአማራና አፋር ክልል ወደ 1 ሺ 300 የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ፈርሰዋል። እነዚህን ትምህርት ቤቶች በቀጣዮቹ አምስት ዓመታት ውስጥ ለመገንባት እቅድ ተይዟል። ሆኖም ግንባታው ሲካሄድ ከጦርነቱ በፊት የነበረውን ትምህርት ቤት አይነት ማስቀመጥ አይፈለግም። ከዚህ ይልቅ ሙሉ በሙሉ አዲስ የትምህርት ቤት አይነት ነው ለመፍጠር የሚያስፈልገው። ዘመናዊ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች የሚባሉትም ለዛ ነው።

ከዚህ አኳያ በወራሪው በቡድኑ የወደመው የመልካ ጨፌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ታስቦ የተሰራ፤ ከስፖርት ጀምሮ ንፁህ የመማሪያ ክፍሎቹንና መፀዳጃ ቤቶችን፣ የአይ ሲ ቲ ክፍሎችንና ቤተመፅሃፍትን ያካተተ ሙሉ እውቀትንና ትምህርት ለተማሪዎች የሚሰጥበት ቦታ እንዲሆንም ነው። ይህንንም ለማድረግ ትምህርት ሚኒስቴር ብቻውን አይሰራም። አብረው የሚሰሩ ኃይሎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥም አንዱ የሰዎች ለሰዎች ድርጅት ነው። የመልካ ጨፌ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግንባታን በገንዘብ የሚደግፈውና የሚገነባውም የሰዎች ለሰዎች ድርጅት እንደሆነም ያነሳሉ።

በዚህ ዓመት ትምህርት ሚኒስቴር ከሚሳራቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ 14ቱን በፋይናንስ የሚደግፈውና የሚገነባውም ይኸው ድርጅት ነው። በዚሁ አካሄድ በኢትጵያ በርካታ የፈረሱ ትምህርት ቤቶችን በአዲስ መልክ ማሰራት የሚለውን ፕሮጀክት የሚደግፉ ሌሎች በርካታ ተቋማት አሉ። ይህን አዲስ አይነት የትምህርት ቤት ሥራ ትምህርት ሚኒስቴር ለመስራት ሲያስብ አጋር አካላት ከሚላቸው ውስጥ ህንጻውንና ሌሎች የትምህርት መሰረቶችን የሚገነባው ሰዎች ለሰዎች ድርጅት ብቻ ሳይሆን ወላጆችም እንደሆኑም ያስረዳሉ።

ወላጆች ትምህርት ቤቶቻቸውን የኛ ብለው ካልያዙትና ትምህርት ቤታቸው የተሻለ እንዲሆን አብረው ከትምህርት ማህበረሰቡ ጋር ካልሰሩ የሚታሰቡትን ተማሪዎች ማፍራት አይቻልም። ከዚህ አንፃር አዲሱ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ማዕከል ወላጆች ናቸው። እንደውም ትምህርት ቤቶቹ የአካባቢው ማህበረሰብ ማዕከል እንዲሆኑ ይፈለጋልም። የአካባቢው ማህረሰብ ከትምህርት ቤቶቹ ጋር ሁሌም ግንኙነት እንዲኖረው ያስፈልጋል።

ሌሎቹ የዚህ አዲስ አይነት የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች ሥራ አጋሮች መምህራን ሲሆኑ፤ ጥሩ መምህራን እንዲፈሩ አዲሱ የትምህርት ስርዓት መምህራንን ለመደገፍ፣ መምህራን ጥሩ ትምህርት እንዲሰጡ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማዘጋጀት ተዘጋጅቶ መጥቷል። በኮምፒዩተር ኦን ላይን የሚሰጡ ትምህርቶችን ለማመቻቸትና ሌሎች የሞያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን ለመስጠት ሥራዎች እንደሚሰሩም አስረድተዋል።

# ‹‹የአባይን ግድብ መገደባችን ፤ ካለፈው ስልጣኔያችን ጋር ስናስተያየው ለኢትዮጵያውያን ያን ያህል አያስደንቅም››

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ**
**ገጣሚና ጸሐፊ ተውኔት**

አስቴር ኤልያስ

ገጣሚና ጸሐፊ ተውኔት ናቸው። በተለይ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥተው ያጠናሉ፤ ይመራመራሉ። በአማራኛ፣ በእንግሊዝኛና በጀርመንኛ ከ60 በላይ የሚሆኑ መጻሕፍትና መጣጥፍ የጻፉ ሲሆን፣ ገና ያልታተሙም በእጃቸው ላይ እንደሚገኝ ይናገራሉ። በቅርቡ ደግሞ «ኢትዮጵያ ግብፅን እንደፈጠረቻት እና እንዳሰለጠነቻት» በሚል ርዕስ ለሕትመት ያበቁት የታሪክ መጽሐፍ ለግብጾችና ለአረቦች የዱባዳ ያህል እንደሚሆንባቸው የሚጠበቅ ሲሆን፣ ለብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ግን ገና ከወዲሁ ቀልባቸውን ይገዛ ጀምሯል። በዚሁ መጻፋቸውና በሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከፕሮፌሰር ፍቅሬ ቶሎሳ ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ «ኢትዮጵያ ግብጽን እንዳስተማረቻትና እንዳሰለጠነቻት» በሚል ርዕስ ለሕትመት የበቃው የመጽሐፍዎ ዋና ጭብጥ ምንድን ነው?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ግብጾች ውሃችንንና አፈራችንን ከመጠቀማቸውም በላይ ለእኛ ንቀት ያሳያሉ። በእኛ ውሃ እና አፈር ጠግበው እኛን መልሰው እንደ ድሃ ይቆጥሩናል። በጦርነትም አቅም እንደሌን ያስቡናል። ነገር ግን ጦርነትን በተመለከተ ከእኛ ጋር በተዋጉ ጊዜ ሁሉ እንዳሸነፍን ጠንቅቀው ያውቁናል። ይሁን እንጂ የአሁኑ ግብጻዊ ትውልድ ይህን የእኛን ጀግንነት አያውቀውም። ስለሆነም መጽሐፌ ይህን ጀግንነታችንን የሚያውቁበትን ቁምነገር ይዟል።

በሌላ በኩል የመጽሐፌ ጭብጥ ከሆነው አንዱ ግብጽ በቱሪዝሙ በኩል የምትምነሸነሽበትን ፒራሚድ የሰራነው እኛ ኢትዮጵያውያን እንደሆንን ግብጻውያኑም ሆኑ ሌሎቹ አያውቁትም፤ እንዲህ ስል ዝም ብሎ ታሪክ ለማዛባት አሊያ መሬት ላይ የሌለን እውነት ለማምጣት አይደለም። ነገር ግን ፒራምድን የሰራነው እኛ ነን። ግብጻውያን እውነታውን ያለመረዳታቸውን ለማረጋገጥ አንድ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። ይኸውም ቀላል ቁጥር የሌለው የግብጽ ሕዝብ የአባይ ውሃ ራሱ የሚመነጨው ከዛው ከግብጽ እንደሚመስለው መረዳት ይቻላል። የግብጽ የፖለቲካ መሪዎች ነን የሚሉት ሕዝቡን ያደነቆሩት እስከዚህ ድረስ ነው።

ስለዚህ እኛ ውሃውንም አፈሩንም ሰጥተናቸው አበልጽገናቸዋል። ፒራሚዱንም ሰርተን ስልጡን ሕዝብ አድርገናቸዋል። ከዚህ በላይ ማስተማር እና ማስልጠን ከወዴት ይመጣል። ይህን ያህል ብናደርግላቸውም ምንም አይነት ዋጋ አልሰጡንም፤ ይልቁኑ ተንቀናል፤ ተደፍረናልም። በመሆኑም ይህን መጽሐፍ ብዙ ዋጋ በመክፈል ለመጻፍ የቻልኩት ቁጭት በፈጠረው ተነሳሽነት ሲሆን፣ ራሳቸው ግብጻውያን የግብጽን ስልጣኔ ፈጣሪ እና መስራች እኛ እንደሆንን እንዲያውቁት ብሎም የዓረቡ ዓለምም በሙሉ እንዲረዳው በማሰብ ነው።

ግብጽ በምድሯ ምንም አይነት እርሻም ሆነ ስልጣኔ በሌለበት ጊዜ የዛሬ ስድስት ሺ ዓመት ገደማ ዓባይ ወንዛችን በከንቱ ሲፈስ ነበር። ነገር ግን ከኢትዮጵያ ተነስተው ኮሻይት ወደምትባል አካባቢ ሄደው አፈሩን አይተውና አልምተው እርሻም አርሰው እንዲሁም ፍልስፍናውን ፒራሚዱንም ሰርተው ያስተማሯቸው ኢትዮጵያውያን ናቸው። ከግሪክና ከጣሊያን ድረስ መጥተው አሪስቶትል፣ ፕሌቶ እና ሌሎችም ፈላስፋዎች ሁሉ ወደግብጽ መጥተው ከኢትዮጵያውያን ካህናት እውቀትን እንደቀሰሙ ራሳቸው በጻፉት መረጃና ሄሮዶቱስ በመባል የሚታወቀው የግሪክ ታሪክ ጸሐፊ ባሰፈረው መረጃ ላይ የተቀመጠ ነው። እኔም ታዋቂ የታሪክ ጸሐፊዎችን መረጃ ይዤ ነው የተነሳሳሁት።

**አዲስ ዘመን፡- የግብጻውያንን ፒራሚድ የሰሩት ኢትዮጵያውያን ስለመሆናቸው በመጽሐፍዎ ገልጸዋል፤ መረጃዎ ምን ያህል ጠንካራ ነው?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** የዛሬ 2 ሺ 50 ዓመት አካባቢ ከግሪክ አገር ተነስቶ የታሪክ አባት በመባል የሚታወቀው ግሪካዊው ሄሮዶቱስ ወደአፍሪካ አገር መጣ፤ ግብጽን፣ ሱዳንና ሊቢያን ጎበኘና በግብጽ ፒራሚድ ውስጥ ገብቶ በፒራሚዱ ውስጥ ያሉትን ጥቁሮች ከየት እንደመጡና፣ የዘር ግንዳቸው ከየት እንደሚመዘዝ ጥያቄ አቀረበላቸው። ይህንን ሁሉ ስልጣኔስ የዘረጋችሁት ማን ናችሁ? ብሎ ሲጠይቃቸው ምላሻቸውም ጥንት አባቶቻችንም የመጡት ከኢትዮጵያ ነውና እኛ ኢትዮጵያውያን ነን የሚል ነበር። ለማስረጃ የምትፈልግ ከሆነ ባለፉት ሶስት ሺ ዓመታት የነበሩትን የኢትዮጵያውያን ነገስታት ስም ዝርዝር ይኸውልህ ሲሉም ስላሳዩት ፒራሚዱን በማየት ፍልስፍናውንም ትምህርቱን ሁሉ በመመርመር በመጨረሻ ላይ ፒራሚዱን የገነቡት ብሎም ስልጣኔውንም የዘረጉት ለእኛ ለግሪኮችና ለጣሊያኖች ፍልስፍና ያስተማሩት ኢትዮጵያውያን ናቸው ሲል ደመደመ።

ከእርሱ በኋላ ደግሞ 400 ዓመት ያህል ዘግይቶ የመጣ ሌላው ዲዮዶሮስ የተባለ ሌላ የግሪክ ታሪክ ጸሐፊ ደግሞ ስዕላዊ ጽሑፉን፣ ስልጣኔውን፣ ኃይማኖቱን ብሎም አዝርዕቱን ሁሉ መርምሮ አይቶ ይህን ሁሉ አዲስ ነገር ያመጡ ኢትዮጵያውያን ናቸው ብሏል። ደግሞ እነርሱ ግሪኮች የሚያመልኳቸውን ሰባቱን አማልዕክት ጥንት ግብጽን የመሰረቱት የኢትዮጵያ ፈርዕኖች ወይም ንጉሶች ናቸው፤ እኛም አምላክ ያደረግናቸው እነርሱን ነው ሲልም ነው ባለታሪኩ ምስክርነቱን የሰጠው። መጽሐፌን የጻፍኩት ሌሎችም የአፍሪካ፣ የአውሮፓ፣ የአሜሪካ እንዲሁም የተለያዩ የዓለም አቀፍ ታሪክ አጥኚዎች ሁሉ መርምረው የደረሱበትን መረጃ ተንተርሼ ነው። ኢትዮጵያ ግብጽን እንደፈጠረቻትና እንዳሰለጠነቻት በሚለው መጽሐፌ ውስጥ በርካታ ዋቢ መጻሕፍትን ማስረጃ ይሆን ዘንድ አካትቻለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ተደብቆ የቆየና በግዕዝ የተጻፈ የኢትዮጵያ የሆነ ሰነድም በማግኘት በማስረጃ የጻፍኩት እና ያጠናቀሩት መጽሐፍ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ከመጽሐፍዎ ጀርባ የሰፈረው ዋቢ መጽሐፍ፣ መጽሔትና አርቲክል በጣም በርካታ ነውና መጽሐፉን ለማዘጋጀት ምን ያህል ጊዜ ፈጀብዎ?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ስለግብጽ ለማጥናት የወሰደብኝ ጊዜ ከአስር እስከ 15 ዓመት ያህል ነው። ነገር ግን ወደጽሁፍ ሳመጣው የወሰደብኝ የስምንት ወር ያህል ጊዜ ነው፤ እንዲህ ስል ግን ጊዜዬን ሌት ተቀን በመጠቀም ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፡- በመጽሐፍዎ አንድ ቦታ ላይ «አረቦች እንዳይንቁን ታሪካችንን ማወቅ አለባቸው» ሲሉ አስፍረዋል፤ አረቦቹ ይህን ታሪክ እውነት ነው ብለው ለመቀበል ዝግጁ የሚሆኑ ይስልዎታል?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ብዙ ማስረጃ ስለደረደርኩ ሕሊና እና ቅን ልብ ያለው አካል ወዲያው ሊቀበለው ይችላል። በተቃራኒው እውነትን ለመካድ ድርቅ የሚል ካለ ግን እንዴት ሊሆን ይችላል ብሎ ግራ ይጋባ ይሆናል። ወይም ደግሞ ልቦናው እያወቀም ቢሆን ሊቀበል አይፈልግ ይሆናል። እውነታው ግን ግብጻውያን በፒራሚዱም ስራ ላይ ሆነ በግብጽ ስልጣኔ ላይ አለመኖራቸው ነው። አረቦች ከደቡብ አረቢያ ተነስተው እዛ የደረሱት በሰባተኛ መቶ ክፍለ ዘመን ማለትም በእስልምና ዘመን ነው። እኛ በብዙ እንቀድማቸዋለን። ከአገራቸውም ሲመጡ የዚያን አይነት ስልጣኔ ይዘው አልመጡም። አገራቸው ሳሉ አረቢያ በረሃ ውስጥ በግመል የሲራራ ነጋዴዎች ነበሩ። እናም የተሰማሩት በንግድ ስራና በመሳሰለው ላይ ነው። ስለዚህም ስልጣኔው አልነበራቸውም። እንዲያውም ነብዩ መሃመድ እስልምናውን እስከሚያመጡላቸው ድረስ ያመልኩ የነበረው በድንጋይና በጣዖት ነበር።

እኛ ግን በዚያ ጊዜ በብዙ ከመራቀቃችን በተጨማሪ ወደኃይማኖት ፍልስፍና ውስጥ ገብተናል። በመጀመሪያ የአዳምንና የሔዋንን ኃይማኖት፣ በኋላ ላይ ደግሞ የሔኖክን አምላክ እናምን ነበር፤ ከዚያ በኋላ ኢትዮጵያ የተባለው ሰው ያመጣውን ኃይማኖት፣ ቀጥሎም ሙሴ ያመጣውን የአስርቱን ትዕዛዛት እናምን ነበር። እናም በክርስትናው እንቀድማቸው ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ለግብጽ ፖለቲከኞችና ለመሪዎቿ ግልጽ ደብዳቤ በመጽሐፍዎ ላይ አስፍረዋል፤ ካሰፈሩት መልዕክት መካከል ‹እውነቱን ለመናገር እኛ ድሃ አይደለንም› የሚል ይገኝበታል፤ ድሃ ላለመሆናችን ማሳያዎ ምንድን ነው? ለመበልጸግስ ምን ማድረግ አለብን?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ድሃ አለመሆናችን ማሳያው


ፎቶ - ሀዲሽ አብርሃ

አንደኛ እነርሱን መመገባችን ነው። ለአምስት ሺ ዓመት ገደማ በውሃችንና በአፈራችን ስንመግባቸው ኖረናል። ሀብታም ለመሆናችን መረጃው ለምሳሌ በኢትዮጵያ ከርሰ ምድር ኦፓልን ጨምሮ ምንም ያልተነካ የተለያየ አይነት ማዕድን መኖሩ አንዱ ማሳያ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ውሃ ካላቸው ጥቂት የዓለም አገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ናት። መሬቱን ገና አላረስነውም። ለምሳሌ ጀርመን አገር ብትሄጂ ከመኪና መንገድ አስፓልቱ በስተቀር ያልለማ መሬት የለም ማለት ይቻላል። እኛ አገር ሰፊ መሬት እያለን አናርስም። የምንከተለው የተለመደ አይነት አሰራር ነው። ባለን መሬት አርሰንና ተጠቅመን ቢሆን ከስንዴ ልመና ወጥተን ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካንም ጭምር መመገብ በቻልን ነበር።

ላለመበልጸጋችን ትልቁ የእኛ በሽታ ተፈጥሮ ላይ ተረባርበን መስራትና መጠቀም ሲገባን እርስ በእርሳችን መፋጀት ላይ ማተኮራችን ነው። አላሰራ ብሎ ጠፍንጎ የያዘን መገዳደልና መገፋፋት ላይ አተኩረን ስለምንንቀሳቀስ ነው። በድህነት የሚያሽማቅቀን የራሳችን የልብ ክፋትና እርስ በእርስ ለመገዳደል መሽቀዳደማችን ነው። ፈጣሪ በሰጠን ጸጋ ላይ ክንዳችንን አሳይተን ካለብን ጉስቁልና መውጣት ሲገባን የምንረባረበው የገዛ ወገናችን ላይ መሆኑ የከፋ ነው። የተቸረን የተፈጥሮ ሀብት ቢኖርም ትኩረት አድርገን የምንንቀሳቀስ አንዱ አንዱን ለማረድ ስለሆነ የተፈጥሮ መኖር በራሱ ትርጉም የለውም፤ ስለዚህ ጥፋቱ እኛው ላይ ነው።

በእርግጥ እኛ እርስ በእርስ እንድንገዳደል በብዙ የሚጥሩ አሉ። አንዷ ግብጽ ስትሆን ስትተናኮለን የኖረችው ለዘመናት ነው። ኢትዮጵያ ላይ መድረስ ሲያቅታት ግብጽ ውስጥ ያሉ ክርስትያኖችን ማጥቃት ትጀምራለች። የግብጽ ክፋትና ተንኮል የጀመረው ዛሬ አይደለም። ለምሳሌ በፊትም ቢሆን ኢትዮጵያን የጎዱ የግብጽ ጳጳሳት አሉ። እኛ ግብጽን ያሰለጠንን፣ያበላንና አሁን ላለችበት ደረጃ ያደረስን ቢሆንም እጃችን አመድ አፋሽ ሆኗል።

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ እንዳሉትም ሆነ ብዙዎች እንደሚያምኑበት ኢትዮጵያ ታላቅ አገር እንደነበረች ነው፤ ይህን ታላቅነቷን አስቀጥላ ለመጓዝ ምን ማድረግ ይጠበቃል?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ታላቅነትን አስጠብቆ ለመጓዝ ከሁሉ አስቀድሞ ሰላም ያስፈልጋል። ሰውን ለመግደል የተያዘው መሳሪያ ለማረሻነት ሊውል ይገባል። አገሪቱ ሰፊና ገና ያልተነካች በመሆኗ ለሁላችንም ትበቃለች። ስለዚህ ወሳኙና አስፈረላጊው ጉዳይ ሰላም፣ ፍቅርና መግባባት ነው። በአገሪቱ ላይ የሕግ የበላይነት ተጠብቆ ፍትህ ሊሰፍንም የግድ ይላል። ሰዎች በእኩልነት የሚታዩባት እና በነጻነት የሚንቀሳቀሱባት አገር መሆን አለባት። ሁሉም ኢትዮጵያዊ ባመቸው ቦታ ሆኖ አርሶና ነግዶ ብሎም ለምርጫ ተወዳድሮ ፓርላማ የሚገባባት አገር ልትሆን ይገባል። ማንም የትም ቦታ ሲሄድ የባዕድነት ስሜት ሳይሰማው ሀብት አፍርቶና ሀብቱም ተጠብቆለት መኖር የሚችልበት አገር መሆን አለባት። ማንም

# ወቅታዊ

በየትኛውም ስፍራ ያለስጋት የሚኖርባት ሁኔታ ሲፈጠር ያኔ ኢትዮጵያ ልታድግና ልትበለጽግ ትችላለች።

ያለበለዚያ አሁን እንዳለው አይነት በጎሰኝነት ላይ አተኩሮ መሄድ አዋጭ አይሆንም፤ አንተ የእነእከሌ ብሔር ነህ መባባሉ አያዋጣም። አንተ የእኔ ጎሳ ካልሆንክ ከዚህ ውጣ ማለቱ አግባብነት የለውም። ለምሳሌ ብዙ ኢትዮጵያውያን ተሰደው ሌላ አገር በሚሄዱበት ጊዜ ያለምንም አድልዎ መብታቸው ተጠብቆ ይኖራሉ። በርትተው እስከሰሩ ድረስ ደግሞ ሴኔተር እስከመሆን ይደርሳሉ። መብታቸውን በመጠቀም ፖሊሲን መንግስትንም እስከ መክሰስ እና እስከማስፈረድ ደረጃ ይደርሳሉ።

እኛ ግን አንድ ሕዝብ ሆነን እርስ በእርስ መጠቃቃት ማብዛታችን ተገቢ አይደለም። ብሔር ተኮር ጥቃቶች ሁሉ ከኋላ ቀርነትም አልፎ ወንጀል ነው ተብሎ ሕግ ሊደነገግለትና ተግባራዊም ሊሆን ይገባል። ስለሆነም ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወደፈለገበት የኢትዮጵያ ክፍል ሄዶ መስራትና በየትኛውም ዳር ድንበሯ ላይ ሰፍሮ በመኖር ማደግና አገሪቱንም የማበልጸግ መብት እንዲኖረው በሕግ ሊደነገግ ተግባራዊም ሊሆን ይገባል።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ ታላቁ የኢትዮጵያ ዓባይ ግድብ ሶስተኛው ዙር ውሃ ሙሌት በስኬት ተጠናቋል፤ ሁለተኛውም ተርባይን ኃይል ማመንጨት ጀመሯል፤ በብዙ ጫና ውስጥ በመሆን የመጣ ስኬት ነውና ይህ የኢትዮጵያውያኑ ጥንካሬ ድሮ ከነበራቸው ብርታት የመጣ ነው ወይስ ሌላ ምክንያት ይመስልዎታል?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ኢትዮጵያ የአባይ ግድብ መገደቧ አያስደንቅም። ምክንያቱም ‹ኢትዮጵ› የተባለ ኢትዮጵያን በስሙ የሚያስጠራ አንድ ከዛሬ አራት ሺ ዓመት በፊት የነበረ ሰው አለ። ይህ ከፍተኛ ስልጣኔ የነበረው ሰው የሳሌም ንጉስ አብርሃ ሄዶ የሚሰግድለት መልከጸዲቅ የሚባል የእርሱ አባት ነው። ይህ በፈጣሪ ታዝዞ የዓባይ ወንዝ ተከትለህ ጣና ላይ ስፍር ተብሎ የመጣ ነው። ጫካ ለነበረች አፍሪካ ስልጣኔን ያመጣ ነው። እርሱ የወለዳቸው ልጆች ናቸው ዛሬ ኢትዮጵያውያን የሆኑት።

ዛሬ የዓባይን ግድብ ስለገነባን እንደትልቅ ነገር ሊታይ አይገባም። ቀደም ሲል ኢትዮጵያ በሚባለው አባታችን ስም አፍሪካን በሞላ የምናስተዳድር ነበርን። ደግሞም ብዙ የስልጣኔ መሰረት ያለን ሰዎች ነን። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩልሽ ከግብጽ አልፈን ግሪክንና ጣሊያንን ጨምሮ ፍልስፍናና ሳይንስ ስናስተምር የነበርን ሕዝብ ነን።

ስለሆነም አሁን ያለው ትውልድ እርስ በእርስ መገዳደልና በተሳሳተ ትርክት ተነሳስተን በጎሳ ተከፋፍለን ይህን ሁሉ ጥፋት አጥፍተን ዘረኛ ሆነን መጨረሻ ላይ ወደኋላ ቀረን እንጂ የጥንቱን የአባቶቻችንና የእናቶቻችንን ወኔ ብንቀሰቅሰቀው የአባይን ግድብ ሳይሆን መላውን አፍሪካ በሰለጠነ መንገድ ወደፊት እናስተዳድራለን። ስለሆነም የአባይ ግድብ መገደባችን ይህን ያህል አያስደንቅም። ምክንያቱም ካለፈው ስልጣኔያችን ጋር ስናስተያየው የአባይ ግድብ ለኢትዮጵያውያኑ ተራ ነገር ነው ማለት ይቻላል። ዘረኝነትን አስወግደን በሰላም መኖር ከቻልን ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለአውሮፓም ሆነ ለአሜሪካ የምናበረክተው የስልጣኔ ነገር አለ።

**አዲስ ዘመን፡- የአባይ ግድብ እንዳይገደብ በተለይ ብድር ከማስከልከል እስከ ማዕቀብም እንዲጣል ለማድረግ ግብጽ በብዙ ደክማለች፤ ይህ ሩጫዋ ትርፍ አስገኝቶላታል ይላሉ?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ትርፍ ያስገኘላት አይመስለኝም፤ ዓላማዋ ግድቡን ብቻ ማስቆም ከሆነ ይህ አልተሳካላትም። ግድቡ አሁን ያለበት ደረጃ ደርሷል፤ ከዚህም በኋላ ይጠናቀቃል። ከአሁን ወዲያ ደግሞ እነካዋለሁ ብላ ብታስብ በአካልም የሚፈርስ ነገር አይደለም። ግድቡን ለማፍረስ ብትፈልግ እንኳ ውሃው የሚያጥለቀልቀው በመጀመሪያ ሱዳንን ቀጥሎም ግብጽን ነው። ስለዚህ ከዚህ በኋላ ምንም ለማድረግ አይችሉም፤ ዘግይቷል። ውሃው እየጨመረ ስለሚሄድ እነርሱም ተንጫጭተው ዝም ይላሉ።

ነገር ግን ኢትዮጵያ የአባይ ግድብን መገንባቷ ሱዳንንም ሆነ ግብጽን አይጎዳም። ውሃ ከሞላና ተርባይኑን ከመታ በኋላ ይሄዳል እንጂ እዛው አይቆይም። እነርሱ አስተሳሰባቸው ድርቅ ያጠቃናል ከሚል ስጋት ሳይሆን ኢትዮጵያ ለምን ትሻሻላለች ከሚል ምቀኝነት የመነጨ ነው። እኛ አስቀድመን ስልጣኔውን ያስተማርናቸው ኩሩ ሕዝብ ስለሆንን ግብጽ ብቻ ሳትሆን አውሮፓን ጨምሮ የቆየ በቀል አለባቸው። ምክንያቱም በአደዋም ሆነ በማይጨው ሊይዙን አልቻሉም። በቅኝ ግዛትም ማንም ሊይዘን አልቻለም።

**አዲስ ዘመን፡- ከአባይ ግድብ ጋር በተያያዘ የሱዳንን ሁኔታ እንዴት ያዩታል?**



**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** በመጀመሪያ ከግብጽ ጋር ያበሩት የተማሩ ሱዳናውያን አይደሉም። ሌሎቹ ግን በዘራቸው በሚወጡት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ሁሉ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ይዘው ኢትዮጵያ እንደሚወዷት ነው ስሜታቸውን የሚገልጹት። እንዲህም የሚያደርጉት ኢትዮጵያ ጎድታቸው ስለማታውቅም ጭምር ነው። ከዚህ ባሻገር ሱዳን ጥንትም ቢሆን ደግሞ የኢትዮጵያ ግዛት ነበረች። ልክ ግብጽን እንዳቀናን ሁሉ የዛሬ 3 ሺ 700 ዓመት አካባቢ አንደኛ ኢትዮጵያዊ ሄዶ ሱዳንን እንዲያቀና ተደርጓል። ሱዳን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በኢትዮጵያውያን ንጉሶች ትመራ ነበር። በመሆኑም ሱዳንንም እኛ ያሳደግናት ናት ማለት ይቻላል። አሁንም ቢሆን ለሱዳን የምትበጃት ኢትዮጵያ ናት።

**አዲስ ዘመን፡- ለግብጽ የልብ ልብ ሲሰጧት የነበሩ ምዕራባውያኑም ሆኑ ሌሎቹ በኢትዮጵያ ላይ በአንድም በሌላም ተጽዕኖ ማሳደራቸው ይታወቃል፤ ጫና መፍጠራቸው ግብጽ እውነቷን ነው ከሚል የመጣ ነው ወይስ ኢትዮጵያን ከመጥላት ?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ለወያኔ ካላቸው ፍቅር የመጣ ነው። እነዚህ አውሮፓውያን በአጼ ኃይለስላሴም ጊዜ ሆነ በደርግ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው የፈለጉትን ጸያፍ ስራ ሁሉ ማድረግ አይችሉም ነበር። ወያኔ ግን በሩን በስፋት ከፍቶላቸው ግቡ ስላላቸው ሁሉም ነገር እንደልባቸው ከመሆኑም በተጨማሪ መፈንጫ አድርገውት ከርመዋል። ከዚህም የተነሳ ኢትዮጵያ እስከ ፍናፍንቶች ድረስ መፈንጫ ሆነች። በሌላ አነጋገር ወያኔ የእነዚህ አካላት ትጉህ ታዛዥ በመሆን ሲያገለግላቸው ቆይቷል። በምትኩ ደግሞ እነርሱ የሚፈልጉትን ነገር ሁሉ ሲያደርጉላቸው ነበር።

በአሁኑ ወቅት ደግሞ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አመራር ዘመን እኛ የምዕራባውያን መልዕክተኛና አገልጋይ አንሆንም፤ እኛ ራሳችንን የቻልንና ሉዓላዊነታችንን አስከብረን የምንኖር ብሎም ኢትዮጵያን ለማበልጸግ የምንፈልግ፣ ከስንዴ ልመና እና በጥቅሉ ኢትዮጵያ ከልመና ወጥታ ራሷን እንድትችል ለማድረግ ነው ፍላጎታችን ብለው ዶክተር ዐቢይ አውጀዋል። በዚህ ጊዜ ድንጋጤ ተፈጥሮባቸዋል። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ ጥገኛ ላትሆን ነው ወይ? የሚል ስጋት ይፈጠርባቸዋል። ለመላ አፍሪካ በጥንት ዘመን መሪ እንደነበረች ሁሉ አሁንም መሪ ሆና አፍሪካውያን ሁሉ ያላቸውን ማዕድናትና ሀብት አያስበዘብዙንም ብሎም አይታዘዙንም በሚል ስለሚደናጋጡ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ መጥፎ አርአያ ልትሆን ነው። ጥንትም ደግሞ በጦርነቱም ስታሸንፈን የኖረች ናት። አሁን ደግሞ በዚህ አይነት ሁኔታ ራሷን ከቻለች ለእኛ አደገኛ በመሆኑ ያሰጋናል በሚልም ስለሚጨነቁም ጭምር ነው። ኢትዮጵያ ቀይ ባህርን ትቆጣጠራለች የሚል ፍራቻም ስላለባቸው ነው። ኢትዮጵያ ያንን መቆጣጠር ከጀመረች ስለሚጎዱ ለእነርሱ አደገኛ አገር እንደምትሆንባቸው በማሰብ ነው። ስለዚህ ቢቻል መሪውን ማጥቃት ካልሆነ ደግሞ በጎሳ፣ በኃይማኖትና በተለያየ ነገር አገሪቱን ማተራመስና በአገር ግንባታ ላይ እንዳያተኩሩ ብሎም ሰላምና አንድነት እንዳይኖራቸው ማድረግ አለብን ከሚል የመነጨ ነው። ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የኢኮኖሚ ጫና ማሳደር እንዳለባቸው ስለሚያስቡም ጭምር ነው ኢትዮጵያ ላይ ጫና የሚያሳድሩት።

የሌላ አገር ተሞክሮ ሲታይ እንደ ዶክተር ዐቢይ ጠንካራ መሪ ነው የሚሏቸውን ገድለዋል። ለምሳሌ የቤልጂየም ቅኝ ተገዥ የነበረችውን የአልማዝ አገር የሆነው የኮንጎውን ፓትሪስ ሉሙምባ የሚባለውን መሪዋን ቤልጂየምና አሜሪካ ሆነው በሲአይኤ አማካይነት ገደለዋቸዋል። በተመሳሳይ በኩዋሜ ንኩሩህማን መፈንቅለ መንግስት አካሄደው ወደአገራቸው እንዳይገቡ በማድረግ የፈለጉትን አሻንጉሊት የሆነ መሪ አስቀምጠዋል። ቶማስ ሳንካራንም የገደሏቸው እንዲሁ ነው። ስለዚህም የሚፈልጉት ለእነርሱ ተገዢ የሆነን መንግስት ነው።

**አዲስ ዘመን፡-በቅርቡ ስንባብ ያበቁትን መጽሐፍ ወደ አረብኛ ቋንቋ በመተርጎም ማጠናቀቅዎን ተናግረዋል፤ ለአረብኛ ተደራሲያን ለማድረስ የተነሳሱበት ነጥብ ምንድን ነው? በቀጣይስ በሌላ ቋንቋ ለመተርጎም እቅድ አልዎት?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ‹ኢትዮጵያ ግብጽን እንደፈጠረቻትና እንዳሰለጠነቻት› የሚለው መጽሐፍ በአረብኛ ቋንቋ ተተርጉሟል። በቅርቡም ወደመካከለኛው ምስራቅ ለተደራሲያን ይሰራጫል። ግብጽም ይደርሳል። ከአንድ ሁለት ወር በኋላ አዲስ አበባ ላይ የምረቃ ስነስርዓት በሚካሄድበት ጊዜ በአማርኛ የተጻፈውም በወቅቱ አንድ ላይ የሚመረቅ ይሆናል። በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ግብጽንና የመካከለኛው ምስራቅ ዲፕሎማቶችን በዕለቱ እንዲገኙ እጠራቸዋለሁ። በወቅቱ የመጽሐፉን ይዘት ከገለጽኩ በኋላ የመጽሐፍ ፊርማ ስርዓት ይኖራል። ለአምባሳደሮቹም ፊርሜ የምሰጥ ይሆናል።

ከዚህ ቀደም በአረብኛ ከሚተላለፉ በሁለት ሚዲያዎች ላይ ቀርቤ ስለመጽሐፉ ማብራሪያ ሰጥቼያለሁ፤ ፒራሚዱም የእኛ መሆኑን ጠቅሼ እስካሁን ያገኙት ገቢ ብዙ ሚሊዮን ዶላር ስለሆነ ውሃውንና አፈሩን እንኳ ብንተውላቸው እኛ ያለማናቸውና ያሰለጠናቸው በመሆናችን እስካሁን ከተገኘው ገቢ እንዲከፍሉም ተናግሬያለሁ። ከቱሪስት በጣም ብዙ ብር ስለሚያገኙ ነጻ ከወጡበት ካባለፈው 50 ዓመት ጀምሮ ያለው ተደምሮ እንድንካፈል በዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት እጠይቃለሁ። ምክንያቱም እነርሱ የመጡት ትናንት ነው፤ እኛ ስንገነባ በቦታ አልነበሩም የሚለውን ሁሉ በሚዲያ በመጥቀሴ እየተንጫጩ ይገኛሉ። ሌሎች ደግሞ ሐሳቡን ከሰሙ በኋላ ኢትዮጵያውያን በገነቡት ፒራሚድ ነው ግብጽ ስታቅራራ የቆየችው ሲሉ በመደመጥ ላይ ናቸው። ከዚህ በኋላ ደግሞ ሙሉ መረጃውን ሊሰጣቸው የሚችል መጽሐፍ ስለሚመረቅ ቀደም ሲል አገራችን በዲፕሎማሲው መስክ በብዙ ደክማለች። ከዚህ በኋላ ደግሞ የመጽሐፉ መመረቅ የአረብ ዜጎች እኛን እንዲያደንቁንና እውነታውን እንዲያውቁ ይረዳቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ አገር በቀል ዩኒቨርስቲ ለመመስረት እቅድ እንዳልዎ ይነገራልና እዚህ ላይ የሚሉት ነገር ካለ?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ይህ ከኢትዮጵያዊነት ጋር የሚያያዝ ነው። እኛ ጥንታዊ አገር እንደመሆናችን የብዙ እውቀት ባለቤት ነን። ነገር ግን እውቀት በየገደማቱ፣ በየአዋቂው ልብና እጅ ውስጥ ብቻ ቀርቷል። በመሆኑም ይህን እውቀት አሰባስበን እኔና መሪ ጌታ በላይ ዓዳሙ አንድ ማዕከል አዲስ አበባ ላይ አበጅተንለት አብረን በማደራጀት ላይ እንገኛለን። ሌሎችም መሰል እውቀት ያላቸው አካላት በማካተት የመጀመሪያው የአገር በቀል ተቋምን ለማቋቋም ነው ያሰብነው። እኛ ጀምረናል፤ በማስተማር ላይም እንገኛለን። በአሁኑ ሰዓት ግን ቦታ ተውሰን ስለሆነ በቀጣይ ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲቀጥል እንፈልጋለን።

እኛ የራሳችን የሆነ የጥንት ፍልስፍና ብሎም የሕክምና ጥበብ አለን፤ ገና ብዙ ያልተነገሩና ያልተዳሰሱ ታሪኮች ያለን ነን። ትውልዱ አገር በቀል እውቀት ስላልተነገረው ከሌላው ዓለም የሚመጣውን እውቀት ብቻ ስላወቀ በእነሱ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ትርክትን ነው የሚያውቀው። ይህ ደግሞ ዛሬ ላለንበት ጥፋት ብሎም የጎሰኝነትና የዘረኝነት ሁኔታ መሰረት ሆኖታል። ትውልዱ የራሱን አገር በቀል እውቀት ካለማወቁም የተነሳ የሚመጣ ፈተና አለ። ስለዚህ የተከፈተው ማዕከል በአገራችን ውጥንቅጥ የሆነ ነገር እንዳይከሰት ብሎም የሚፈጠርን ችግር ለመቀልበስ አዲሱን ትውልድ ትክክለኛውን የኢትዮጵያን ታሪክና ፍልስፍና እንዲሁም የፖለቲካ ትርክት ላይ ሆኖ እንዲመሰረት የሚያደርግ የትምህርት ተቋም ሆኖ እንዲያገለግል ነው። አሁን ለጊዜው ድግሪ ያላቸውና ኢትዮጵያዊነታቸውን በእጅጉ የሚፈልጉ ሰዎች ናቸው እኛ ዘንድ እየተማሩ ያሉት። ለህጻናቱ ደግሞ ከግብረገብነቱ ጀምሮ ከስር መሰረት ጀምረናል።

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ ብልጽግናዋ የሚረጋገጠው መግባባትና ሰላም ሲኖር እንደሆነ ተናግረዋልና ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚያተላልፉት መልዕክት ካለ?**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** ለኢትዮጵያ የሚያዋጣት ጎሰኝነትንና ዘርኝነትን ትታ በኢትዮጵያዊነት መሄድ ስትችል ነው። በብሔር ላይ የተመሰረተ ማንነት ሳይሆን በኢትዮጵያዊነት ላይ የተመሰረተ ማንነት ነው መሆን ያለበት። ምክንያቱም ሁላችንንም የሚያገናኘን ኢትዮጵያዊ የሚለው ነው። እኔ ለምሳሌ አፋር ውስጥ ሄጄ የወለድኳቸው ልጆች አፋርኛ ተናጋሪ ቢሆኑ፣ ወደኦሮሚያ ክልል ሄጄ ደግሞ እንዲሁ የወለድኳቸው ልጆች ኦሮሚኛ ተናጋሪ ቢሆኑ፣ አማራም ትግራይም እንደሱ ቢሆን ልጆቼ በቋንቋ ባይግባቡ ወንድማማችነታቸው ይሰረዛል? አይሰረዝም። እኔስ የእነርሱን ቋንቋ ባለመናገሬ አባትነቴ ይፋቃል? አይፋቅም። ስለዚህ ለዝምድና ዋና መሰረቱ ቋንቋ ሳይሆን ደምና ዘር ነው። ቋንቋ መግባቢያ ነው። ካልሆነ ግን አንድ ዘር መሆናችንን ትተን ቋንቋ ላይ ብቻ ብናተኩር ተለያይተን እንቀራለን። ጎሳ በራሱ የቋንቋ ክፍል እንጂ የዘር ክፍል አይደለም። ጎሳዎች ስንል ቋንቋዎች እንደማለት ነው። ለምሳሌ አንድ አፍሪካዊ እንግሊዝኛ ስለተናገረ ጥቁርነቱን ሊፍቅለት አይችልም፤ አሊያ እንግሊዝኛ መናገሩ ነጭ ሊያደርገው አይችልም። ስለሆነም እኛ ኢትዮጵያውያን ወደ 84 ያህል ቋንቋ አለን፤ እርሱ መግባቢያችን ነው፤ ዘራችን ግን አንድ በመሆኑ አንለያይም። ስለዚህ ኢትዮጵያዊነት ላይ አተኮርን ማለት ሁላችንንም የሚያገናኘን ጉዳይ ላይ አተኮርን ማለት ነው። ኢትዮጵያ ማለት የክብር ስም ነው። ይህቺን አገር እንደገና በጋራ አሳድገናት የቀድሞ ገናናነትዋን በመመለስ ለሌሎችም የምትተርፍ አገር እናድርጋት እላለሁ። ኢትዮጵያን ፈጣሪ ይጠብቃት።

**አዲስ ዘመን፡- ፕሮፌሰር ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ፕሮፌሰር ፍቅሬ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## በክሬሚያ የሚገኙ የሩስያ መርከቦች የድሮን ጥቃት ደረሰባቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በክሬሚያ የሚገኙ የሩስያ ጦር ኃይሎች የሰው አልባ አውሮፕላን (ድሮን) ጥቃት ዒላማ ሆነዋል። በሴቫስቶፖል ከተማ በሩሲያ ጥቁር ባህር መርከቦች ላይ ጥቃት ለማድረስ ያነጣጠረ የዩክሬን ሰው አልባ አውሮፕላን ቅዳሜ ተመትቶ መውደቁን በሩሲያ የተሾሙት የየግዛቲቱ መሪ ተናግረዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

በኃይል በሩሲያ ግዛትነት ስር በገባችው ክሬሚያ በዚህ ወር በሩሲያ ኃይሎች እና ተተቋማት ላይ ተከታታይ ጥቃቶች ተፈጽመዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት የተባበሩት መንግሥታት ተቆጣጣሪዎች በሩሲያ ቁጥጥር ስር የሚገኘውን የዛፖሪዝሂያ የኒውክሌር ጣቢያን እንዲጎበኙ የሚያስችለውን ስምምነት ተቀብለዋል።

ቅዳሜ ማለዳ ላይ በተሰራጨ አንድ ተንቀሳቃሽ ምስል በሴቫስቶፖል የሩስያ ጥቁር ባህር መርከብ በሚገኝበት አካባቢ ጭስ ሲወጣ አሳይቷል። ቢቢሲ ምስሉን ማረጋገጥ አልቻለም።

በሩሲያ የተሾሙት አስተዳዳሪው ሚካሂል ራዝቮዛይቭ የችግሩን አሳሳቢነት አሳንሰውታል። የመርከቦቹ የአየር መከላከያ ምላሽ በመስጠት የዩክሬን ሰው አልባ አውሮፕላን ማውደሙን ተናግረዋል። "በዋናው መሥሪያ ቤት ጣሪያ ላይ ወድቋል። ምንም ጉልህ ጉዳት አልደረሰም። ማንም አልተጎዳም" ብለዋል። በወሩ መጀመሪያ ላይ በክሬሚያ ምዕራባዊ የባህር ጠረፍ በምትገኘው ሳኪ የሩሲያ ጦር ሰፈር ላይ በተፈጸመ ጥቃት ዘጠኝ የሩስያ ጄቶች ወድመዋል።

በወቅቱ በማሕበራዊ ድረ-ገጾች ላይ የተለቀቁ ተንቀሳቃሽ ምስሎች ብዙ የሩሲያ ቱሪስቶች በአቅራቢያው ካለ ሪዞርት ሲሸሹ ታይቷል። ክሬሚያ እአአ በ2014 በሩስያ የተወረረች እና በኃይል የተወሰደች ሲሆን ዩክሬን ልታስመልሳት ቃል ገብታለች።

የኪዬቭ መንግሥት በቅርብ ጊዜ በተፈፀሙ ጥቃቶች እጁ ስለመኖሩ ከማረጋገጥም ሆነ ከመካድ ተቆጥቧል። የምዕራባውያን ባለሥልጣናት እነዚህ ጥቃቶች በሩሲያ ኃይሎች ላይ ከፍተኛ የሥራ እና የሥነ-ልቦና ተፅእኖ እያሳደሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ በሌላ ዜና የዛፖሪዝሂያ የኑክሌር ጣቢያ ደሕንነት በዓለም አቀፍ ተቆጣጣሪዎች መጎብኘቱ ወደነበረበት ሊመልሰው ይችላል ሲሉ የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎዲሚር ዜለንስኪ ገልጸዋል።

የሩሲያው ቭላድሚር ፑቲን ሞስኮ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተቆጣጣሪዎች ወደ ተቋሙ እንዲገቡ ፈቃድ ትሰጣለች ካሉ በኋላ ነው ይህንን ያሉት። ባለፈው ሳምንት ክሬምሊን እና ኪዬቭ በኒውክሌር ጣቢያው ጥቃት በማድረስ የኒውክለር አደጋ ስጋት ተደቅኗል በማለት እርስ በርስ ሲወነጃጀሉ ነበር።

ሩሲያ ካርኪቭን፣ ዲኒፕሮን እና ማይኮላይቭን እና ሌሎችንም ከተሞች ዒላማ በማድረግ በለሊት የማጥቃት ስልቷን ቀጥላለች። በሩሲያ የተሾሙት የማሪዎፖል ከንቲባ ከግድያ ሙከራ ተርፈዋል ተብሏል።

የሩስያ የመንግሥት ቲቪ ጋዜጠኛ እንዳለው ከንቲባው ኮስትያንቲን ኢቫሽቼንኮ በመኪና ውስጥ እያሉ በአቅራቢያቸው ፍንዳታ መድረሱን ተናግሯል። ቅዳሜ ዕለት ሌሎች ሁለት የእህል መርከቦች ከዩክሬን ከተነሱ በኋላ የተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በቱርክ ጋዜጣዊ መግለጫ ሰጥተዋል።

መርከቦቹ እህል ጭነው ወደ አፍሪካ ቀንድ ማምራታቸውን መመልከት "በጣም ልብ የሚነካ" ነው በማለት ተናግረዋል። እነዚህ መርከቦች "በአስቸኳይ ረሃብ ለሚሰቃዩት እርዳታ" ለማድረስ ይረዳሉ ብለዋል።

ጉቴሬዝ አክለውም ከሩሲያ የምግብ እና ማዳበሪያ ማጓጓዝ መቻሉ እየናረ ከመጣውን የኑሮ ውድነት አንጻር ወሳኝ ነው ብለዋል።



## አውሮፓ በአስርት ዓመታት ውስጥ ባልታየ የከፋ ድርቅ እየተሰቃየች ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአየር ንብረት ተመራማሪዎች ድርቅ፣ የሙቀት መጠን መጨመር እና ሰደድ እሳትን የመሳሰሉት ከባድ የአየር ሁኔታዎች እየጨመሩ መምጣታቸውን እያስጠነቀቁ ነው።

በዚህም አብዛኛው የአውሮፓ ክፍል ከፍተኛ የሚባል የሙቀት መጠን አስመዝግቧል። በእንግሊዝ ወንዞች እየደረቁ ሲሆን ፈረንሳይ ከ7 ሺህ ሄክታር በላይ ደን በሰደድ እሳት ወድሞባታል።

ስፔንም የውሃ መጠኗ ከ40 በመቶ በታች መውረዱን ገልጻለች። ይህ ሁኔታ መላዋን አውሮፓ አስጨንቋል። የውሃ መጠኑ ዝቅ ማለት ባህር ሰርጓጅ የሆኑ ቅርሶችና ያልተፈለጉ ነገሮች ለእይታ እንዲጋለጡ አድርጓል፡፡

በስፔን አርኪኦሎጂስቶች የስፔን የድንጋይ አጥር በመባል የሚታወቁት በውሃ ተሸፍነው የነበሩት የቅድመ ታሪክ ድንጋዮች መገኘታቸው አስደስቷቸዋል፡፡ በአውሮፓ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት የውሃ መጠን በመቀነሱ የጥንት ድንጋዮች እና በ2ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የነበሩ የጦር መርከቦች ብቅ ሊሉ ችለዋል፡፡

በአውሮፓ በተከሰተው ነዳድ ድርቅ ምክንያት ወንዞች እና ሀይቆች ጥቂቶች መስታወስ እስከሚችሉት ድረስ ዝግ ማለቱን ሮይተርስ ዘግቧል፡፡ የውሃ መጠኑ ዝቅ ማለት ባህር ሰርጓጅ የሆኑ ቅርሶችና ያልተፈለጉ ነገሮች ለእይታ እንዲጋለጡ አድርጓል፡፡

በከፍተኛ ድርቅ እየተሰቃየች ባለችው ስፔን፤ አርኪኦሎጂስቶች የስፔን የድንጋይ አጥር በመባል የሚታወቁት በውሃ ተሸፍነው የነበሩት የቅድመ ታሪክ ድንጋዮች መገኘታቸው አስደስቷቸዋል ሲል ዘገባው ጠቅሷል፡፡

በመደበኛ ስያሜያቸው ዶምሌን አፍ ጓደልፔራል የሚባሉት ድንጋዮች የስፔን ባለሥልጣናት የውሃ መጠን በ28 በመቶ ቀንሷል በሚባለው ካሴርስ ማእከላዊ ግዛት በሚገኘው ግድብ አንድ ጫፍ ተጋልጠው ይገኛሉ፡፡

ቦታው በፈረንጆቹ በ1926 በጀርመናዊ ጂኦሎጂስት ሁጎ አበርሜር የተገኘ ሲሆን በ 1963 በስፔኑ ፋራንሲስኮ የገጠር ልማት ፕሮጀክት ጊዜ በጎርፍ ተወስዶ ነበር፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ በትክክል የታየው አራት ጊዜ ብቻ ነው፡፡

በውሃ መጠን መቀነስ ምክንያት በጀመርንም ባሉ ወንዞች የ "ረሃብ ድንጋይ" የሚባለው በራይን ወንዝ ተገኝቷል፡፡

**ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም**

## ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶቹ ከአገልግሎቱ ጋር የተፈራረሙት የመግባቢያ ሰነድ

በጦርነቱ የተጎዱ የትምህርትና የጤና ተቋማትን በተሻለ ሁኔታ መልሶ ለመገንባት የሚያስችል ስምምነት ሰነድ በትምህርት ሚኒስቴር፤ በጤና ሚኒስቴር እና በኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት መካከል ባሳለፍነው ሳምንት ተፈራርመዋል።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ በመርሃ ግብሩ ባደረጉት ንግግር ላይ እንደገለጹት፤ በጦርነቱ ከአራት ሺ በላይ ትምህርት ተቋማት ላይ ጉዳት ደርሷል። ከዚህ ውስጥ አንድ ሺ ሦስት መቶ የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ ወድመዋል። የወደሙትን የትምህርት ተቋማትን በተሻለ ደረጃ መልሶ ለመገንባት ሥራዎች ተጀምረዋ፡፡ በቀጣይ ዓመት ሦስት መቶ የሚደርሱ ትምህርት ቤቶችን ለመገንባት ታቅዷል፤ ለዚህም በተለያየ መልኩ ሀብት ለማሰባሰብ እየተሠራ ነው፡፡

ፕሮፌሰር ብርሃኑ እንደሚገልጹት፤ ከኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ጋር የተደረገው ስምምነትም ዳያስፖራዎች የሚያደርጉትን ድጋፍ በተደራጀ መልኩ ለማሰባሰብ ያግዛል፡፡ ከዳያስፖራውና ከሌሎችም ባለድርሻ አካላት ሀብት በማሰባሰብ ሙሉ በሙሉ የወደሙትን አንድ ሺ ሦስት ትምህርት ቤቶች በአራት ዓመታት ገንብቶ ለማጠናቀቅ በርካታ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉም ይገኛል፡፡

በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የዚህ ሥራ ባለቤቶች መሆናቸውን እንደሚያምኑ የጠቀሱት ሚኒስትሩ ፤ በባለቤትነታቸውም መሰል ችግር ሲፈጠር ገንዘብ ከመሰብሰብ ባለፈ ቀጣይነት ባለው መንገድ የሀገሪቱን ልማት በማገዝ ሀገሪቱን ከልመና ለማላቀቅ የሚደረገው እንቅስቃሴ ላይ መሳተፍ እንዳለባቸውም ያመላክታሉ፡፡



ስምምነቱን ሲፈራረሙ

ከዳያስፖራዎች ከሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ባለፈ እውቀታቸውን እንዲያካፍሉና በቴክኖሎጂ እገዛ እንዲያደርጉ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ለመልሶ ግንባታ የሚሰባሰበው ሀብትም በአግባቡ ጥቅም ላይ የሚውል መሆኑን በመረዳት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በተለያየ መልኩ የተለመደ ትብብራቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪያቸውንም አቅርበዋል።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር ሊያ ታደሰ በበኩላቸው፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተከሰተው ግጭት የጤና ተቋማት ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዋል። በዚህም ምክንያት በእነዚህ ተቋማት አገልግሎት ሲያገኙ የነበሩ በርካታ ዜጎች ለችግር መዳረጋቸውን ያወሳሉ፡፡ እነዚህን ተቋማት ወደ ሥራ ለማስገባት በተደረገው ርብርብ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በግዓብት፣ በመሣሪያና በገንዘብ ስድስት መቶ ሚሊዮን ሀብት ማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን ፤ ጉዳት የደረሰባቸውን ጤና ተቋማት መልሶ ለመገንባት በተሠራው ሥራ ብዙ ጤና ተቋማትን ወደ አገልግሎት መመለስ እንደተቻለም ያብራራሉ፡፡

ዶክተር ሊያ፤ እስካሁን ለተደረገው ድጋፍ ምስጋና ያቀረቡ መሆኑን በመጥቀስ፤ አሁንም ወደ አገልግሎት ያልተመለሱ ጤና ተቋማትን ወደ አገልግሎት ለመመለስ ብዙ ሀብት ስለሚጠይቅ በውስጥና በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና አጋር አካላት ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር መሐመድ እንድሪስ እንደሚገልጹት፤ ዳያስፖራው ለሀገሩ የሚያደርጋቸውን ተሳትፎ ማስተባበር የአገልግሎቱ ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ አገልግሎቱ ከተቋቋመ በኋላ ባሉት ጊዜያት ከሦስት ነጥብ 46 ቢሊዮን ብር በላይ ከዳያስፖራዎች የተሰበሰበ ሲሆን፤ በዘንድሮው ዓመት ብቻ ወደ አንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ለመሰብሰቡ ተችሏል ፡፡

እንደ ዶክተር መሐመድ ገለፃ ፤በውጭ ሀገራት ያለው ዳያስፖራ ሀገሩን በተለያየ አግባብ ሲረዳ የቆየ ቢሆንም ሥርዓት ዘርግቶና በተደራጀ መልኩ ተሳትፎ እንዲያደርግ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ "አይዞን ኢትዮጵያ" የሚል ፕላትፎርም ለመመስረት ተችሏል፡፡ በመሆኑም ዳያስፖራው የተፈጠረው ፕላትፎርም ተጠቅሞ ድጋፉን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡

ዳያስፖራው በተለያየ መልኩ ለሀገሩ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የተፈረመው ስምምነትም ዳያስፖራው በተበታተነ መልኩ ለተለያዩ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችና ለመልሶ ግንባታ ሲያደርግ የቆየውን ድጋፍ በተደራጀ አሠራር አጠናክሮ ለመቀጠል እንደሚያስችልም ያስረዳሉ፡፡ የትምህርት ሚኒስቴር የተጎዱ ትምህርት ቤቶችን በተሻለ ሁኔታ መልሶ ለመገንባት የተለያዩ ተግባራት እያከናወነ እንደሚገኝም ይታወቃል፡፡

የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# አትሌት ሰይፉ ቱራ በቺካጎ ማራቶን ለአሸናፊነት ይጠበቃል

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም አትሌቲክስ የፕላቲኒየም ደረጃ ከተሰጣቸው ጥቂት የጎዳና ላይ ሩጫዎች መካከል አንዱ የሆነው የቺካጎ ማራቶን በመጪው ወር መጀመሪያ ይካሄዳል:: ታሪካዊ በሆነው በዚህ ውድድር ላይም እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በርካታ ዝነኛ አትሌቶች እንዲሁም የውድድሩ የአምና አሸናፊዎችም ተሳታፊ እንደሚሆኑ አረጋግጠዋል:: ከእነዚህ መካከል ኢትዮጵያዊያን የረጅም ርቀት አትሌቶችም በዚህ ውድድር እንደተለመደው አሸናፊ ይሆናሉ በሚል ቅድመ ግምት አግኝተዋል::

በወንዶች በኩል ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከጥቂት ተፎካካሪዎቻቸው ባለፈ እርስ በእርሳቸው ለአሸናፊነት የሚያደርጉት ፍልሚያም ተጠባቂ ሆኗል:: ይህም የሆነበት ምክንያት ተሳትፏቸውን ካረጋገጡት እውቅ አትሌቶች መካከል ባላቸው ፈጣን ሰዓት በቀዳሚነት የተቀመጡት ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች በመሆናቸው ነው:: በግል ፈጣን ሰዓቱ ከአትሌቶች ዝርዝር ሶስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠው አትሌት ሰይፉ ቱራ ደግሞ አሸናፊ ይሆናል በሚል በተለይ ግምት ያገኘ አትሌት ነው:: ይኸውም አትሌቱ ያለፈው ዓመት የቺካጎ ማራቶን አሸናፊ በመሆኑ ነው::

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰው ልጆች የጤና ስጋት በሆነው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ከሁለት ዓመታት መቋረጥ በኋላ በተካሄደው 43ኛው የቺካጎ ማራቶን፤ የወንዶች ውድድር የተጠናቀቀው በኢትዮጵያዊው አትሌት አሸናፊነት ነበር:: በዚህ ውድድር 2:06:12 በሆነ ሰዓት ርቀቱን በማጠናቀቅ ቀዳሚ የሆነው አትሌት ደግሞ ሰይፉ ቱራ ነው:: ይህ የአትሌቱ በውድድሩ ላይ ድጋሚ መሳተፍም ለሁለተኛ ጊዜ አሸናፊ ሊያደርገው እንደሚችል የሚጠበቅ ነው:: አትሌቱ ባለፈው



የአምናው የቺካጎ ማራቶን አሸናፊ አትሌት ሰይፉ ቱራ ዘንድሮም የቦታውን ድል እንደሚደግም ይጠበቃል

የውድድር ዓመት በተካፈለበት የሚላኖ ማራቶን አራተኛ ደረጃን የያዘ ቢሆንም፤ በወቅቱ ያስመዘገበው 2:04:29 የሆነ ሰዓት ግን አትሌቱ ማራቶንን መሮጥ ከጀመረበት እአአ ከ2017 ጀምሮ ፈጣን በሚል ተመዝግቦለታል:: በመሆኑም አትሌቱ ያለውን የርቀቱን እንዲሁም የቦታውን ልምድ ተጠቅሞ አሸናፊ የመሆን እድሉ የሰፋ እንደሚሆንም በስፖርት ቤተሰቡ እምነት አግኝቷል::

በውድድሩ ከሚካፈሉት መካከል 2:03:40 የሆነ ሰዓት ያለው አትሌት ሂርጳሳ ነጋሳ ፈጣኑ ሲሆን፤ ይህንንም ሰዓት እአአ በ2019 የዱባይ ማራቶን ያስመዘገበው ነው:: ሌላኛው የውድድሩ አሸናፊ እና ጠንካራ ተፎካካሪ እንደሚሆን የተገመተው አትሌት ደግሞ ዳዊት ወልዴ ነው:: አትሌቱ ባለፈው ዓመት በተካሄደው የሮተርዳም ማራቶን 2:04:27 የሆነ ሰዓት ሲኖረው፤ ይኸውም የርቀቱ ምርጥ በሚል ተይዞለታል:: 2:04:43 የሆነ ሰዓት ያለው አስራር አብድራህማንም ለአሸናፊነት ከሚፎካከሩት መካከል ይገኝበታል::

የኢትዮጵያዊያኑ አትሌቶች ተፎካካሪና ፈተና እንደሚሆኑ ከሚጠበቁት መካከል አንዱ ዩጋንዳዊው አትሌት ስቴፈን ኪሳ ነው:: በቶኪዮ ኦሊምፒክ 10ሺ ሜትር ሃገሩን የወከለው አትሌቱ በማራቶንም ተሳታፊ ሲሆን፤ የግሉ ፈጣን ሰዓት ደግሞ 2:04:48 ነው:: አትሌቱ በሃምቡርግ፣ ለንደን እና ቶሮንቶ ማራቶኖች ልምድ ያለው ሲሆን፤ ለአሸናፊነት በሚደረገው ፉክር የኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ዋነኛ ፈተና እንደሚሆንም ነው የሚጠበቀው::

በሴቶች በኩል በሚካሄደው ውድድርም በተመሳሳይ የአምናው የውድድሩ አሸናፊ የሆነችው ኬንዊቷ አትሌት ሩት ቼፕንጌቲች በድጋሚ ተካፋይ እንደምትሆን አወዳዳሪዎቹ አሳውቀዋል:: የርቀቱ የ2019 የዓለም ቻምፒዮናዋ አትሌት በዚያው ዓመት በተካፈለችበት የዱባይ ማራቶን አሸናፊ የሆነችበት 2:17:08 የሆነ ሰዓት የግሏ ፈጣን በሚል ተይዞላታል:: ባለፈው ዓመት በተካሄደው የቺካጎ ማራቶን ቀዳሚ ሆና የገባችበት ሰዓት 2:22:31 ነው:: ይሁንና አትሌቷ ኢትዮጵያ ቻምፒዮን በሆነችበትና ያለፈው ወር በተካሄደው የኦሪጎን የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ውድድሩን ለማቋረጥ ተገዳ ነበር:: ይኸውም አትሌቷ በድጋሚ የውድድሩ አሸናፊ ትሆናለች በሚል የተሰጣትን ግምት አጠራጣሪ አድርጎታል:: በኬንያ በኩል ሴልስቲን ቼፕቺርቺር እንዲሁም ቪቪያን ኪፕላጋት የውድድሩ ተካፋዮች እና የሃገራቸው ልጅ ተፎካካሪ እንደሚሆኑ ነው የሚጠበቀው::

በኢትዮጵያ በኩል በብቸኝነት ተካፋይ እንደምትሆን የታወቀችው አትሌት ሄቨን ሃይሉ ናት:: ወጣቷ አትሌት እአአ በ2012 የአምስተርዳም ማራቶን ሶስተኛ ሆና የገባችበት 2:20:19 የሆነ ሰዓት የግሏ ፈጣን ነው:: የዚህ ዓመት የሮተርዳም ማራቶን አሸናፊ የሆነችው አትሌት ሄቨን ከኬንያዊያኑ አትሌቶች ጋር ያላት ተቀራራቢ ሰዓት ሲሆን፤ በዓመቱ ካለችበት መልካም አቋም አንጻር የውድድሩ አሸናፊ ልትሆን እንደምትችል ትጠበቃለች::

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ በደህንነት አጋርነትና በሕልውና በስጋትነት መካከል

ይበል ካሳ

ሰው ያልሆኑ ፍጥረታት እንደሰው ሊያስቡና ሰብዓዊ ዕውቀት ሊኖራቸው ይችላል የሚለው እሳቤ በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተመሠረተ ባይሆንም በአፈ ታሪኮችና በተረቶች አማካኝነት ከጥንት ጀምሮ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ በልዩ ልዩ መንገድ ሲንጸባረቅ የነበረ መሆኑን የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ:: ሰው ሠራሽ ሰብዓዊ አስተውሎት(Artificial Intelligence) የሚለውን አሁን ላይ የሚጠራበትን ስያሜ ያገኘው ግን በአውሮፓውያኑ 1956 ጆን ማካርቲ በተባለ ሳይንቲስት ዳርሙዝ ኮሌጅ አሜሪካን አገር በተካሄደ ጥናታዊ ጉባኤ ላይ ነው::

አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ የተለያዩ የአመክንዮና ኮዶችን በመጠቀም በኮምፒውተር አማካኝነት የሰው ልጆችን አዕምሮ የሚመስል የአስተሳሰብና የዕውቀት ሥርዓትን ለመፍጠር የሚታትር የቴክኖሎጂ ዘርፍ ነው:: ዘርፉ ከላይ እንደተጠቀሰው ከ1950ዎቹ ጀምሮ የተጀመረ ቢሆንም ከፍተኛ ዕድገትና እመርታን ያሳየው ባለፉት አስር ዓመታት መሆኑን መረጃዎች ያመላክታሉ:: በዚህም አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ በአሁኑ ሰዓት በኢኮኖሚክስ፣ በህክምና፣ በኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽንና በሌሎችም በርካታ ዘርፎች በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ እየዋለ ይገኛል::

አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ራሱ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂ አካል እንደመሆኑ መጠን በሰዎች፣ በኮምፒውተሮችና በይነ መረቦች ትስስርና መስተጋብር አማካኝነት በተገነባው ዘመናችን የሳይበር ምህዳር ውስጥ ደግሞ ወሳኝ ሚናን ይጫወታል:: በተለይም የምህዳሩን ደህንነት ከማስጠበቅ አኳያ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ በእጅጉ ተመራጭ እየሆነ መጥቷል:: ምክንያቱ ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ ለጥቃት ተጋላጭ የሆነውን የሳይበር ምህዳር ጥቃቱ ከመፈጸሙ በፊት ሊደርሱ የሚችሉ የሳይበር ጥቃቶችን ቀድሞ ለማወቅና ለመከላከል አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ተወዳዳሪ የሌለው ቴክኖሎጂ ሆኖ በመገኘቱ ነው:: በዚህም አርቲፊሻል ኢንተለጀንስን

> ለአርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ በግብዓትነት የሚያገለግሉት እንደ ባዮሜትሪክስና አልጎሪዝም የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎች የሰዎችን፣ የተቋማትንና የመንግሥታት ግላዊነትና ሚስጥራዊ መረጃዎች በቀላሉ በአጥቂዎችና በሳይበር ወንጀለኞች እንዲታወቁ ዕድል የሚፈጥሩ በመሆናቸው የበለጠ ለጥቃት ተጋላጭ ያደርጋሉ፡፡

በመጠቀም የሳይበር ጥቃቶች ከመድረሳቸው በፊት ትክክለኛ ቅድመ ግምቶችንና ትንበያዎችን መስጠት ስለሚቻል በርካታ የሳይበር ጥቃቶችን ከመድረሳቸው በፊት አስቀድሞ መከላከል የሚቻልበትን ዕድል ይፈጥራል::

ከዚህ አኳያ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ በአሁኑ ሰዓት በበርካታ የበለጸጉ ሀገራት የሚገኙ ትልልቅ ተቋማትና ድርጅቶች ዋነኛ የሳይር ደህንነት ማስተበቂያ መንገድ እየሆነ መጥቷል:: ለአብነት ስታቲስታ የተባለው ታዋቂ ቴክኖሎጂ ኩባንያ በእአአ 2019 ባወጣው መረጃ 83 በመቶ የሚጠጉ መቀመጫቸውን አሜሪካ ውስጥ ያደረጉ ተቋማት ያለአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ተቋማት የሳይበር ደህንነታቸውን ማስጠበቅ የማይቻለቸው መሆኑን የሚያምኑ መሆናቸውን ገልጿል::

በአሁኑ ሰዓት በበይነመረብና በኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕድገት በየጊዜው በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ ያለውን የአምስተኛውን ትውልድ የሳይበር ጥቃት ለመከላከል ከማንኛውም የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂ በላይ አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ተመራጭ ሆኗል:: ምክንያቱም እንደከዚህ በፊቱ ለጥቃት ምላሽ በመስጠት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን አስቀድሞ በመከላከል ላይ የተመሠረተ ንቁና ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት የሚያስችል(Real time prevention) ፈጣን የሳይበር ደህንነት ሥርዓትን ለመዘርጋት አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ዋነኛው ዘዴ ሆኖ በመገኘቱ ነው:: በአርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ አማካኝነት የሳይበር ጥቃቶች ከመፈጸማቸው በፊት አስቀድሞ አጥንቶ ጥቃቶችን በትክክል መተንበይ፣ ሲደርሱም ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት ይቻላል::

ሁለተኛው ነገር በግለሰብ፣ በተቋም በሀገር፣ በቀጠናና በአህጉር ደረጃ ከሚደረግ የተናጠል የሳይበር ደህንነት ሥርዓት ይልቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀናጀና ሁሉንም ያካተተ(Wholistic) የሳይበር ደህንነት ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግና የሳይበር ምህዳሩን በተቀናጀ መንገድ ለመጠበቅ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ፋይዳው የጎላ በመሆኑ ነው:: በመሆኑም የሳይበር አጥቂዎቹ የደረሱበትን ከፍተኛ የእድገት ደረጃ የሚመጥን፣ ዘመኑን የሚዋጂ ስልጡን የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱና ከዚህ አኳያ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ቴክኖሎጂ ከሁሉም የተሻለ አዋጭ ሆኖ በመገኘቱ በዘርፉ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ፈሰስ እየተደረገበት ይገኛል::

ይሁን እንጂ የሳይበር ደህንነትን በማስጠበቅ ረገድ አርቲፊሻል ኢንተሊጀንስ ይህን ያህል ተመራጭና የተሻለ ሆኖ ቢገኝም ልክ እንደማንኛውም የሰው ልጆች ሥራ የራሱን ተያያዥ ጉዳቶች ማምጣቱም አልቀረም:: በዚህ ረገድ በመጀመሪያ የሚጠቀሰው አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ለሳይበር ደህንነት እጅጉን አስፈላጊ የመሆኑን ያህል በዚያው ልክ ለጥቃትም የማጋለጥ ዕድሉም ሰፊ ሆኖ መገኘቱ ቀዳሚው ነው:: ምክንያቱም አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስን በመጠቀም የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎች በተሻለ ፍጥነትና ትክክለኝነት ምህዳሩን መጠበቅና ከጥቃት መከላከል እንደሚችሉት ሁሉ የሳይበር አጥቂዎችና ወንጀለኞችም አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስን በመጠቀም የጥቃት ዘዴያቸውን ይበልጥ ማክበድና በስፋት ጥቃት መፈጸም የሚችሉበትን ዕድል የሚፈጥርላቸው በመሆኑ ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ለአርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ በግብዓትነት የሚያገለግሉት እንደ ባዮሜትሪክስና አልጎሪዝም የመሳሰሉ ቴክኖሎጂዎች የሰዎችን፣ የተቋማትንና የመንግሥታት ግላዊነትና ሚስጥራዊ መረጃዎች በቀላሉ በአጥቂዎችና በሳይበር ወንጀለኞች እንዲታወቁ ዕድል የሚፈጥሩ በመሆናቸው የበለጠ ለጥቃት ተጋላጭ ያደርጋሉ:: አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስን ለመጠቀም ከፍተኛ መጠን ያለው ዳታ የሚያስፈልግ መሆኑና ዳታ በጨመረ ቁጥር ደግሞ ተያያዥ የሳይበር ደህንነት ችግሮች አብረው የሚጨምሩ መሆናቸው እንዲሁም ቴክኖሎጂውን ለመተግበር ከፍተኛ ወጭ የሚጠይቅ መሆኑ ከአርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ተያያዥ ጉዳቶች መካከል አብረው የሚጠቀሱ ተጨማሪ ችግሮች ናቸው::

አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ ምንም እንኳን የሳይበር ደህንነትን ጨምሮ ሌሎች በርካታ ትሩፋቶችን ለሰው ልጆች ያበረከተ ቴክኖሎጂ ቢሆንም በዚያው ልክ ለሳይበር ጥቃት አጋላጭ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከዚህም ያለፈ አጠቃላይ ለሰውልጆች ህልውና ስጋት መሆኑንም የሚገልጹ የዘርፉ ጠቢባን አሉ:: ከአራት ዓመት በፊት ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ታዋቂው እንግሊዛዊ አስትሮ ፊዚስትና ሳይንቲስት ዓለም በቴክኖሎጅ ወለድ ሰው ሰራሽ አስተውሎት(Artificial Intelligence) ልትጠፋ እንደምትችል ከሚያምኑት መካከል አንደኛው ነው:: እንደስቲፈን ሃውኪንግ ዓይነት ምሁራን ለዚህ በምክንያትነት የሚያቀርቡት ደግሞ የአርቴፊሻል ኢንተሊጀንስ የመጨረሻ ዓላማ እንደሰው የሚያስብ ማሽን መፍጠርና ሰውን በአርቴፊሻል ወይንም ሰውሰራሽ አካል መተካት በመሆኑ የሰው ልጅ አንድ ቀን በእዚህ ሰው ሰራሽ አካል ቁጥጥር ስር ሊወድቅና ሊጠፋ ይችላል የሚል ነው:: እኛም በእርግጥም ሁሉም ነገር በአግባቡ ካልሆነ በቀር ዕውቀትም ሊያጠፋ ይችላልና የሰው ልጅ ራሱ በፈጠረው ዕውቀት እንዳይጠፋ አርቴፊሻል ኢንተሊጀንስን በጥንቃቄና በአግባቡ ሊጠቀምበት ይገባል በማለት ጽሑፋችንን በዚሁ እናጠናቃለን::